# መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ።

(ክለሳ.1.20020507)

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ ንጉሡ ፡ ዳዊትም ፡ ሸመገለ ፥ ዕድሜውም ፡ በዛ ፤ ልብስም ፡ ደረቡለት ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አይሞቀውም ፡ ነበር ።

2 ፤ ባሪያዎቹም ፦ ለጌታችን ፣ ለንጉሡ ፡ ድንግል ፡ ትፈለጋለች ፤ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ቆማ ፡ ታገልግለው ፥ በጌታችንም ፡ በንጉሡ ፡ ብብት ፡ ተኝታ ፡ ታሙቀው ፡ አሉት ።

3 ፤ በእስራኤልም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ የተዋበች ፡ ቈንጆ ፡ ፈለጉ ፤ ሱነማዊቱን ፡ አቢሳንም ፡ አገኙ ፥ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ይዘዋት ፡ መጡ ።

4 ፤ ቈንጆዪቱም ፡ እጅግ ፡ ውብ ፡ ነበረች ፤ ንጉሡንም ፡ ትረዳውና ፡ ታገለግለው ፡ ነበር ፥ ንጉሡ ፡ ግን ፡ አያውቃትም ፡ ነበር ።

5 ፤ የአጊትም ፡ ልጅ ፡ አዶንያስ ፦ ንጉሥ ፡ እኾናለኹ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፤ ሠረገላዎችንና ፡ ፈረሰኞዎችን ፣ በፊቱም ፡ የሚሮጡ ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ አዘጋጀ ።

6 ፤ አባቱም ፡ ከቶ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፦ እንዲህ ፡ ለምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ ብሎ ፡ አልተቈጣውም ፡ ነበር ፤ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ከአቤሴሎምም ፡ በኋላ ፡ ተወልዶ ፡ ነበር ።

7 ፤ ሤራውም ፡ ከጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮአብና ፡ ከካህኑ ፡ ከአብያታር ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ እነርሱም ፡ አዶንያስን ፡ ተከትለው ፡ ይረዱት ፡ ነበር ።

8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ካህኑ ፡ ሳዶቅና ፡ የዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፣ ነቢዩም ፡ ናታን ፣ ሳሚም ፣ ሬሲም ፣ የዳዊትም ፡ ኀያላን ፡ ከአዶንያስ ፡ ጋራ ፡ አልነበሩም ።

9 ፤ አዶንያስም ፡ በጎችንና ፡ በሬዎችን ፣ ፍሪዳዎችንም ፡ በዐይንሮጌል ፡ አጠገብ ፡ ባለችው ፡ በዞሔሌት ፡ ድንጋይ ፡ ዘንድ ፡ ሠዋ ፤ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡ ወንድሞቹን ፡ ኹሉ ፥ የንጉሡንም ፡ ባሪያዎች ፥ የይሁዳን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ጠራ ።

10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ነቢዩን ፡ ናታንን ፥ በናያስንም ፥ ኀያላኑንም ፥ ወንድሙንም ፡ ሰሎሞንን ፡ አልጠራም ።

11 ፤ ናታንም ፡ የሰሎሞንን ፡ እናት ፡ ቤርሳቤሕን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራት ፦ ጌታችን ፡ ዳዊት ፡ ሳያውቅ ፥ የአጊት ፡ ልጅ ፡ አዶንያስ ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፡ አልሰማሽምን ፧

12 ፤ አኹንም ፡ ነዪ ፥ የልጅሽን ፡ የሰሎሞንን ፡ ነፍስና ፡ የአንቺን ፡ ነፍስ ፡ እንድታድኚ ፡ እመክርሻለኹ ።

13 ፤ ኼደሽ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ግቢና ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ለእኔ ፡ ለባሪያኽ ፦ ልጅሽ ፡ ሰሎሞን ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይነግሣል ፥ በዙፋኔም ፡ ይቀመጣል ፡ ብለኽ ፡ አልማልኽልኝምን ፧ ስለ ፡ ምንስ ፡ አዶንያስ ፡ ይነግሣል ፧ በዪው ።

14 ፤ እንሆ ፥ አንቺ ፡ በዚያ ፡ ለንጉሥ ፡ ስትነግሪ ፥ እኔ ፡ ከአንቺ ፡ በኋላ ፡ እገባለኹ ፥ ቃልሽንም ፡ አጸናለኹ ።

15 ፤ ቤርሳቤሕም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዕልፍኝ ፡ ገባች ፤ ንጉሡም ፡ እጅግ ፡ ሸምግሎ ፡ ነበር ፥ ሱነማዊቱም ፡ አቢሳ ፡ ታገለግለው ፡ ነበር ።

16 ፤ ቤርሳቤሕም ፡ አጐንብሳ ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሣች ፤ ንጉሡም ፦ ምን ፡ ትፈልጊያለሽ ፧ አለ ።

17 ፤ ርሷም ፡ አለችው ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ለባሪያኽ ፦ ልጅሽ ፡ ሰሎሞን ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይነግሣል ፥ በዙፋኔም ፡ ይቀመጣል ፡ ብለኽ ፥ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምለኽልኛል ፤

18 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ አዶንያስ ፡ መንገሡ ፡ ነው ፤ አንተም ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ይህን ፡ አታውቅም ፤

19 ፤ ርሱም ፡ ብዙ ፡ በሬዎችንና ፡ ፍሪዳዎችን ፣ በጎችንም ፡ ሠውቷል ፥ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፣ ካህኑንም ፡
አብያታርን ፣ የሰራዊቱንም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብን ፡ ጠርቷል ፤ ባሪያኽን ፡ ሰሎሞንን ፡ ግን ፡ አልጠራውም ።

20 ፤ አኹንም ፥ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በዃላ ፡ በጌታዬ ፡ በንጉሥ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠውን ፡
ትነግራቸው ፡ ዘንድ ፥ የእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ዐይን ፡ ይመለከትኻል ።

21 ፤ ይህ ፡ ባይኾን ፥ ጌታዬ ፡ ከአባቶችኽ ፡ ጋራ ፡ ባንቀላፋኽ ፡ ጊዜ ፥ እኔና ፡ ልጄ ፡ ሰሎሞን ፥ እንደ ፡ ኀጢአተኛዎች ፡
እንቈጠራለን ።

22 ፤ እንሆም ፥ ለንጉሡ ፡ ስትናገር ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ ገባ ።

23 ፤ ለንጉሡም ፦ እንሆ ፥ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ መጥቷል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፤ ርሱም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ፊት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡
በግንባሩ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተደፍቶ ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።

24 ፤ ናታንም ፡ አለ ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፦ ከእኔ ፡ በዃላ ፡ አዶንያስ ፡ ይነግሣል ፥ በዙፋኔም ፡ ላይ ፡
ይቀመጣል ፡ ብለኻልን ፧

25 ፤ ርሱ ፡ ዛሬ ፡ ወርዶ ፡ ብዙ ፡ በሬዎችንና ፡ ፍሪዳዎችን ፡ በጎችንም ፡ ሠውቷል ፥ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡
ኹሉ ፥ የሰራዊትንም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብን ፥ ካህኑንም ፡ አብያታርን ፡ ጠርቷል ፤ እንሆም ፥ በፊቱ ፡ እየበሉና ፡
እየጠጡ ፦ አዶንያስ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ ይላሉ ።

26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኔን ፡ ባሪያኽን ፥ ካህኑንም ፡ ሳዶቅን ፥ የዮዳዔንም ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፥ ባሪያኽንም ፡ ሰሎሞንን ፡
አልጠራም ።

27 ፤ በእውኑ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሡ ፡ የተደረገ ፡ ነውን ፧ ለባሪያኽም ፡ ከአንተ ፡ በዃላ ፡ በጌታዬ ፡ በንጉሡ ፡
ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠውን ፡ አልነገርኽምን ፧

28 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፦ ቤርሳቤሕን ፡ ጥሩልኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ገባች ፥ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ቆመች ።

29 ፤ ንጉሡም ፦ ነፍሴን ፡ ከመከራ ፡ ኹሉ ፡ ያዳነኝ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን!

30 ፤ በእውነት ፦ ልጅሽ ፡ ሰሎሞን ፡ ከእኔ ፡ በዃላ ፡ ይነግሣል ፥ በእኔም ፡ ፋንታ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ ይቀመጣል ፡ ብዬ ፡
በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ማልኹልሽ ፥ እንዲሁ ፡ ዛሬ ፡ በእውነት ፡ አደርጋለኹ ፡ ብሎ ፡ ማለ ።

31 ፤ ቤርሳቤሕም ፡ በግንባሯ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተደፍታ ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሣችና ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡
ለዘለዓለም ፡ በሕይወት ፡ ይኑር ፡ አለች ።

32 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፦ ካህኑን ፡ ሳዶቅንና ፡ ነቢዩን ፡ ናታንን ፣ የዮዳዔንም ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ ጥሩልኝ ፡
አለ ። ወደንጉሡም ፡ ፊት ፡ ገቡ ።

33 ፤ ንጉሡም ፡ አላቸው ፦ የጌታችኹን ፡ ባሪያዎች ፡ ይዛችኹ ፡ ኺዱ ፥ ልጄንም ፡ ሰሎሞንን ፡ በበቅሎዬ ፡ ላይ ፡
አስቀምጡት ፥ ወደ ፡ ግዮንም ፡ አውርዱት ፤

34 ፤ በዚያም ፡ ካህኑ ፡ ሳዶቅና ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ አድርገው ፡ ይቅቡት ፤ ቀንደ ፡ መለከትም ፡
ነፍታችኹ ፦ ሰሎሞን ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ በሉ ።

35 ፤ በዃላውም ፡ ተከትላችኹ ፡ ውጡ ፤ ርሱም ፡ መጥቶ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ ይቀመጥ ፥ በእኔም ፡ ፋንታ ፡
ይንገሥ ፤ በእስራኤልና ፡ በይሁዳም ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አዝዥለኹ ።

36 ፤ የዮዳዔም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ መልሶ ፡ ለንጉሡ ፡ አለ ፥ ያበጅ ፡ ያድርግ ፤ የጌታዬም ፡ የንጉሥ ፡ አምላክ ፡ ይህን ፡
ይናገር ።

37 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሥ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁ ፡ ከሰሎሞን ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፥ ዙፋኑንም ፡ ከጌታዬ ፡
ከንጉሡ ፡ ዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የበለጠ ፡ ያድርግ ።

38 ፤ ካህኑም ፡ ሳዶቅና ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፣ የዮዳዔም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፣ ከሊታውያንና ፡ ፈሊታውያንም ፡
ወረዱ ፥ ሰሎሞንንም ፡ በንጉሡ ፡ በዳዊት ፡ በቅሎ ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው ፡ ወደ ፡ ግዮን ፡ አመጡት ።

39 ፤ ካህኑም ፡ ሳዶቅ ፡ ከድንኳኑ ፡ የቅብዓቱን ፡ ቀንድ ፡ ወስዶ ፡ ሰሎሞንን ፡ ቀባ ፤ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ ነፉ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፦ ሰሎሞን ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ አሉ ።

40 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ርሱን ፡ ተከትለው ፡ ወጡ ፥ ሕዝቡም ፡ ዘፈን ፡ ይዘፍኑ ፡ ነበር ፥ በታላቅም ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤ ከጩኸታቸውም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ተናወጠች ።

41 ፤ አዶንያስና ፡ ርሱም ፡ የጠራቸው ፡ ኹሉ ፡ መብሉና ፡ መጠጡ ፡ ተፈጽሞ ፡ ሳለ ፡ ሰሙ ፤ ኢዮአብም ፡ የቀንደ ፡ መለከት ፡ ድምፅ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ ይህ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ የሽብር ፡ ድምፅ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለ ።

42 ፤ ርሱም ፡ ይህን ፡ ሲናገር ፡ የካህኑ ፡ የአብያታር ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ መጣ ፤ አዶንያስም ፦ አንተ ፡ መልካም ፡ ሰው ፡ ነኽና ፥ መልካም ፡ ታወራልናለኽና ፡ ግባ ፡ አለ ።

43 ፤ ዮናታንም ፡ ለአዶንያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፦ በእውነት ፡ ጌታችን ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ሰሎሞንን ፡ አነገሠው ።

44 ፤ ንጉሡም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካህኑን ፡ ሳዶቅንና ፡ ነቢዩን ፡ ናታንን ፡ የዮዳዔንም ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ ከሊታውያንንና ፡ ፈሊታውያንንም ፡ ሰደደ ፥ በንጉሡም ፡ በቅሎ ፡ ላይ ፡ አስቀመጡት ።

45 ፤ ካህኑም ፡ ሳዶቅና ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ በግዮን ፡ ንጉሥ ፡ አድርገው ፡ ቀቡት ፤ ከዚያም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ወጡ ፥ ከተማዪቱም ፡ አስተጋባች ፤ የሰማችኹትም ፡ ድምፅ ፡ ይህ ፡ ነው ።

46 ፤ ደግሞም ፡ ሰሎሞን ፡ በመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጧል ።

47 ፤ የንጉሡም ፡ ባሪያዎች ፡ ገብተው ፦ እግዚአብሔር ፡ የሰሎሞንን ፡ ስም ፡ ከስምኽ ፡ ዙፋኑንም ፡ ከዙፋንኽ ፡ የበለጠ ፡ ያድርግ ፡ ብለው ፡ ጌታችንን ፡ ንጉሡን ፡ ዳዊትን ፡ ባረኩ ፤ ንጉሡም ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ኾኖ ፡ ሰገደ ።

48 ፤ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፦ ዐይኔ ፡ እያየ ፡ ዛሬ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠውን ፡ የሰጠኝ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ አለ ።

49 ፤ አዶንያስም ፡ የጠራቸው ፡ ኹሉ ፡ ፈሩ ፥ ተነሥተውም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየመንገዳቸው ፡ ኼዱ ።

50 ፤ አዶንያስም ፡ ሰሎሞንን ፡ ፈራ ፥ ተነሥቶም ፡ ኼደ ፥ የመሠዊያውንም ፡ ቀንድ ፡ ያዘ ።

51 ፤ ለሰሎሞንም ፦ እንሆ ፥ አዶንያስ ፡ ንጉሡን ፡ ሰሎሞንን ፡ ፈርቶ ፦ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ ባሪያውን ፡ በሰይፍ ፡ እንዳይገድለኝ ፡ ዛሬ ፡ ይማልልኝ ፡ ብሎ ፡ የመሠዊያውን ፡ ቀንድ ፡ ይዟል ፡ አሉት ።

52 ፤ ሰሎሞንም ፦ ርሱ ፡ አካኼዱን ፡ ያሳመረ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከርሱ ፡ አንዲት ፡ ጠጕር ፡ እንኳ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አትወድቅም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክፋት ፡ የተገኘበት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይሞታል ፡ አለ ።

53 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞንም ፡ ላከ ፥ ከመሠዊያውም ፡ አወረዱት ፤ መጥቶም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እጅ ፡ ነሣ ፥ ሰሎሞንም ፦ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ ዳዊትም ፡ የሚሞትበት ፡ ቀን ፡ ቀረበ ፤ ልጁንም ፡ ሰሎሞንን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዘዘው ።

2 ፤ እኔ ፡ የምድሩን ፡ ኹሉ ፡ መንገድ ፡ እኼዳለኹ ፤

3 ፤ በርታ ፡ ሰውም ፡ ኹን ፤ የምታደርገውንና ፡ የምትኼድበትን ፡ ኹሉ ፡ ታከናውን ፡ ዘንድ ፥ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ሥርዐቱንና ፡ ትእዛዛቱን ፡ ፍርዱንና ፡ ምስክሩንም ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፥ በመንገዱም ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፥ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቅ ።

4 ፤ ይኸውም ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እኔ ፦ ልጆችኽ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቢጠብቁ ፥ በፊቴም ፡ በፍጹም ፡ ልባቸውና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሳቸው ፡ በእውነት ፡ ቢኼዱ ፡ ከእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ሰው ፡ አይቈረጥብኽም ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

5 ፤ አንተም ፡ ደግሞ ፡ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፥ ኹለቱን ፡ የእስራኤልን ፡ ጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔርን ፡

የዬቴሩንም ፡ ልጅ ፡ ዐማሳይን ፡ ገድሎ ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ታውቃለኽ ፤ የሰልፉንም ፡ ደም ፡ በሰላም ፡
አፈሰሰ ፥ በወገቡም ፡ ባለው ፡ ድግና ፡ በእግሩ ፡ ባለው ፡ ጫማ ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ አኖረ ።

6 ፤ አንተም ፡ እንደ ፡ ጥበብኽ ፡ አድርግ ፥ ሽበቱንም ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ አታውርደው ።

7 ፤ ከወንድምኽ ፡ ከአቤሴሎም ፡ ፊት ፡ በሸሸኹ ፡ ጊዜ ፡ ቀርበውኛልና ፥ ለገለዓዳዊው ፡ ለቤርዜሊ ፡ ልጆች ፡ መልካም ፡
ቸርነት ፡ አድርግላቸው ፥ በማእድኽም ፡ ከሚበሉት ፡ መካከል ፡ ይኹኑ ።

8 ፤ እኔም ፡ ወደ ፡ መሃናይም ፡ በኼድኹ ፡ ጊዜ ፡ ብርቱ ፡ ርግማን ፡ የረገመኝ ፡ የብራቂም ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የብንያማዊው ፡
የጌራ ፡ ልጅ ፡ ሳሚ ፥ እንሆ ፥ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ዮርዳኖስን ፡ በተሻገርኹ ፡ ጊዜ ፡ ሊቀበለኝ ፡
ወረደ ፥ እኔም ፦ በሰይፍ ፡ አልገድልኽም ፡ ብዬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምዬለታለኹ ።

9 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ጥበበኛ ፡ ሰው ፡ ነኽና ፥ ያለቅጣት ፡ አትተወው ፤ የምታደርግበትንም ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፥ ሽበቱንም ፡
ከደም ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ አውርድ ።

10 ፤ ዳዊትም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ተቀበረ ።

11 ፤ ዳዊትም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የነገሠው ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ። በኬብሮን ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡
ነገሠ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

12 ፤ ሰሎሞንም ፡ በአባቱ ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ፤ መንግሥቱም ፡ እጅግ ፡ ጸና ።

13 ፤ የአጊት ፡ ልጅ ፡ አዶንያስም ፡ ወደሰሎሞን ፡ እናት ፡ ወደ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ መጣ ፤ ርሷም ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ መምጣትኽ ፡
በሰላም ፡ ነውን ፡ አለች ፤

14 ፤ ርሱም ፦ በሰላም ፡ ነው ፡ አለ ። ደግሞም ፦ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ጕዳይ ፡ አለኝ ፡ አለ ፤ ርሷም ፦ ተናገር ፡ አለች ።

15 ፤ ርሱም ፦ መንግሥቱ ፡ ለእኔ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ንጉሥ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
አድርገው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አንቺ ፡ ታውቂያለሽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ኾኖለታልና ፥ መንግሥቱ ፡
ከእኔ ፡ ዐልፎ ፡ ለወንድሜ ፡ ኾኗል ።

16 ፤ አኹንም ፡ አንዲት ፡ ልመና ፡ እለምንሻለኹ ፤ አታሳፍሪኝ ፡ አለ ። ርሷም ፦ ተናገር ፡ አለችው ።

17 ፤ ርሱም ፦ አያሳፍርሽምና ፡ ሱነማዪቱን ፡ አቢሳን ፡ ይድርልኝ ፡ ዘንድ ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንድትነግሪው ፡
እለምንሻለኹ ፡ አለ ።

18 ፤ ቤርሳቤሕም ፦ መልካም ፡ ነው ፥ ስለ ፡ አንተ ፡ ለንጉሡ ፡ እነግረዋለኹ ፡ አለች ።

19 ፤ ቤርሳቤሕም ፡ የአዶንያስን ፡ ነገር ፡ ትነግረው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ገባች ፤ ንጉሡም ፡
ሊቀበላት ፡ ተነሣ ፡ ሳማትም ፥ በዙፋኑም ፡ ተቀመጠ ፤ ለንጉሡም ፡ እናት ፡ ወንበር ፡ አስመጣላት ፥ በቀኙም ፡
ተቀመጠች ።

20 ፤ ርሷም ፦ አንዲት ፡ ታናሽ ፡ ልመና ፡ እለምንኻለኹ ፤ አታሳፍረኝ ፡ አለች ። ንጉሡም ፦ እናቴ ፡
ሆይ ፥ አላሳፍርሽምና ፡ ለምኚ ፡ አላት ።

21 ፤ ርሷም ፦ ሱነማዪቱ ፡ አቢሳ ፡ ለወንድምኽ ፡ ለአዶንያስ ፡ ትዳርለት ፡ አለች ።

22 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ለእናቱ ፡ መልሶ ፦ ሱነማዪቱን ፡ አቢሳን ፡ ለአዶንያስ ፡ ለምን ፡ ትለምኚለታለሽ ፧ ታላቅ ፡
ወንድሜ ፡ ነውና ፥ መንግሥትን ፡ ደግሞ ፡ ለምኚለት ፤ ካህኑም ፡ አብያታርና ፡ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡
ጋራ ፡ ናቸው ፡ አላት ።

23 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፦ አዶንያስ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሕይወቱ ፡ ላይ ፡ አለመናገሩ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይህን ፡ ያድርግብኝ ፥ ይህንም ፡ ይጨምርብኝ ።

24 ፤ አኹንም ፡ ያጸናኝ ፥ በአባቴም ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ያስቀመጠኝ ፥ እንደ ፡ ተናገረውም ፡ ቤትን ፡ የሠራልኝ ፡
ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ዛሬ ፡ አዶንያስ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደላል ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማለ ።

25 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የዮዳሄን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ላከ ፤ ርሱም ፡ ወደቀበት ፥ ሞተም ።

26 ፤ ንጉሡም ፡ ካህኑን ፡ አብያታርን ፦ አንተ ፡ ዛሬ ፡ የሞት ፡ ሰው ፡ ነበርኽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአምላክን ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ተሸከምኽ ፥ አባቴም ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ ኹሉ ፡ አንተ ፡
ስለ ፡ ተቀበልኽ ፡ አልገድልኽምና ፡ በዐናቶት ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ዕርሻኽ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

27 ፤ በሴሎም ፡ በዔሊ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ የተናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ሰሎሞን ፡ አብያታርን ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ክህነት ፡ አወጣው ።

28 ፤ ለኢዮአብም ፡ ወሬ ፡ ደረሰለት ፤ ኢዮአብም ፡ አቤሴሎምን ፡ አልተከተለም ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ አዶንያስን ፡ ተከትሎ ፡
ነበር ። ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ ሸሸቶ ፡ የመሠዊያውን ፡ ቀንድ ፡ ያዘ ።

29 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ኢዮአብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ ሸሸቶ ፡ መሠዊያውን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡
ሰማ ፤ ሰሎሞንም ፡ የዮዳዔን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፥ ኺድ ፡ ውደቅበት ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ።

30 ፤ በናያስም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ መጥቶ ፦ ንጉሡ ፦ ውጣ ፡ ይልኻል ፡ አለው ፤ ርሱም ፦ በዚህ ፡
እሞታለኹ ፡ እንጂ ፡ አልወጣም ፡ አለ ። በናያስም ፦ ኢዮአብ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ የመለሰልኝም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወሬ ፡ አመጣ ።

31 ፤ ንጉሡም ፡ አለው ፦ እንደ ፡ ነገረኽ ፡ አድርግ ፤ ኢዮአብም ፡ በከንቱ ፡ ያፈሰሰውን ፡ ደም ፡ ከእኔና ፡ ከአባቴ ፡ ቤት ፡
ታርቅ ፡ ዘንድ ፡ ገድለኽ ፡ ቅበረው ።

32 ፤ አባቴ ፡ ዳዊት ፡ ሳያውቅ ፡ ከርሱ ፡ የሚሻሉትን ፡ ኹለቱን ፡ ጻድቃን ፡ ሰዎች ፥ የእስራኤልን ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡
የኔርን ፡ ልጅ ፡ አበኔርን ፥ የይሁዳንም ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ የዬቴርን ፡ ልጅ ፡ ዐማሳይን ፥ በሰይፍ ፡
ገድሏልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ደሙን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይመልሰው ።

33 ፤ ደማቸውም ፡ በኢዮአብ ፡ ራስና ፡ በዘሩ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይመለስ ፤ ለዳዊት ፡ ግን ፡ ለዘሩና ፡ ለቤቱ ፡
ለዙፋኑም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኹን ።

34 ፤ የዮዳዔም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ ወጥቶ ፡ ወደቀበት ፡ ገደለውም ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ ባለው ፡ በቤቱ ፡ ተቀበረ ።

35 ፤ ንጉሡም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ የዮዳዔን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ የሰራዊቱ ፡ አለቃ ፡ አደረገ ፤ በአብያታርም ፡ ፋንታ ፡ ካህኑን ፡
ሳዶቅን ፡ አደረገ ።

36 ፤ ንጉሡም ፡ ልኮ ፡ ሳሚን ፡ አስጠራውና ። በኢየሩሳሌም ፡ ቤት ፡ ሥርተኽ ፡ ተቀመጥ ፥ ወዲህና ፡ ወዲያም ፡
አትውጣ ።

37 ፤ በወጣኽበትም ፡ ቀን ፥ የቄድሮንንም ፡ ፈፋ ፡ በተሻገርኽበት ፡ ቀን ፡ ፈጽመኽ ፡ እንድትሞት ፡ ዕወቅ ፤ ደምኽ ፡
በራስኽ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፡ አለው ።

38 ፤ ሳሚም ፡ ንጉሡን ፦ ነገሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ባሪያኽ ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋል ፡
አለው ፤ ሳሚም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ተቀመጠ ።

39 ፤ ከሦስት ፡ ዓመትም ፡ በኋላ ፡ ከሳሚ ፡ ባሪያዎች ፡ ኹለቱ ፡ ወደጌት ፡ ንጉሥ ፡ ወደመዓካ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ አንኩስ ፡
ኰበለሉ ፤ ሳሚንም ፦ እንሆ ፥ ባሪያዎችኽ ፡ በጌት ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

40 ፤ ሳሚም ፡ ተነሣ ፥ አህያውንም ፡ ጫኖ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ወደ ፡ አንኩስ ፡ ዘንድ ፡
ኼደ ፤ ሳሚም ፡ ኼዶ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ከጌት ፡ አመጣ ።

41 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሳሚ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ኼዶ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ ሰማ ።

42 ፤ ንጉሡም ፡ ልኮ ፡ ሳሚን ፡ አስጠራና ። ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ለመኼድ ፡ በወጣኽ ፡ ቀን ፡ ፈጽመኽ ፡ እንድትሞት ፡
ዕወቅ ፡ ብዬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አላስማልኹኽምን ፧ ወይስ ፡ አላስመሰከርኹብኽምን ፧ አንተም ፦ ቃሉ ፡ መልካም ፡
ነው ፥ ሰምቻለኹ ፡ አልኸኝ ።

43 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መሐላ ፡ እኔስ ፡ ያዘዝኹኽን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልጠበቅኽም ፧ አለው ።

44 ፤ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ ሳሚን ፦ አንተ ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ላይ ፡ የሠራኸውን ፡ ልብኽም ፡ ያሰበውን ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡

ታውቃለኽ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ክፋትኽን ፡ በራስኽ ፡ ላይ ፡ ይመልሳል ።

45 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ ግን ፡ የተባረከ ፡ ይኾናል ፥ የዳዊትም ፡ ዙፋን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጸናል ፡
አለው ።

46 ፤ ንጉሡም ፡ የዮዳዔን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ አዘዘው ፥ ወጥቶም ፡ ወደቀበት ፥ ሞተም ። መንግሥትም ፡ በሰሎሞን ፡ እጅ ፡
ጸና ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ለፈርዖን ፡ ዐማች ፡ ኾነ ፤ የፈርዖንን ፡ ልጅ ፡ አገባ ፥ ቤቱንና ፡ የእግዚአብሔርንም ፡
ቤት ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ቅጥር ፡ ሠርቶ ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፡ ወደዳዊት ፡ ከተማ ፡ አመጣት ።

2 ፤ እስከዚያም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ መቅደስ ፡ አልተሠራም ፡ ነበርና ፥ ሕዝቡ ፡ በኰረብታ ፡ ላይ ፡
ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋ ፡ ነበር ።

3 ፤ ሰሎሞንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይወድ ፡ ነበር ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ሥርዐት ፡ ይኼድ ፡ ነበር ፤ ብቻ ፡ በኰረብታ ፡
መስገጃ ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

4 ፤ ገባዖን ፡ ዋና ፡ የኰረብታ ፡ መስገጃ ፡ ነበረችና ፡ ንጉሡ ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚያ ፡ ኼደ ፤ ሰሎሞንም ፡ በዚያ ፡
መሠዊያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ።

5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በገባዖን ፡ ለሰሎሞን ፡ በሌሊት ፡ በሕልም ፡ ተገለጠለት ፤ እግዚአብሔርም ፦ ምን ፡ እንድሰጥኽ ፡
ለምን ፡ አለ ።

6 ፤ ሰሎሞንም ፡ አለ ፦ ርሱ ፡ በፊትኽ ፡ በእውነትና ፡ በጽድቅ ፡ በልብም ፡ ቅንነት ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡
ኼደ ፥ ከባሪያኽ ፡ ከአባቴ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ታላቅ ፡ ቸርነት ፡ አድርገኻል ፤ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ኾነም ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡
የሚቀመጥ ፡ ልጅ ፡ ሰጥተኽ ፡ ታላቁን ፡ ቸርነትኽን ፡ አቈይተኽለታል ።

7 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ እኔን ፡ ባሪያኽን ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፋንታ ፡ አንግሠኸኛል ፤ እኔም ፡
መውጫዬንና ፡ መግቢያዬን ፡ የማላውቅ ፡ ታናሽ ፡ ብላቴና ፡ ነኝ ።

8 ፤ ባሪያኽም ፡ ያለው ፡ አንተ ፡ በመረጥኸው ፡ ሕዝብኽ ፡ ስለ ፡ ብዛቱም ፡ ይቈጠርና ፡ ይመጠን ፡ ዘንድ ፡ በማይቻል ፡
በታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ነው ።

9 ፤ ስለዚህም ፡ በሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ መፍረድ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፥ መልካሙንና ፡ ክፉውንም ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ ለባሪያኽ ፡
አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ስጠው ፤ አለዚያማ ፡ በዚህ ፡ በታላቅ ፡ ሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ ይችላል ፧

10 ፤ ሰሎሞንም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ለመነ ፥ ነገሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ አሠኘው ።

11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፦ ፍርድን ፡ ትለይ ፡ ዘንድ ፡ ለራስኽ ፡ ማስተዋልን ፡ ለመንኽ ፡ እንጂ ፡ ለራስኽ ፡ ብዙ ፡
ዘመናትን ፡ ባለጠግነትንም ፡ የጠላቶችኽንም ፡ ነፍስ ፡ ሳትለምን ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለምነኻልና ፥ እንሆ ፥

12 ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ ቃል ፡ አድርጌልኻለኹ ፤ እንሆ ፥ ማንም ፡ የሚመስልኽ ፡ ከአንተ ፡ በፊት ፡ እንደሌለ ፡ ከአንተም ፡
በኋላ ፡ እንዳይነሣ ፡ አድርጌ ፡ ጥበበኛና ፡ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ሰጥቼኻለኹ ።

13 ፤ ደግሞም ፡ ከነገሥታት ፡ የሚመስልኽ ፡ ማንም ፡ እንዳይኖር ፡ ያልለመንኸውን ፡ ባለጠግነትና ፡ ክብር ፡ ሰጥቼኻለኹ ።

14 ፤ አባትኽም ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ኼደ ፥ ሥርዐቴንና ፡ ትእዛዜን ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ በመንገዴ ፡ የኼድኽ ፡ እንደ ፡
ኾነ ፥ ዕድሜኽን ፡ አረዝመዋለኹ ።

15 ፤ ሰሎሞንም ፡ ነቃ ፥ እንሆም ፥ ሕልም ፡ ነበረ ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጥቶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
ታቦት ፡ ፊት ፡ ቆመ ፥ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አሳረገ ፥ የደኅንነትንም ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ፥ ለባሪያዎቹም ፡
ኹሉ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ።

16 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኹለት ፡ ጋለሞታዎች ፡ ሴቶች ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጥተው ፡ በፊቱ ፡ ቆሙ ።

17 ፤ አንደኛዪቱም ፡ ሴት ፡ አለች ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እኔና ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ እንኖራለን ፤ እኔም ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ በቤት ፡ ሳለኹ ፡ ወለድኹ ።

18 ፤ እኔ ፡ ከወለድኹ ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ ደግሞ ፡ ወለደች ፤ እኛ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ዐብረን ፡ ነበርን ፥ ከኹለታችንም ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም ።

19 ፤ ርሷም ፡ በላዩ ፡ ስለ ፡ ተኛችበት ፡ የዚች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ በሌሊት ፡ ሞተ ።

20 ፤ ርሷም ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ ተነሥታ ፥ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ተኝቼ ፡ ሳለኹ ፥ ልጄን ፡ ከአጠገቤ ፡ ወሰደች ፥ በብብቷም ፡ አደረገችው ፥ የሞተውንም ፡ ልጇን ፡ በእኔ ፡ ብብት ፡ አደረገች ።

21 ፤ ልጄንም ፡ አጠባ ፡ ዘንድ ፡ በማለዳ ፡ ብነሣ ፥ እንሆ ፥ ሞቶ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ብርሃን ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ተመለከትኹት ፥ እንሆም ፥ የወለድኹት ፡ ልጄ ፡ አልነበረም ።

22 ፤ ኹለተኛዪቱም ፡ ሴት ፦ ደኅነኛው ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፥ የሞተውም ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንቺ ፡ እንደምትዪው ፡ አይደለም ፡ አለች ። ይህችም ፦ የሞተው ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፥ ደኅነኛውም ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ አለች ፤ እንዲሁም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ይነጋገሩ ፡ ነበር ።

23 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፦ ይህች ፦ ደኅነኛው ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፥ የሞተውም ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ትላለች ፤ ያችኛዪቱም ፦ አይደለም ፥ የሞተው ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ደኅነኛውም ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ትላለች ፡ አለ ።

24 ፤ ንጉሡም ፦ ሰይፍ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ፤ ሰይፍም ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ፊት ፡ መጡ ።

25 ፤ ንጉሡም ፦ ደኅነኛውን ፡ ሕፃን ፡ ለኹለት ፡ ከፍላችኹ ፡ ለአንዲቱ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፥ ለኹለተኛዪቱም ፡ ኹለተኛውን ፡ ክፍል ፡ ስጡ ፡ አለ ።

26 ፤ ደኅነኛውም ፡ የነበራት ፡ ሴት ፡ አንዠቷ ፡ ስለ ፡ ልጇ ፡ ናፍቋልና ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ደኅነኛውን ፡ ለርሷ ፡ ስጣት ፡ እንጂ ፡ አትግደል ፡ ብላ ፡ ለንጉሡ ፡ ተናገረች ። ያችኛዪቱ ፡ ግን ፦ ይከፈል ፡ እንጂ ፡ ለኔም ፡ ለአንቺም ፡ አይኹን ፡ አለች ።

27 ፤ ንጉሡም ፡ መልሶ ፦ ይህችኛዪቱ ፡ እናቱ ፡ ናትና ፥ ደኅነኛውን ፡ ሕፃን ፡ ለርሷ ፡ ስጧት ፡ እንጂ ፡ አትግደሉት ፡ አለ ።

28 ፤ ንጉሡም ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ እስራኤል ፡ ዅሉ ፡ ሰሙ ፤ ፍርድን ፡ ለማድረግ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ እንደ ፡ ነበረበት ፡ አይተዋልና ፥ ንጉሡን ፡ ፈሩ ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ምዕራፍ ፡ 4 ።

1 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በእስራኤል ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ነግሦ ፡ ነበር ።

2 ፤ የነበሩትም ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ ካህኑ ፡ ዐዛርያስ[158] ፥

3 ፤ ጸሓፊዎቹም ፡ የሴባ ፡ ልጆች ፡ ኤልያፍና ፡ አኪያ ፥ ታሪክ ፡ ጸሓፊም ፡ የአኺሉድ ፡ ልጅ ፡ ኢዮሳፍጥ ፥

4 ፤ የዮዳዔም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ የሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤ ሳዶቅና ፡ አብያታርም ፡ ካህናት ፡ ነበሩ ፤

5 ፤ የናታንም ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፡ የሹሞች ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤ የናታንም ፡ ልጅ ፡ ዛቡድ ፡ የንጉሡ ፡ አማካሪና ፡ ወዳጅ ፡ ነበረ ፤

6 ፤ አኺሳርም ፡ የቤት ፡ አዛዥ ፥ የዓብዳም ፡ ልጅ ፡ አዶኒራም ፡ አስገባሪ ፡ ነበረ ።

7 ፤ ለንጉሡና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡም ፡ ቀለብ ፡ የሚሰጡ ፡ በእስራኤል ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሹሞች ፡ ለሰሎሞን ፡ ነበሩት ። ከዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ አንዱን ፡ ወር ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ይቀልቡ ፡ ነበር ።

8 ፤ ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ በተራራማው ፡ አገር ፡ በኤፍሬም ፡ የሑር ፡ ልጅ ፤

9 ፤ በማቃጽና ፡ በሸዓልቢም ፡ በቤትሳሚስና ፡ በኤሎንቤትሐናን ፡ የዴቀር ፡ ልጅ ፤

158 ዕብ. ፥ ዐዛርያ ።

10 ፤ በአሩቦት ፡ የሔሴድ ፡ ልጅ ፥ ለርሱም ፡ ሰኰትና ፡ የኦፌር ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ነበረ ፤

11 ፤ በዶር ፡ አገር ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፡ የዐሚናዳብ ፡ ልጅ ፥ ርሱም ፡ የሰሎሞንን ፡ ልጅ ፡ ጣፈትን ፡ አግብቶ ፡ ነበር ፤

12 ፤ ከቤትሳን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ አቤልምሖላና ፡ እስከዮቅምዓም ፡ ማዶ ፡ ድረስ ፡ በታዕናክና ፡ በመጊዶ ፡ በጸርታንም ፡
አጠገብ ፡ በኢይዝራኤል ፡ በታች ፡ ባለው ፡ በቤትሳን ፡ ኹሉ ፡ የአኂሉድ ፡ ልጅ ፡ በዓና ፡ ነበረ ፤

13 ፤ በሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ የጌበር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ ለርሱም ፡ በገለዓድ ፡ ያሉት ፡ የምናሴ ፡ ልጅ ፡ የኢያዕር ፡ መንደሮች ፡
ነበሩ ፤ ለርሱም ፡ ደግሞ ፡ በባሳን ፡ በአርጎብ ፡ ዳርቻ ፡ ያሉት ፡ ቅጥርና ፡ የናስ ፡ መወርወሪያዎች ፡ የነበረባቸው ፡ ስድሳ ፡
ታላላቅ ፡ ከተማዎች ፡ ነበሩበት ፤

14 ፤ በመሃናይም ፡ የዒዶ ፡ ልጅ ፡ አኂናዳብ ፤

15 ፤ በንፍታሌም ፡ አኪማዐስ ፡ ነበረ ፥ ርሱም ፡ የሰሎሞንን ፡ ልጅ ፡ ባስማትን ፡ አግብቶ ፡ ነበር ፤

16 ፤ በአሴር[159]ና ፡ በበዓሎት ፡ የኩሲ ፡ ልጅ ፡ በዓና ፤

17 ፤ በይሳኮር ፡ የፋሩዋ ፡ ልጅ ፡ ኢዮሳፍጥ ፤

18 ፤ በብንያም ፡ የኤላ ፡ ልጅ ፡ ሳሚ ፤

19 ፤ በአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ በሴዎንና ፡ በባሳን ፡ ንጉሥ ፡ በዐግ ፡ አገር ፥ በገለዓድ ፡ አገር ፥ የኡሪ ፡ ልጅ ፡ ጌበር ፡
ነበረ ፤ በዚያችም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ርሱ ፡ ብቻውን ፡ ሹም ፡ ነበረ ።

20 ፤ ይሁዳና ፡ እስራኤልም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ብዛት ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፤ በልተውም ፡ ጠጥተውም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡
ነበር ።

21 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከወንዙ ፡ ዠምሮ ፡ እስከግብጽ ፡ ዳርቻ ፡ እስከ ፡ ፍልስጥኤም ፡ ድረስ ፡ በመንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡
ነግሦ ፡ ነበር ፤ ግብርም ፡ ያመጡለት ፡ ነበር ፥ በዕድሜውም ፡ ሙሉ ፡ ለሰሎሞን ፡ ይገዙ ፡ ነበር ።

22 ፤ ለሰሎሞንም ፡ ለቀን ፡ ለቀኑ ፡ ቀለብ ፡ የሚኾን ፡ ሠላሳ ፡ ኰር ፡ መልካም ፡ ዱቄትና ፡ ስድሳ ፡ ኰር ፡ መናኛ ፡ ድቄት ፥

23 ፤ ከዋላና ፡ ከሚዳቋ ፡ ከበረሓ ፡ ፍየልና ፡ ከሰቡ ፡ ወፎች ፡ በቀር ፡ ዐሥር ፡ ፍሪዳዎች ፡ ኻያም ፡ የተሰማሩ ፡ በሬዎች ፡
አንድ ፡ መቶም ፡ በጎች ፡ ነበረ ።

24 ፤ ከወንዙ ፡ ወዲህ ፡ ባሉት ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ከወንዙም ፡ ወዲህ ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከቲፍሳ ፡ ዠምሮ ፡
እስከ ፡ ጋዛ ፡ ድረስ ፡ ነግሦ ፡ ነበር ፤ በዙሪያውም ፡ ባለው ፡ በኹሉ ፡ ወገን ፡ ሰላም ፡ ኾኖለት ፡ ነበር ።

25 ፤ በሰሎሞንም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ይሁዳና ፡ እስራኤል ፡ ከዳን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ድረስ ፡ እያንዳንዱ ፡
ከወይኑና ፡ ከበለሱ ፡ በታች ፡ ተዘልሎ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ።

26 ፤ ለሰሎሞንም ፡ በአርባ ፡ ሺሕ ፡ ጋጥ ፡ የሚገቡ ፡ የሠረገላ ፡ ፈረሶች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ ሺሕ ፡ ፈረሰኛዎች ፡
ነበሩት ።

27 ፤ እነዚያም ፡ ሹሞች ፡ እያንዳንዱ ፡ በየወሩ ፡ ንጉሡን ፡ ሰሎሞንንና ፡ ወደንጉሡ ፡ ወደሰሎሞን ፡ ማእድ ፡
የሚቀርቡትን ፡ ኹሉ ፡ ይቀልቡ ፡ ነበር ፤ ምንም ፡ አያጐድሉም ፡ ነበር ።

28 ፤ እያንዳንዱም ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ለፈረሶቹና ፡ ለሰጋር ፡ በቅሎዎች ፡ ገብስና ፡ ጭድ ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ያመጡ ፡
ነበር ።

29 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለሰሎሞን ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ጥበብና ፡ ማስተዋል ፡ በባሕርም ፡ ዳር ፡ እንዳለ ፡ አሸዋ ፡ የልብ ፡
ስፋት ፡ ሰጠው ።

30 ፤ የሰሎሞንም ፡ ጥበብ ፡ በምሥራቅ ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ጥበብና ፡ ከግብጽ ፡ ጥበብ ፡ ኹሉ ፡ በለጠ ።

159 ዕብ. ፥ አሼር ።

31 ፤ ከሰውም ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ከኢይዝራኤላዊው ፡ ከኤታንና ፡ ከማሖል[160] ፡ ልጆች ፣ ከሄማን[161]ና ፡ ከከልቀድ ፣ ከደራልም ፡ ይልቅ ፡ ጥበበኛ ፡ ነበረ ። በዙሪያውም ፡ ባሉ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ዝናው ፡ ወጣ ።

32 ፤ ርሱም ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ምሳሌዎች ፡ ተናገረ ፤ መሐልዩም ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ ነበረ ።

33 ፤ ስለ ፡ ዛፍም ፡ ከሊባኖስ ፡ ዝግባ ፡ ዠምሮ ፡ በቅጥር ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ እስከሚበቅለው ፡ እስከ ፡ ሂሶጵ ፡ ድረስ ፡ ይናገር ፡ ነበር ፤ ደግሞም ፡ ስለ ፡ አውሬዎችና ፡ ስለ ፡ ወፎች ፡ ስለ ፡ ተንቀሳቃሾችና ፡ ስለ ፡ ዓሣዎች ፡ ይናገር ፡ ነበር ።

34 ፤ ከአሕዛብም ፡ ኹሉ ፥ ጥበቡንም ፡ ሰምተው ፡ ከነበሩ ፡ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ለመስማት ፡ ሰዎች ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።



ምዕራፍ ፡ 5 ።

1 ፤ የጢሮስ ፡ ንጉሥ ፡ ኪራም ፡ ለዳዊት ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ወዳጅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፥ ሰሎሞን ፡ በአባቱ ፡ ፋንታ ፡ ንጉሥ ፡ ለመኾን ፡ እንደ ፡ ተቀባ ፡ ሰምቶ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ሰደደ ።

2 ፤ ሰሎሞንም ፡ ወደ ፡ ኪራም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ላከ ።

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ እስኪጥልለት ፡ ድረስ ፡ በዙሪያው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሰልፍ ፡ አባቴ ፡ ዳዊት ፡ የአምላኩን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ እንዳልቻለ ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ።

4 ፤ አኹንም ፡ አምላኬ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዙሪያዬ ፡ ካሉት ፡ ዕረፍት ፡ ሰጥቶኛል ፤ ጠላትም ፡ ክፉም ፡ ነገር ፡ የለብኝም ።

5 ፤ እንሆም ፥ እግዚአብሔር ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፦ ባንተ ፡ ፋንታ ፡ በዙፋንኽ ፡ ላይ ፡ የማስቀምጠው ፡ ልጅኽ ፡ ርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ነገረው ፥ ለአምላኬ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ እሠራ ፡ ዘንድ ፡ ዐስባለኹ ።

6 ፤ አኹንም ፡ ከወገኔ ፡ እንደ ፡ ሲዶናውያን ፡ ዕንጨት ፡ መቈረጥ ፡ የሚያውቅ ፡ እንደሌለ ፡ ታውቃለኽና ፡ የዝግባ ፡ ዛፍ ፡ ከሊባኖስ ፡ ይቈርጡልኝ ፡ ዘንድ ፡ ባሪያዎችኽን ፡ እዘዝ ፤ ባሪያዎቼም ፡ ከባሪያዎችኽ ፡ ጋራ ፡ ይኹኑ ፤ የባሪያዎችኽንም ፡ ዋጋ ፡ እንደተናገርኸው ፡ ኹሉ ፡ እሰጥኻለኹ ።

7 ፤ ኪራምም ፡ የሰሎሞንን ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለውና ፦ በዚህ ፡ በታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ጥበበኛ ፡ ልጅ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ ይመስገን ፡ አለ ።

8 ፤ ኪራምም ፦ የላክኽብኝን ፡ ኹሉ ፡ ሰማኹ ፤ ስለ ፡ ዝግባውና ፡ ስለ ፡ ጥዱ ፡ ዕንጨት ፡ ፈቃድኽን ፡ ኹሉ ፡ አደርጋለኹ ።

9 ፤ ባሪያዎቼ ፡ ከሊባኖስ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ይጐትቱታል ፤ እኔም ፡ በታንኳ ፡ አድርጌ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እያንሳፈፍኹ ፡ አንተ ፡ እስከወሰንኸው ፡ ስፍራ ፡ ድረስ ፡ አደርስልኻለኹ ፥ በዚያም ፡ እፈታዋለኹ ፥ አንተም ፡ ከዚያ ፡ ታስወስደዋለኽ ፤ አንተም ፡ ፈቃዴን ፡ ታደርጋለኽ ፤ ለቤቴም ፡ ቀለብ ፡ የሚኾነውን ፡ ትሰጠኛለኽ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ላከ ።

10 ፤ እንዲሁም ፡ ኪራም ፡ የዝግባውንና ፡ የጥዱን ፡ ዕንጨት ፡ እንደሚሻው ፡ ያኽል ፡ ኹሉ ፡ ለሰሎሞን ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ።

11 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለኪራም ፡ ስለ ፡ ቤቱ ፡ ቀለብ ፡ ኻያ ፡ ሺ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ስንዴ ፡ ኻያ ፡ ኰርም ፡ ጥሩ ፡ ዘይት ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ፤ ሰሎሞንም ፡ ለኪራም ፡ በየዓመቱ ፡ ይህን ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ።

12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ለሰሎሞን ፡ ጥበብን ፡ ሰጠው ፤ በኪራምና ፡ በሰሎሞንም ፡ መካከል ፡ ሰላም ፡ ነበረ ፤ ኹለቱም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተጋቡ ።

13 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ገባሮቹን ፡ መርጦ ፡ አወጣ ፤ የገባሮቹም ፡ ቍጥር ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበረ ።

14 ፤ በየወሩም ፡ እያከታተለ ፡ ወደ ፡ ሊባኖስ ፡ ዐሥር ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ይሰድ ፡ ነበር ፤ አንድ ፡ ወርም ፡ በሊባኖስ ፡ ኹለት ፡ ወርም ፡ በቤታቸው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ። አዶኒራምም ፡ አስገባሪ ፡ ነበረ ።

15 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሰባ ፡ ሺሕ ፡ ተሸካሚዎች ፥ ሰማንያ ፡ ሺሕም ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ የሚጠርቡ ፡ ጠራቢዎች ፡ ነበሩት ።

160 ዕብ. ፡ ማሖል ፡ (ማሕሌት • በቁሙ) ።

161 ዕብ. ፥ ሄይማን ፡ (ሀይማኒ • አማኝ) ።

16 ፤ ይኸውም ፡ በሠራተኛው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ከተሾሙት ፡ ከሦስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ሌላ ፡ ነው ።

17 ፤ ንጉሡም ፡ ታላላቅ ፡ ምርጥ ፡ ምርጥ ፡ ድንጋዮችን ፡ ይፈፍሩና ፡ ይጠርቡ ፡ ዘንድ ፡ ለቤቱም ፡ መሠረት ፡ ይረበርቡት ፡
ዘንድ ፡ አዘዘ ።

18 ፤ የሰሎሞንና ፡ የኪራምም ፡ ዐናጢዎች ፡ ጌባላውያንም ፡ ወቀሯቸው ፥ ቤቱንም ፡ ለመሥራት ፡ ዕንጨቱንና ፡
ድንጋዮቹን ፡ አዘጋጁ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ምዕራፍ ፡ 6 ።

1 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከወጡ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ ሰሎሞን ፡
በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፥ ዚፍ ፡ በሚባለው ፡ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡
መሥራት ፡ ዠመረ ።

2 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሠራው ፡ ቤት ፡ ርዝመቱ ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ኻያ ፡
ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

3 ፤ በመቅደሱም ፡ ፊት ፡ ወለል ፡ ነበረ ፤ ርዝመቱም ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ወርድ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ከቤቱ ፡ ወደ ፡
ፊት ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

4 ፤ ለቤቱም ፡ በዐይነ ፡ ርግብ ፡ የተዘጉ ፡ መስኮቶች ፡ አደረገ ።

5 ፤ በቤቱም ፡ ግንብ ፡ ዙሪያ ፥ በመቅደሱና ፡ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ግንብ ፡ ዙሪያ ፥ ደርብ ፡ ሠራ ፥ በዙሪያውም ፡
ጓዳዎች ፡ አደረገ ።

6 ፤ የታችኛውም ፡ ደርብ ፡ ወርዱ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ የመካከለኛው ፡ ደርብ ፡ ወርዱ ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፥ የሦስተኛውም ፡
ደርብ ፡ ወርዱ ፡ ሰባት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ። ሠረገላዎቹ ፡ በቤቱ ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገቡ ፡ ከቤቱ ፡ ግንብ ፡ ውጭ ፡
አረፍቶች ፡ አደረገ ።

7 ፤ ቤቱም ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽመው ፡ በተወቀሩ ፡ ድንጋዮች ፡ ተሠራ ፤ በተሠራም ፡ ጊዜ ፡ መራጃና ፡ መጥረቢያ ፡
የብረትም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አልተሰማም ።

8 ፤ የታችኛውም ፡ ደርብ ፡ ጓዳዎች ፡ በር ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ መካከለኛው ፡
ደርብ ፥ ከመካከለኛውም ፡ ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ ደርብ ፡ በመውጫ ፡ ያስወጣ ፡ ነበር ።

9 ፤ ቤቱንም ፡ ሠርቶ ፡ ፈጸመው ፤ በዝግባው ፡ ሠረገላዎችና ፡ ሳንቃዎች ፡ ከደነው ።

10 ፤ በቤቱም ፡ ኹሉ ፡ ዙሪያ ፡ ቁመታቸው ፡ ዐምስት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ደርቦች ፡ ሠራ ፤ ከቤቱም ፡ ጋራ ፡
በዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ አጋጠማቸው ።

11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ መጣ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦

12 ፤ ስለዚህ ፥ ስለምትሠራው ፡ ቤት ፡ በሥርዐቴ ፡ ብትኼድ ፥ ፍርዴንም ፡ ብታደርግ ፥ ትመላለስበትም ፡ ዘንድ ፡
ትእዛዜን ፡ ኹሉ ፡ ብትጠብቅ ፥ ለአባትኽ ፡ ለዳዊት ፡ የነገርኹትን ፡ ቃል ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አጸናለኹ ።

13 ፤ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ እኖራለኹ ፥ ሕዝቤንም ፡ እስራኤልን ፡ አልጥልም ።

14 ፤ ሰሎሞንም ፡ ቤቱን ፡ ሠራው ፥ ፈጸመውም ።

15 ፤ የቤቱንም ፡ ግንብ ፡ ውስጡን ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ለበጠ ፤ ከቤቱም ፡ መሠረት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ጣራው ፡ ድረስ ፡
ውስጡን ፡ በዕንጨት ፡ ለበጠው ፤ ደግሞም ፡ የቤቱን ፡ ወለል ፡ በጥድ ፡ ዕንጨት ፡ ከደነው ።

16 ፤ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ኋለኛውን ፡ ኻያውን ፡ ክንድ ፡ በዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ ጋረደው ።

17 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ፊት ፡ ያለውም ፡ መቅደስ ፡ ርዝመቱ ፡ አርባ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

18 ፤ የቤቱንም ፡ ውስጥ ፡ በተጕበጕበና ፡ በፈነዳ ፡ አበባ ፡ በተቀረጸ ፡ ዝግባ ፡ ለበጠው ፤ ኹሉም ፡ ዝግባ ፡

ነበረ ፤ ድንጋዩም ፡ አልታየም ፡ ነበር ።

19 ፤ በዚያም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ያኖር ፡ ዘንድ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳኑን ፡ አበጀ ።

20 ፤ የቅድስተ ፡ ቅዱሳንም ፡ ርዝመት ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ስፋቱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ በጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ለበጠው ።

21 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ፊት ፡ ከዝግባ ፡ የተሠራ ፡ መሠዊያ ፡ አደረገ ፤ በጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ለበጠው ።

22 ፤ ቤቱንም ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ በወርቅ ፡ ለበጠው ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ፊት ፡ የነበረውን ፡ መሠዊያ ፡ ኹሉ ፡ በወርቅ ፡ ለበጠው ።

23 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ውስጥ ፡ ቁመታቸው ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ከወይራ ፡ ዕንጨት ፡ ኹለት ፡ ኪሩቤል ፡ ሠራ ።

24 ፤ የኪሩብም ፡ አንደኛው ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ የኪሩብም ፡ ኹለተኛው ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ከአንደኛው ፡ ክንፍ ፡ ጫፍ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ኹለተኛው ፡ ክንፍ ፡ ጫፍ ፡ ድረስ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

25 ፤ ኹለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ኹለቱም ፡ ኪሩቤል ፡ አንድ ፡ ልክና ፡ አንድ ፡ መልክ ፡ ነበረ ።

26 ፤ የአንዱ ፡ ኪሩብ ፡ ቁመት ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የኹለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ።

27 ፤ ኪሩቤልንም ፡ በውስጠኛው ፡ ቤት ፡ አኖራቸው ፤ የኪሩቤልም ፡ ክንፎቻቸው ፡ ተዘርግተው ፡ ነበር ፤ የአንዱም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ አንደኛውን ፡ ግንብ ፡ ይነካ ፡ ነበር ፥ የኹለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ኹለተኛውን ፡ ግንብ ፡ ይነካ ፡ ነበር ፤ የኹለቱም ፡ ክንፎች ፡ በቤቱ ፡ መካከል ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይነካኩ ፡ ነበር ።

28 ፤ ኪሩቤልንም ፡ በወርቅ ፡ ለበጣቸው ።

29 ፤ በቤቱም ፡ ግንብ ፡ ኹሉ ፡ ዙሪያ ፡ በውስጥና ፡ በውጭ ፡ የኪሩቤልና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የፈነዳም ፡ አበባ ፡ ምስል ፡ ቀረጸ ።

30 ፤ የቤቱንም ፡ ወለል ፡ በውስጥና ፡ በውጭ ፡ በወርቅ ፡ ለበጠ ።

31 ፤ ለቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ መግቢያ ፡ ከወይራ ፡ ዕንጨት ፡ ደጆች ፡ ሠራ ፤ መድረኩንና ፡ መቃኖቹን ፡ ደፉንም ፡ ዐምስት ፡ ማእዘን ፡ አደረገ ።

32 ፤ ኹለቱንም ፡ ደጆች ፡ ከወይራ ፡ ዕንጨት ፡ ሠራ ፤ የኪሩቤልንና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የፈነዳም ፡ አበባ ፡ ምስል ፡ ቀረጸባቸው ፥ በወርቅም ፡ ለበጣቸው ፤ ኪሩቤልናና ፡ የዘንባባውን ፡ ዛፍ ፡ በወርቅ ፡ ለበጣቸው ።

33 ፤ እንዲሁም ፡ ለመቅደሱ ፡ መግቢያ ፡ ከወይራ ፡ ዕንጨት ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ መቃን ፡ አደረገ ።

34 ፤ ኹለቱንም ፡ ደጆች ፡ ከጥድ ፡ ዕንጨት ፡ ሠራ ፤ አንዱ ፡ ደጅ ፡ በማጠፊያ ፡ ከተያያዘ ፡ ከኹለት ፡ ሳንቃ ፡ ተደረገ ፥ ኹለተኛውም ፡ ደጅ ፡ በማጠፊያ ፡ ከተያያዘ ፡ ከኹለት ፡ ሳንቃ ፡ ተደረገ ።

35 ፤ የኪሩቤልንና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የፈነዳም ፡ አበባ ፡ ምስል ፡ ቀረጸባቸው ፤ በተቀረጸውም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በወርቅ ፡ ለበጣቸው ።

36 ፤ የውስጠኛውንም ፡ አደባባይ ፡ ቅጥር ፡ ሦስቱን ፡ ተራ ፡ በተጠረበ ፡ ድንጋይ ፥ አንዱንም ፡ ተራ ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ሠራው ።

37 ፤ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ዚፍ ፡ በሚባል ፡ ወር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ተመሠረተ ።

38 ፤ በዐሥራ ፡ አንደኛውም ፡ ዓመት ፡ ቡል ፡ በሚባል ፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ ክፍሎቹና ፡ እንደ ፡ ሥርዐቱ ፡ ኹሉ ፡ ተጨረሰ ። በሰባትም ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሠራው ።

## ____________________መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 7 ።

1 ፤ ሰሎሞንም ፡ የራሱን ፡ ቤት ፡ በዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሠራ ፥ የቤቱንም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ጨረሰ ።

2 ፤ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ ቤት ፡ የሚባል ፡ ቤትን ፡ ሠራ ፤ ርዝመቱንም ፡ መቶ ፡ ክንድ ፥ ስፋቱንም ፡ ዐምሳ ፡
ክንድ ፥ ቁመቱንም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ አደረገ ፤ የዝግባም ፡ ዕንጨት ፡ በሦስት ፡ ተራ ፡ በተሠሩ ፡ አዕማድ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡
ነበር ፤ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ አግዳሚ ፡ ሠረገላዎች ፡ ነበሩ ።

3 ፤ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ በነበሩ ፡ አግዳሚዎች ፡ ቤቱ ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር ፤ አዕማዱም ፡ በአንዱ ፡ ተራ ፡
ዐሥራ ፡ ዐምስት ፥ በአንዱ ፡ ተራ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ እየኾኑ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ነበሩ ።

4 ፤ መስኮቶቹም ፡ በሦስት ፡ ተራ ፡ ነበሩ ፥ መስኮቶቹም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይተያዩ ፡ ነበር ።

5 ፤ ደጆቹና ፡ መስኮቶቹም ፡ ኹሉ ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ነበሩ ፤ መስኮቶቹም ፡ በሦስት ፡ ተራ ፡ ኾነው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
ይተያዩ ፡ ነበር ።

6 ፤ አዕማዱም ፡ ያሉበቱን ፡ ቤት ፡ ሠራ ፤ ርዝመቱም ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፥ ስፋቱም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ፊት ፡
ደግሞ ፡ አዕማድና ፡ መድረክ ፡ ያሉበት ፡ ወለል ፡ ነበረ ።

7 ፤ ደግሞም ፡ የሚፈርድበት ፡ ዙፋን ፡ ያለበትን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ አደረገ ። ከወለሉም ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ጣራው ፡
ድረስ ፡ በዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር ።

8 ፤ ከፍርድ ፡ ሰቀላ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፥ በሌላውም ፡ አደባባይ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲሁ ፡
ሠራ ። እንደዚሁም ፡ ያለ ፡ ቤት ፡ ሰሎሞን ፡ ላገባት ፡ ለፈርዖን ፡ ልጅ ፡ ቤት ፡ ሠራ ።

9 ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፡ ከመሠረቱ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ጕልላቱ ፡ ድረስ ፡ በጥሩ ፡ በተጠረበና ፡ በውስጥና ፡ በውጭ ፡ በልክ ፡
በተከረከመ ፡ ድንጋይ ፡ ተሠርተው ፡ ነበር ፤ በውጭውም ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ አደባባይ ፡ ድረስ ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ።

10 ፤ መሠረቱም ፡ ዐሥር ፡ ወይም ፡ስምንት ፡ ክንድ ፡ በኾነ ፡ በጥሩና ፡ በታላቅ ፡ ድንጋይ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ።

11 ፤ በላዩም ፡ ልክ ፡ ኾኖ ፡ የተከረከመ ፡ ጥሩ ፡ ድንጋይና ፡ የዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ነበረ ።

12 ፤ በታላቁም ፡ አደባባይ ፡ ዙሪያ ፡ የነበረው ፡ቅጥር ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ውስጠኛው ፡ አደባባይ ፡
ቅጥርና ፡ እንደ ፡ ቤቱ ፡ ወለል ፡ ሦስቱ ፡ ተራ ፡ በተጠረበ ፡ ድንጋይ ፡ አንዱም ፡ ተራ ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ።

13 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ልኮ ፡ ኪራምን ፡ ከጢሮስ ፡ አስመጣ ።

14 ፤ ርሱም ፡ ከንፍታሌም ፡ ወገን ፡ የነበረች ፡ የባል ፡ አልባ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ አባቱም ፡ የጢሮስ ፡ ሰው ፡ ናስ ፡
ሠራተኛ ፡ ነበረ ፤ የናስንም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ በጥበብና ፡ በማስተዋል ፡ በብልኀትም ፡ ተሞልቶ ፡
ነበር ። ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ መጥቶ ፡ ሥራውን ፡ ኹሉ ፡ ሠራ ።

15 ፤ ኹለቱን ፡ የናስ ፡ አዕማድ ፡ አደረገ ፤ የአንዱም ፡ ዐምድ ፡ ቁመት ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የዙሪያውም ፡
መጠን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ የዐምዱም ፡ ውፍረት ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ ነበረ ፥ ውስጠ ፡ ክፍትም ፡
ነበረ ። ኹለተኛውም ፡ ዐምድ ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ።

16 ፤ በኹለቱም ፡ አዕማድ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጡ ፡ ከፈሰሰ ፡ ናስ ፡ ኹለት ፡ ጕልላት ፡ ሠራ ፤ የአንዱም ፡ ጕልላት ፡
ቁመት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ የኹለተኛውም ፡ ጕልላት ፡ ቁመት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

17 ፤ በአዕማዱም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ጕልላቶች ፡ ይሸፍኑ ፡ ዘንድ ፡ ኹለት ፡ እንደ ፡ መርበብ ፡ ሥራ ፡
አደረገ ፤ አንዱም ፡ መርበብ ፡ ለአንዱ ፡ ጕልላት ፡ ኹለተኛውም ፡ መርበብ ፡ ለኹለተኛው ፡ ጕልላት ፡ ነበረ ።

18 ፤ ሮማኖችንም ፡ ሠራ ፤ ባንድ ፡ ጕልላት ፡ ዙሪያ ፡ በተራ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩ ፥ በአንድም ፡ መርበብ ፡
ላይ ፡ ኹለት ፡ ተራ ፡ ነበረ ፤ እንዲሁም ፡ ለኹለተኛው ፡ ጕልላት ፡ አደረገ ።

19 ፤ በወለሉም ፡ አዕማድ ፡ በነበሩት ፡ ጕልላቶች ፡ ላይ ፡ የሱፍ ፡ አበባ ፡ የሚመስል ፡ ሥራ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡
ቀረጸ ።

20 ፤ በኹለቱም ፡ አዕማድ ፡ በነበሩት ፡ ጕልላቶች ፡ ላይ ፡ በመርበቡ ፡ ሥራ ፡ አጠገብ ፡ ሮማኖቹን ፡ አደረገ ።

21 ፤ አዕማዱንም ፡ በመቅደሱ ፡ ወለል ፡ አጠገብ ፡ አቆማቸው ፤ የቀኙንም ፡ ዐምድ ፡ አቁሞ ፡ ያቁም ፡ ብሎ ፡
ጠራው ፤ የግራውንም ፡ ዐምድ ፡ አቁሞ ፡ በለዝ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

22 ፤ በአዕማዱም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የሱፍ ፡ አበባ ፡ የሚመስል ፡ ሥራ ፡ ነበረ ፤ እንዲሁም ፡ የአዕማዱ ፡ ሥራ ፡ ተጨረሰ ።

23 ፤ ከፈሰሰም ፡ ናስ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ በዙሪያውም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ክብ ፡ ኵሬ ፡ ሠራ ።

24 ፤ ከከንፈሩም ፡ በታች ፡ ላንድ ፡ ክንድ ፡ ዐሥር ፡ ላንድ ፡ ክንድም ፡ ዐሥር ፡ ጕብጕቦች ፡ አዞረበት ፤ ርሱም ፡ በቀለጠ ፡ ጊዜ ፡ ጕብጕቦቹ ፡ በኹለት ፡ ተራ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ቀልጠው ፡ ነበር ።

25 ፤ ኵሬውም ፡ በዐሥራ ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፡ ምስል ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ ከነርሱም ፡ ሦስቱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፥ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፥ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፥ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ። ኵሬውም ፡ በላያቸው ፡ ነበረ ፥ የኋላም ፡ ዠርባቸው ፡ በስተውስጥ ፡ ነበረ ።

26 ፤ ውፍረቱም ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ ነበረ ፤ ከንፈሩም ፡ እንደ ፡ ጽዋ ፡ ከንፈር ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ፤ እንደ ፡ ሱፍ ፡ አበባዎች ፡ ኾኖ ፡ ተከርክሞ ፡ ነበር ። ኹለት ፡ ሺሕም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ይይዝ ፡ ነበር ።

27 ፤ ዐሥርም ፡ የናስ ፡ መቀመጫዎች ፡ ሠራ ፤ የአንዱም ፡ መቀመጫ ፡ ርዝመት ፡ አራት ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ አራት ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

28 ፤ የመቀመጫውም ፡ ሥራ ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ፤ በክፈፎችም ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ሰንበር ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

29 ፤ በክፈፎቹም ፡ መካከል ፡ በነበሩ ፡ ሰንበሮች ፡ ላይ ፡ አንበሳዎችና ፡ በሬዎች ፡ ኪሩቤልም ፡ ነበሩ ፤ እንዲሁም ፡ በክፈፎቹ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤ ከአንበሳዎቹና ፡ ከበሬዎቹ ፡ በታች ፡ ሻኵራ ፡ የሚመስል ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ነበር ።

30 ፤ በየመቀመጫዎቹም ፡ ኹሉ ፡ አራት ፡ የናስ ፡ መንኰራኵሮች ፡ ነበሩባቸው ፤ መንኰራኵሮቹም ፡ የሚዞሩበትን ፡ የናስ ፡ ወስከምት ፡ ሠራ ፤ ከመታጠቢያውም ፡ ሰን ፡ በታች ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ በኩል ፡ አራት ፡ በምስል ፡ የፈሰሱ ፡ እግሮች ፡ ነበሩ ።

31 ፤ በክፈፉም ፡ ውስጥ ፡ የነበረ ፡ ዐንገት ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ዐንገቱም ፡ ድቡልቡል ፡ ነበረ ፥ ቁመቱም ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ነበረ ። በዐንገቱም ፡ ላይ ፡ ቅርጽ ፡ ነበረበት ፤ ክፈፉ ፡ ግን ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ድቡልቡል ፡ አልነበረም ።

32 ፤ አራቱም ፡ መንኰራኵሮች ፡ ከሰንበሮቹ ፡ በታች ፡ ነበሩ ፤ የመንኰራኵሮቹም ፡ ወስከምት ፡ በመቀመጫው ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ፤ የመንኰራኵሩም ፡ ቁመት ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ነበረ ።

33 ፤ የመንኰራኵሮቹም ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሠረገላ ፡ መንኰራኵር ፡ ነበረ ፥ ወስከምቶቹና ፡ የመንኰራኵሮቹ ፡ ክፈፍ ፡ ቅትርቶቹም ፡ ወስከምቱም ፡ የሚገባበት ፡ ቧምቧ ፡ ኹሉ ፡ በምስል ፡ የፈሰሰ ፡ ነበር ።

34 ፤ በያንዳንዱም ፡ መቀመጫ ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ደገፋዎች ፡ ነበሩ ፤ ደገፋዎቹም ፡ ከመቀመጫው ፡ ጋራ ፡ ተገጥመው ፡ ነበር ።

35 ፤ በመቀመጫውም ፡ ላይ ፡ ስንዝር ፡ የሚኾን ፡ ድቡልቡል ፡ ነገር ፡ ነበረ ፤ በመቀመጫውም ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ መያዣዎችና ፡ ሰንበሮች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይጋጠሙ ፡ ነበር ።

36 ፤ በመያዣውና ፡ በሰንበሮቹ ፡ ላይ ፡ ኪሩቤልንና ፡ አንበሳዎችን ፡ የዘንባባውንም ፡ ዛፍ ፡ እንደ ፡ መጠናቸው ፡ ቀረጸ ፥ በዙሪያውም ፡ ሻኵራ ፡ አደረገ ።

37 ፤ እንዲሁ ፡ ዐሥሩን ፡ መቀመጫዎች ፡ ሠራ ፤ ኹሉም ፡ በምስልና ፡ በመጠን ፡ በንድፍም ፡ ትክክሎች ፡ ነበሩ ።

38 ፤ ዐሥሩንም ፡ የናስ ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ ሠራ ፤ አንዱ ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ አርባ ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ያነሣ ፡ ነበር ፤ እያንዳንዱም ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ በዐሥሩም ፡ መቀመጫዎች ፡ ላይ ፡ በያንዳንዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ።

39 ፤ ዐምስቱንም ፡ መቀመጫዎች ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ፥ ዐምስቱንም ፡ በቤቱ ፡ ግራ ፡ አኖራቸው ፤ ኵሬውንም ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ፡ በአዜብ ፡ በኩል ፡ አኖረው ።

40 ፤ ኪራምም ፡ ምንቸቶችንና ፡ መጫሪያዎችን ፡ ድስቶችንም ፡ ሠራ ፤ ኪራምም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡

በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ጨረሰ ።

41 ፤ ኹለቱም ፡ አዕማድ ፥ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ኩብ ፡ የሚመስሉትን ፡ ጕልላቶች ፥ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ኹለቱን ፡ ጕልላቶች ፡ የሚሸፍኑትን ፡ ኹለቱን ፡ መርበቦች ፥

42 ፤ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ኹለቱን ፡ ጕልላቶች ፡ ይሸፍኑ ፡ ዘንድ ፡ ለያንዳንዱ ፡ መርበብ ፡ በኹለት ፡ በኹለት ፡ ተራ ፡ አድርጎ ፡ ለኹለቱ ፡ መርበቦች ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሮማኖች ፡ አደረገ ።

43 ፤ ዐሥሩንም ፡ መቀመጫዎች ፥ በመቀመጫዎችም ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡትን ፡ ዐሥሩን ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፥

44 ፤ አንዱንም ፡ ኵሬ ፥ ከኵሬውም ፡ በታች ፡ የሚኾኑትን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ በሬዎች ፥

45 ፤ ምንቸቶቹንም ፥ መጫሪያዎቹንም ፥ ድስቶቹንም ፡ አደረገ ። ኪራምም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራው ፡ ይህ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ የጋለ ፡ ናስ ፡ ነበረ ።

46 ፤ በዮርዳኖስ ፡ ሜዳ ፡ በሱኮትና ፡ በጸርታን ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ በወፍራሙ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ አስፈሰሰው ።

47 ፤ ሰሎሞንም ፡ ዕቃውን ፡ ኹሉ ፡ ሳያስመዝን ፡ አኖረ ፤ የናሱም ፡ ሚዛን ፡ ከብዛቱ ፡ የተነሣ ፡ አይቈጠርም ፡ ነበር ።

48 ፤ ሰሎሞንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ አሠራ ፤ የወርቁን ፡ መሠዊያ ፥ የገጹም ፡ ኅብስት ፡ የነበረበትን ፡ የወርቅ ፡ ገበታ ፥

49 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ፊት ፡ ዐምስቱ ፡ በቀኝ ፡ ዐምስቱም ፡ በግራ ፡ የሚቀመጡትን ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የተሠሩትንም ፡ መቅረዞች ፥ የወርቁንም ፡ አበባዎችና ፡ ቀንዲሎች ፡ መኰስተሪያዎችም ፥

50 ፤ ከጥሩ ፡ ወርቅም ፡ የተሠሩትን ፡ ጽዋዎችና ፡ ጕጠቶች ፥ ድስቶቹንና ፡
ጭልፋዎቹንም ፥ ማንደጃዎቹንም ፥ ለውስጠኛውም ፡ ቤት ፡ ለቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ደጆች ፡ ለቤተ ፡ መቅደሱም ፡ ደጆች ፡ የሚኾኑትን ፡ የወርቅ ፡ ማጠፊያዎች ፡ አሠራ ።

51 ፤ እንዲሁ ፡ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያሠራው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተፈጸመ ። አባቱም ፡ ዳዊት ፡ የቀደሰውን ፥ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ዕቃም ፥ ሰሎሞን ፡ አገባ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በነበሩ ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ አኖረው ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ምዕራፍ ፡ 8 ።

1 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከጽዮን ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ሽማግሌዎችና ፡ የነገድ ፡ አለቃዎችን ፡ ኹሉ ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ የአባቶቻቸውን ፡ ቤቶች ፡ መሳፍንት ፥ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰበሰባቸው ።

2 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኤታኒም ፡ በሚባል ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በበዓሉ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ተከማቹ ።

3 ፤ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ መጡ ፤ ካህናቱም ፡ ታቦቱን ፡ አነሡ ።

4 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፥ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ፥ በድንኳኑም ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ የተቀደሰውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ አመጡ ፤ እነዚህንም ፡ ኹሉ ፡ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑ ፡ አመጡ ።

5 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የተሰበሰቡ ፡ የእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ኾነው ፥ ከብዛታቸው ፡ የተነሣ ፡ የማይቈጠሩትንና ፡ የማይመጠኑትን ፡ በጎችና ፡ በሬዎች ፡ ይሠዉ ፡ ነበር ።

6 ፤ ካህናቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ በቤቱ ፡ በቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስጥ ፡ ከኪሩቤል ፡ ክንፍ ፡ በታች ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ አመጡት ።

7 ፤ ኪሩቤልም ፡ በታቦቱ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ነበር ፤ ኪሩቤልም ፡ ታቦቱንና ፡ መሎጊያዎቹን ፡ በስተላይ ፡ በኩል ፡ ሸፍነው ፡ ነበር ።

8 ፤ መሎጊያዎቹም ፡ ረጃጅሞች ፡ ነበሩ ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ፊት ፡ ከመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ጫፎቻቸው ፡ ይታዩ ፡
ነበር ፤ በውጭ ፡ ያለ ፡ ግን ፡ አያያቸውም ፡ ነበር ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ አሉ ።

9 ፤ በታቦቱም ፡ ውስጥ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፥ ሙሴ ፡ በኮሬብ ፡ ካስቀመጣቸው ፡ ከኹለቱ ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ በቀር ፡ ምንም ፡
አልነበረበትም ።

10 ፤ ካህናቱም ፡ ከመቅደሱ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ደመናው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞላው ።

11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞልቶ ፡ ነበርና ፥ ካህናቱ ፡ ከደመናው ፡ የተነሣ ፡ ለማገልገል ፡
ይቆሙ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

12 ፤ ሰሎሞንም ፦ እግዚአብሔር ፦ በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ እኖራለኹ ፡ ብሏል ፤

13 ፤ እኔም ፡ ለዘለዓለም ፡ የምትኖርበት ፡ ማደሪያ ፡ ቤት ፡ በእውነት ፡ ሠራኹልኽ ፡ አለ ።

14 ፤ ንጉሡም ፡ ፊቱን ፡ ዘወር ፡ አድርጎ ፡ የእስራኤልን ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ መረቀ ፤ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ ቆመው ፡
ነበር ።

15 ፤ 16 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ ካወጣኹበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ስሜ ፡ በዚያ ፡ ይኾን ፡
ዘንድ ፥ በርሷም ፡ ቤት ፡ ይሠራልኝ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ከተማ ፡ አልመረጥኹም ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ስሜ ፡
በዚያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ መርጫለኹ ፥ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡
መርጫለኹ ፡ ብሎ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ በአፉ ፡ የተናገረ ፥ በእጁም ፡ የፈጸመ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይመስገን ።

17 ፤ አባቴም ፡ ዳዊት ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ዐሰበ ።

18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አባቴን ፡ ዳዊትን ፦ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ በልብኽ ፡ ዐስበኻልና ፥ ይህን ፡ በልብኽ ፡
ማሰብኽ ፡ መልካም ፡ አደረግኽ ።

19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከወገብኽ ፡ የሚወጣው ፡ ልጅኽ ፡ ርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፡ እንጂ ፡ ቤት ፡ የምትሠራልኝ ፡
አንተ ፡ አይደለኽም ፡ አለው ።

20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አጸና ፤ እግዚአብሔርም ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፋንታ ፡
ተነሣኹ ፥ በእስራኤልም ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጥኹ ፥ ለእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ ሠራኹ ።

21 ፤ ከግብጽም ፡ ምድር ፡ ባወጣቸው ፡ ጊዜ ፡ ከአባቶቻችን ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላለበት ፡
ታቦት ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ አደረግኹለት ።

22 ፤ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ እያየ ፡ ሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ እጆቹን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡
ዘረጋ ።

23 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፥ በላይ ፡ በሰማይ ፡ በታችም ፡ በምድር ፡ አንተን ፡ የሚመስል ፡
አምላክ ፡ የለም ፤ በፍጹም ፡ ልባቸው ፡ በፊትኽ ፡ ለሚኼዱ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡ ምሕረትን ፡ የምትጠብቅ ፥

24 ፤ ለባሪያኽ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠኸውን ፡ ተስፋ ፡ የጠበቅኽ ፤ በአፍኽ ፡ ተናገርኽ ፥ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ቀንም ፡
በእጅኽ ፡ ፈጸምኸው ።

25 ፤ አኹንም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ። አንተ ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ ኼድኽ ፡ ልጆችኽ ፡ መንገዳቸውን ፡
ቢጠብቁ ፥ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ በፊቴ ፡ አታጣም ፡ ብለኽ ፡ ተስፋ ፡ የሰጠኸውን ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡
ጠብቅ ።

26 ፤ አኹንም ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ለባሪያኽ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ የተናገርኸው ፡ ቃል ፥ እባክኽ ፥ ይጽና ።

27 ፤ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይኖራልን ፥ እንሆ ፥ ሰማይ ፡ ከሰማያትም ፡ በላይ ፡ ያለው ፡
ሰማይ ፡ ይይዝኽ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ይልቁንስ ፡ እኔ ፡ የሠራኹት ፡ ቤት ፡ እንዴት ፡ ያንስ!

28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ወደባሪያኽ ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ተመልከት ፥ ዛሬም ፡ ባሪያኽ ፡ በፊትኽ ፡
የሚጸልየውን ፡ ጸሎትና ፡ ጥሪውን ፡ ስማ ፤

29 ፤ ባሪያኽ ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልየውን ፡ ጸሎት ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፦ በዚያ ፡ ስሜ ፡ ይኾናል ፡ ወዳልኸው ፡ ስፍራ ፡
ወደዚህ ፡ ቤት ፡ ዐይኖችኽ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ የተገለጡ ፡ ይኹኑ ።

30 ፤ ባሪያኽና ፡ ሕዝብኽ ፡ እስራኤል ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልዩትን ፡ ልመና ፡ ስማ ፤ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡
ስማ ፤ ሰምተኽም ፡ ይቅር ፡ በል ።

31 ፤ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፡ ቢበድል ፥ በላዩም ፡ መሐላ ፡ ቢጫን ፥ ርሱም ፡ መጥቶ ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ በመሠዊያኽ ፡ ፊት ፡
ቢምል ፥

32 ፤ በሰማይ ፡ ስማ ፡ አድርግም ፤ በባሪያዎችኽም ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ኹን ፤ በበደለኛውም ፡ ላይ ፡ ፍረድ ፥ መንገዱንም ፡
በራሱ ፡ ላይ ፡ መልስበት ፤ ንጹሑን ፡ አጽድቀው ፥ እንደ ፡ ጽድቁም ፡ ክፈለው ።

33 ፤ ሕዝብኽ ፡ እስራኤል ፡ አንተን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ ድል ፡ በተመቱ ፡ ጊዜ ፥ ወዳንተ ፡
ቢመለሱ ፥ ስምኽንም ፡ ቢያከብሩ ፥ በዚህም ፡ ቤት ፡ ቢጸልዩና ፡ ቢለምኑኽ ፥

34 ፤ አንተ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፤ የሕዝብኽንም ፡ የእስራኤልን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፥ ለአባቶቻቸውም ፡ ወደሰጠኻት ፡
ምድር ፡ መልሳቸው ።

35 ፤ አንተን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ ሰማይ ፡ በተዘጋ ፡ ጊዜ ፡ ዝናብም ፡ ባልዘነበ ፡ ጊዜ ፥ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ ቢጸልዩ ፥ ስምኽንም ፡
ቢያከብሩ ፥ ባስጨነቅኻቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከኀጢአታቸው ፡ ቢመለሱ ፥ አንተ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፤

36 ፤ የሚኼዱበትንም ፡ መልካም ፡ መንገድ ፡ በማሳየት ፡ የባሪያዎችኽንና ፡ የሕዝብኽን ፡ የእስራኤልን ፡ ኀጢአት ፡
ይቅር ፡ በል ፤ ለሕዝብኽም ፡ ርስት ፡ አድርገኽ ፡ ለሰጠኻት ፡ ምድር ፡ ዝናብ ፡ ስጥ ።

37 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ራብ ፥ ወይም ፡ ቸነፈር ፥ ወይም ፡ ዋግ ፥ ወይም ፡ ዐረማሞ ፥ ወይም ፡ አንበጣ ፥ ወይም ፡ ኩብኩባ ፡
ቢኾን ፥ የሕዝብኽም ፡ ጠላት ፡ የአገሩን ፡ ቀበሌዎች ፡ ከቦ ፡ ቢያስጨንቃቸው ፥ መቅሠፍትና ፡ ደዌ ፡ ዅሉ ፡ ቢኾን ፥

38 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የልቡን ፡ ሕመም ፡ ዐውቆ ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ቢጸልይ ፥ እጆቹንም ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ ቢዘረጋ ፥

39 ፤ 40 ፤ ለአባቶቻችን ፡ በሰጠኻት ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በሚኖሩበት ፡ ዘመን ፡ ዅሉ ፡ ይፈሩኽ ፡ ዘንድ ፡ በማደሪያኽ ፡
በሰማይ ፡ ስማ ፥ ይቅርም ፡ በል ፤ አንተ ፡ ብቻ ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ዅሉ ፡ ልብ ፡ ታውቃለኽና ፡ ልቡን ፡ ለምታውቀው ፡
ሰው ፡ ዅሉ ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ዅሉ ፡ መጠን ፡ ክፈለውና ፡ ስጠው ።

41 ፤ 42 ፤ ከሕዝብኽም ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ ያልኾነ ፡ እንግዳ ፡ ታላቁን ፡ ስምኽን ፥ ብርቱዪቱንም ፡
እጅኽን ፥ የተዘረጋውንም ፡ ክንድኽን ፡ ሰምቶ ፡ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ መጥቶም ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡
በጸለየ ፡ ጊዜ ፥

43 ፤ አንተ ፡ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፤ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ስምኽን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሕዝብኽም ፡
እንደ ፡ እስራኤል ፡ ይፈሩኽ ፡ ዘንድ ፥ በዚህም ፡ በሠራኹት ፡ ቤት ፡ ስምኽ ፡ አንደ ፡ ተጠራ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ እንግዳው ፡
የሚለምንኽን ፡ ዅሉ ፡ አድርግ ።

44 ፤ ሕዝብኽም ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ለመውጋት ፡ አንተ ፡ በምትልካቸው ፡ መንገድ ፡ ቢወጡ ፥ አንተም ፡ ወደመረጥኻት ፡
ከተማ ፡ እኔም ፡ ለስምኽ ፡ ወደሠራኹት ፡ ቤት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቢጸልዩ ፥

45 ፤ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥ ፍርድንም ፡ አድርግላቸው ።

46 ፤ የማይበድልም ፡ ሰው ፡ የለምና ፡ አንተን ፡ ቢበድሉ ፥ ተቈጥተኽም ፡ ለጠላቶቻቸው ፡ አሳልፈኽ ፡ ብትሰጣቸው ፡
ሩቅ ፡ ወይም ፡ ቅርብ ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ ወደጠላቶች ፡ አገር ፡ ቢማረኩም ፥

47 ፤ በተማረኩበትም ፡ አገር ፡ ኾነው ፡ በልባቸው ፡ ንስሓ ፡ ቢገቡ ፥ በማራኪዎቹም ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡
ተመልሰው ፦ ኀጢአት ፡ ሠርተናል ፥ በድለንማል ፥ ክፉንም ፡ አድርገናል ፡ ብለው ፡ ቢለምኑኽ ፥

48 ፤ በማረኳቸው ፡ በጠላቶቻቸው ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ በፍጹም ፡ ልባቸውና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሳቸው ፡ ወዳንተ ፡

ቢመለሱ ፥ ለአባቶቻቸው ፡ ወደሰጠኻት ፡ ወደ ፡ ምድራቸው ፡ ወደመረጥኻትም ፡ ከተማ ፡ ለስምኽም ፡ ወደሠራኹት ፡ ቤት ፡ ቢጸልዩ ፥

49 ፤ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥

50 ፤ ፍርድንም ፡ አድርግላቸው ፥ አንተንም ፡ የበደሉኽን ፡ ሕዝብኽን ፥ ባንተም ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ በደላቸውን ፡ ዅሉ ፡ ይቅር ፡ በል ፤ ይራሩላቸውም ፡ ዘንድ ፡ በማረኳቸው ፡ ፊት ፡ ምሕረት ፡ ስጣቸው ፤

51 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከብረት ፡ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ያወጣኻቸው ፡ ሕዝብኽና ፡ ርስትኽ ፡ ናቸውና ።

52 ፤ በጠሩኽ ፡ ጊዜ ፡ ዅሉ ፡ ትሰማቸው ፡ ዘንድ ፡ ለባሪያኽና ፡ ለሕዝብኽ ፡ ለእስራኤል ፡ ልመና ፡ ዐይኖችኽ ፡ የተገለጡ ፡ ይኹኑ ።

53 ፤ ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ አባቶቻችንን ፡ ከግብጽ ፡ ባወጣኽ ፡ ጊዜ ፡ በባሪያኽ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተናገርኽ ፡ ርስት ፡ ይኾኑኽ ፡ ዘንድ ፡ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ለይተኻቸዋልና ።

54 ፤ ሰሎሞንም ፡ ይህችን ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ዅሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸልዮ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ በጒልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፡ እጁንም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘርግቶ ፡ ነበርና ፥ ከእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ተነሣ ።

55 ፤ ቆሞም ፡ የእስራኤልን ፡ ጉባኤ ፡ ዅሉ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ሲመርቅ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

56 ፤ እንደተናገረው ፡ ተስፋ ፡ ዅሉ ፡ ለሕዝቡ ፡ ለእስራኤል ፡ ዕረፍትን ፡ የሰጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፤ በባሪያው ፡ በሙሴ ፡ ከሰጠው ፡ ከመልካም ፡ ተስፋ ፡ ዅሉ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አልወደቀም ።

57 ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአባቶቻችን ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ አይተወን ፥ አይጣለንም ፤

58 ፤ በመንገዱም ፡ ዅሉ ፡ እንኼድ ፡ ዘንድ ፥ ለአባቶቻችንም ፡ ያዘዛትን ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ትእዛዙንም ፡ እንጠብቅ ፡ ዘንድ ፥ ልባችንን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ያዘንብል ፡ ዘንድ ።

59 ፤ ለባሪያውና ፡ ለሕዝቡ ፡ ለእስራኤል ፡ በየዕለቱ ፡ ፍርድን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይህች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የለመንኺት ፡ ቃል ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቀረበች ፡ ትኹን ፤

60 ፤ የምድር ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ከርሱም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እንደሌለ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ።

61 ፤ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ቀን ፡ በሥርዐቱ ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፥ ትእዛዙንም ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፥ ከአምላካችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ልባችኹ ፡ ፍጹም ፡ ይኹን ።

62 ፤ ንጉሡም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ዅሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ።

63 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ በሬዎችና ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፡ አቀረበ ። ንጉሡና ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ዅሉ ፡ እንዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ቀደሱ ።

64 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ የናሱ ፡ መሠዊያ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ የደኅንነቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ ይይዝ ፡ ዘንድ ፡ ታናሽ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፥ በዚያ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ የደኅንነቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ አሳርጓልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ የነበረውን ፡ የአደባባዩ ፡ መካከል ፡ ንጉሡ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ቀደሰ ።

65 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ሰሎሞን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ዅሉ ፥ ከሐማት ፡ መግቢያ ፡ ዠምሮ ፡ እስከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፥ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓሉን ፡ አደረጉ ።

66 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ሕዝቡን ፡ አሰናበተ ፤ እነርሱም ፡ ንጉሡን ፡ መረቁ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ለባሪያው ፡ ለዳዊትና ፡ ለሕዝቡ ፡ ለእስራኤል ፡ ስላደረገው ፡ ቸርነት ፡ ዅሉ ፡ በልባቸው ፡ ተደስተው ፡ ሐሤትም ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ኼዱ ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ምዕራፍ ፡ 9 ።

1 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፥ የንጉሡን ፡ ቤትና ፡ ሰሎሞን ፡ የወደደውን ፡ የልቡን ፡ ዐሳብ ፡ ኹሉ ፡ ሠርቶ ፡
በፈጸመ ፡ ጊዜ ፥

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ በገባዖን ፡ ለሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ተገለጠለት ፡ ዳግመኛ ፡ ተገለጠለት ።

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፦ በፊቴ ፡ የጸለይኸውን ፡ ጸሎትኽንና ፡ ልመናኽን ፡ ሰምቻለኹ ፤ ለዘለዓለምም ፡ ስሜ ፡
በዚያ ፡ ያድር ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ የሠራኸውን ፡ ቤት ፡ ቀድሻለኹ ፤ ዐይኖቼና ፡ ልቤም ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ይኾናሉ ።

4 ፤ ዳዊትም ፡ አባትኽ ፡ በየዋህ ፡ ልብና ፡ በቅንነት ፡ እንደ ፡ ኼደ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ በፊቴ ፡ ብትኼድ ፥ ያዘዝኹኽንም ፡
ኹሉ ፡ ብታደርግ ፥ ሥርዐቴንም ፡ ፍርዴንም ፡ ብትጠብቅ ፥

5 ፤ እኔ ፦ ከእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ከዘርኽ ፡ ሰው ፡ አታጣም ፡ ብዬ ፡ ለአባትኽ ፡ ለዳዊት ፡ እንደ ፡
ተናገርኹ ፥ የመንግሥትኽን ፡ ዙፋን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ አጸናለኹ ።

6 ፤ እናንተና ፡ ልጆቻችኹ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ከመከተል ፡ ብትመለሱ ፥ የሰጠኇችኹንም ፡ ትእዛዜንና ፡ ሥርዐቴን ፡
ባትጠብቁ ፥ ኼዳችኹም ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ብታመልኩ ፥ ብትሰግዱላቸውም ፥

7 ፤ እስራኤልን ፡ ከሰጠኇቸው ፡ ምድር ፡ አጠፋቸዋለኹ ፤ ለስሜም ፡ የቀደስኹትን ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ ከፊቴ ፡
እጥለዋለኹ ፤ እስራኤልም ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ምሳሌና ፡ ተረት ፡ ይኾናሉ ።

8 ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የነበረውም ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ ባድማ ፡ ይኾናል ፤ በዚያም ፡ የሚያልፍ ፡ ኹሉ ፡
እያፏጨ ፦ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ አገርና ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ፧ ብሎ ፡ ይደነቃል ።

9 ፤ መልሰውም ፦ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አባቶቻቸውን ፡ ያወጣውን ፡ አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡
ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ ስለ ፡ ተከተሉ ፥ ስለ ፡ ሰገዱላቸውም ፥ ስለ ፡ አመለኳቸውም ፥ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡
ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አመጣባቸው ፡ ይላሉ ።

10 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ ኹለቱን ፡ ቤቶች ፡ የሠራበት ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡
ጊዜ ፥

11 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ በገሊላ ፡ ምድር ፡ ያሉትን ፡ ኻያ ፡ ከተማዎች ፡ ለኪራም ፡ ሰጠው ። የጢሮስም ፡ ንጉሥ ፡ ኪራም ፡
የሚሻውን ፡ ያኽል ፡ የዝግባና ፡ የጥድ ፡ ዕንጨት ፡ የሚሻውንም ፡ ያኽል ፡ ወርቅ ፡ ኹሉ ፡ ለሰሎሞን ፡ ሰጥቶት ፡ ነበር ።

12 ፤ ኪራምም ፡ ሰሎሞን ፡ የሰጠውን ፡ ከተማዎች ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ከጢሮስ ፡ ወጣ ፤ ደስም ፡ አላሠኙትም ።

13 ፤ ርሱም ፦ ወንድሜ ፡ ሆይ ፥ የሰጠኸኝ ፡ እነዚህ ፡ ከተማዎች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አለ ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡
የከቡል ፡ አገር ፡ ተብለው ፡ ተጠሩ ።

14 ፤ ኪራምም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ለንጉሡ ፡ ላከ ።

15 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የራሱን ፡ ቤት ፥ ሚሎንም ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡
ቅጥር ፥ ሐጾርንም ፥ መጊዶንም ፥ ጌዝርንም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ገባሮችን ፡ መልምሎ ፡ ነበር ።

16 ፤ የግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ወጥቶ ፡ ጌዝርን ፡ ይዞ ፡ ነበር ፥ በእሳትም ፡ አቃጥሎ ፡ ነበር ፥ በከተማም ፡ የኖሩትን ፡
ከነዓናውያን ፡ ገድሎ ፡ ነበር ፤ ለልጁም ፡ ለሰሎሞን ፡ ሚስት ፡ ትሎት ፡ አድርጎ ፡ ሰጥቷት ፡ ነበር ።

17 ፤ ሰሎሞንም ፡ ጌዝርን ፥ የታችኛውንም ፡ ቤት ፡

18 ፤ ሖሮን ፥ ባዕላትንም ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡ አገር ፡ ያለችውን ፡ ተድሞርን ፥

19 ፤ ለሰሎሞንም ፡ የነበሩትን ፡ የዕቃ ፡ ቤት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ የሠረገላውንም ፡ ከተማዎች ፥ የፈረሰኞዎችንም ፡
ከተማዎች ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ በሊባኖስም ፡ በመንግሥቱም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ሰሎሞን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የወደደውን ፡
ኹሉ ፡ ሠራ ።

20 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ያልነበሩትን ፡ ከአሞራውያንና ፡ ከኬጢያውያን ፥ ከፌርዛውያን ፥ ከዔዊያውያንና ፡
ከኢያቡሳውያን ፡ የቀሩትን ፥

21 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ያጠፏቸው ፡ ዘንድ ፡ ያልቻሉትን ፥ በኋላቸው ፡ የቀሩትን ፡ ልጆቻቸውን ፥ ሰሎሞን ፡ እስከ ፡

ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ገባሮች ፡ አድርጎ ፡ መለመላቸው ።

22 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማንንም ፡ ባሪያ ፡ አላደረገም ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡
ሰልፈኞዎች ፥ ሎሌዎችም ፥ መሳፍንትም ፥ አለቃዎችም ፥ የሠረገላዎችና ፡ የፈረሶች ፡ ባልደራሶች ፡ ነበሩ ።

23 ፤ ሰሎሞንም ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሠራተኛውን ፡ ሕዝብ ፡ የሚያዙ ፡ አለቃዎች ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡
ነበሩ ።

24 ፤ የፈርዖንም ፡ ልጅ ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ ሰሎሞን ፡ ወደሠራላት ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ወጣች ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሚሎን ፡
ሠራ ።

25 ፤ ሰሎሞንም ፡ በየዓመቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ የሚቃጠለውንና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሠራው ፡
መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ያሳርግ ፡ ነበር ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ዕጣን ፡ ያሳርግ ፡ ነበር ፤ ቤቱንም ፡
ጨረሰ ።

26 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ በኤሎት ፡ አጠገብ ፡ ባለችው ፡ በዔጽዮንጋብር ፡
መርከቦችን ፡ ሠራ ።

27 ፤ ኪራምም ፡ በእነዚያ ፡ መርከቦች ፡ ከሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ ጋራ ፡ የባሕሩን ፡ ነገር ፡ የሚያውቁ ፡ መርከበኞዎች ፡
ባሪያዎቹን ፡ ሰደደ ።

28 ፤ ወደ ፡ ኦፊርም ፡ መጡ ፥ ከዚያም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ወሰዱ ፥ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡
ሰሎሞን ፡ ይዘው ፡ መጡ ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ምዕራፍ ፡ 10 ።

1 ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የወጣለትን ፡ የሰሎሞንን ፡ ዝና ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ በእንቆቅልሽ ፡
ትፈትነው ፡ ዘንድ ፡ መጣች ።

2 ፤ በግመሎችም ፡ ላይ ፡ ሽቱና ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ የከበረም ፡ ዕንቍ ፡ አስጭና ፡ ከታላቅ ፡ ጓዝ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ገባች ፤ ወደ ፡ ሰሎሞንም ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡ በልቧ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ አጫወተችው ።

3 ፤ ሰሎሞንም ፡ የጠየቀችውን ፡ ኹሉ ፡ ፈታላት ፤ ሊፈታላት ፡ ያልቻለውና ፡ ከንጉሡ ፡ የተሰወረ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ።

4 ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ኹሉ ፥ ሠርቶትም ፡ የነበረውን ፡ ቤት ፥

5 ፤ የማእዱንም ፡ መብል ፥ የብላቴናዎቹንም ፡ አቀማመጥ ፥ የሎሌዎቹንም ፡ አሠራር ፡ አለባበሳቸውንም ፥ ጠጅ ፡
አሳላፊዎቹንም ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የሚያሳርገውን ፡ መሥዋዕት ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ አልቀረላትም ።

6 ፤ ንጉሡንም ፡ አለችው ፦ ስለ ፡ ነገርኽና ፡ ስለ ፡ ጥበብኽ ፡ በአገሬ ፡ ሳለኹ ፡ የሰማኹት ፡ ዝና ፡ እውነት ፡ ነው ።

7 ፤ እኔም ፡ መጥቼ ፡ በዐይኔ ፡ እስካይ ፡ ድረስ ፡ የነገሩኝን ፡ አላመንኹም ፡ ነበር ፤ እንሆም ፥ እኩሌታውን ፡ አልነገሩኝም ፡
ነበር ፤ ጥበብኽና ፡ ሥራኽ ፡ ከሰማኹት ፡ ዝና ፡ ይበልጣል ።

8 ፤ በፊትኽ ፡ ኹልጊዜ ፡ የሚቆሙ ፡ ጥበብኽንም ፡ የሚሰሙ ፡ ሰዎችኽና ፡ እነዚህ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ።

9 ፤ አንተን ፡ የወደደ ፥ በእስራኤልም ፡ ዙፋን ፡ ያስቀመጠኽ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባረከ ፡
ይኹን ፤ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ለዘለዓለም ፡ ወዶታልና ፥ ስለዚህ ፡ ጽድቅና ፡ ፍርድ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡
አድርጎ ፡ አስነሣኽ ።

10 ፤ ለንጉሡም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፥ እጅግም ፡ ብዙ ፡ ሽቱ ፥ የከበረም ፡ ዕንቍ ፡ ሰጠችው ፤ የሳባ ፡
ንግሥት ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ሰጠችው ፡ ያለ ፡ የሽቱ ፡ ብዛት ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ አልመጣም ፡ ነበር ።

11 ፤ ከኦፊርም ፡ ወርቅ ፡ ያመጡ ፡ የኪራም ፡ መርከቦች ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሰንደል ፡ ዕንጨትና ፡ የከበረ ፡ ዕንቍ ፡ ከኦፊር ፡
አመጡ ።

12 ፤ ንጉሡም ፡ ከሰንደሉ ፡ ዕንጨት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ ለንጉሡ ፡ ቤት ፡ መከታ ፥ ለመዘምራኑም ፡ መሰንቆና ፡
በገና ፡ አደረገ ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ የሰንደል ፡ ዕንጨት ፡ ከቶ ፡ አልመጣም ፡ አልታየምም ።

13 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፥ በገዛ ፡ እጁ ፡ ከሰጣት ፡ ሌላ ፥ የወደደችውን ፡ ኹሉ ፡ ከርሱም ፡ የለመነችውን ፡ ኹሉ ፡ ለሳባ ፡
ንግሥት ፡ ሰጣት ፤ ርሷም ፡ ተመልሳ ፡ ከባሪያዎቿ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ምድሯ ፡ ኼደች ።

14 ፤ 15 ፤ ግብርም ፡ የሚያስገብሩ ፡ ሰዎች ፡ ነጋዴዎችም ፡ የዐረብም ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ የምድርም ፡ ሹማምት ፡
ከሚያወጡት ፡ ሌላ ፥ በየዓመቱ ፡ ለሰሎሞን ፡ የሚመጣለት ፡ የወርቅ ፡ ሚዛን ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡
መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ።

16 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከጥፍጥፍ ፡ ወርቅ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻ ፡ አሠራ ፤ በአንዱም ፡ አላባሽ ፡
አግሬ ፡ ጋሻ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ ወርቅ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።

17 ፤ ከጥፍጥፍም ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ጋሻ ፡ አሠራ ፤ በአንዱም ፡ ጋሻ ፡ የገባው ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ ምናን ፡
ነበረ ፤ ንጉሡም ፡ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ በተባለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ።

18 ፤ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ ከዝኆን ፡ ጥርስ ፡ ታላቅ ፡ ዙፋን ፡ አሠራ ፥ በጥሩም ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ።

19 ፤ ወደ ፡ ዙፋንም ፡ የሚያስኼዱ ፡ ስድስት ፡ ዕርከኖች ፡ ነበሩ ፤ በስተኋላውም ፡ ያለው ፡ የዙፋኑ ፡ ራስ ፡ ክብ ፡
ነበረ ፤ በዚህና ፡ በዚያ ፡ በመቀመጫው ፡ አጠገብ ፡ ኹለት ፡ የክንድ ፡ መደገፊያዎች ፡ ነበሩበት ፥ በመደገፊያዎቹም ፡
አጠገብ ፡ ኹለት ፡ አንበሳዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

20 ፤ በስድስቱም ፡ ዕርከኖች ፡ ላይ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ አንበሳዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ በመንግሥታት ፡
ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ አልተሠራም ።

21 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የሚጠጣበት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ፥ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ የተባለውም ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡
ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ እንጂ ፡ ብር ፡ አልነበረም ። በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ብር ፡ ከቶ ፡ አይቈጠርም ፡ ነበር ።

22 ፤ ለንጉሡም ፡ ከኪራም ፡ መርከቦች ፡ ጋራ ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ነበሩት ፤ በሦስት ፡ በሦስት ፡ ዓመትም ፡ አንድ ፡
ጊዜ ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ወርቅና ፡ ብር ፥ የዝኆንም ፡ ጥርስ ፥ ዝንጀሮና ፡ ዝንጕርጕር ፡ ወፍ ፡ ይዘው ፡ ይመጡ ፡
ነበር ።

23 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በባለጠግነትና ፡ በጥበብ ፡ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ በልጦ ፡ ነበር ።

24 ፤ ምድርም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልቡ ፡ ያኖረለትን ፡ ጥበቡን ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ የሰሎሞንን ፡ ፊት ፡ ይመኝ ፡
ነበር ።

25 ፤ ከነርሱም ፡ እያንዳንዱ ፡ በዓመቱ ፡ በዓመቱ ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ፥ የብርና ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፥ ልብስና ፡ የጦር ፡
መሣሪያ ፥ ሽቱም ፥ ፈረሶችና ፡ በቅሎዎች ፡ እየያዘ ፡ ይመጣ ፡ ነበር ።

26 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሠረገላዎችንና ፡ ፈረሰኛዎችን ፡ ሰበሰበ ፤ አንድ ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሠረገላዎች ፥ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡
ሺሕም ፡ ፈረሰኛዎች ፡ ነበሩት ፥ በሠረገላዎችም ፡ ከተማዎች ፡ ከንጉሡም ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኖራቸው ።

27 ፤ ንጉሡም ፡ ብሩን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ እንዲበዛ ፡ አደረገው ፤ የዝግባም ፡ ዕንጨት ፡ ብዛት ፡ በቈላ ፡
እንደሚበቅል ፡ ሾላ ፡ ኾነ ።

28 ፤ ሰሎሞንም ፡ ፈረሶችን ፡ ከግብጽና ፡ ከቀዌ ፡ አገር ፡ አስመጣ ፤ የንጉሡም ፡ ነጋዴዎች ፡ በገንዘብ ፡ እየገዙ ፡ ከቀዌ ፡
ያመጧቸው ፡ ነበር ።

29 ፤ አንዱም ፡ ሠረገላ ፡ በስድስት ፡ መቶ ፥ አንዱም ፡ ፈረስ ፡ በመቶ ፡ ዐምሳ ፡ ብር ፡ ከግብጽ ፡ ይወጣ ፡
ነበር ። እንዲሁም ፡ ለኬጢያውያንና ፡ ለሶርያ ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ በእጃቸው ፡ ያወጡላቸው ፡ ነበር ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ምዕራፍ ፡ 11 ።

1 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከፈርዖን ፡ ልጅ ፡ ሌላ ፥ በሞዐባውያንና ፡ በአሞናውያን ፡ በኤዶማውያን ፡ በሲዶናውያንና ፡

በኬጢያውያን ፡ ሴቶች ፥ በብዙ ፡ እንግዳዎች ፡ ሴቶች ፡ ፍቅር ፡ ተነደፈ ።

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ። አምላኮቻቸውን ፡ ትከተሉ ፡ ዘንድ ፡ ልባችኹን ፡ በእውነት ፡ ያዘነብላሉና ፡
ወደ ፡ እነርሱ ፡ አትግቡ ፥ እነርሱም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ አይግቡ ፡ ካላቸው ፡ ከአሕዛብ ፥ ከነዚህ ፡ ጋራ ፡ ሰሎሞን ፡ በፍቅር ፡
ተጣበቀ ።

3 ፤ ለርሱም ፡ ወይዛዝር ፡ የኾኑ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሚስቶች ፡ ሦስት ፡ መቶም ፡ ቁባቶች ፡ ነበሩት ፤ ሚስቶቹም ፡ ልቡን ፡
አዘነበሉት ።

4 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሲሸመግል ፡ ሚስቶቹ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ይከተል ፡ ዘንድ ፡ ልቡን ፡ አዘነበሉት ፤ የአባቱ ፡ የዳዊት ፡
ልብ ፡ ከአምላኩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ፍጹም ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሰሎሞን ፡ ልቡ ፡ እንዲሁ ፡ አልነበረም ።

5 ፤ ሰሎሞንም ፡ የሲዶናውያንን ፡ አምላክ ፡ ዐስታሮትን ፥ የአሞናውያንንም ፡ ርኵሰት ፡ ሚልኮምን ፥ ተከተለ ።

6 ፤ ሰሎሞንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አደረገ ፥ እንደ ፡ አባቱም ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብሔርን ፡
በመከተል ፡ ፍጹም ፡ አልኾነም ።

7 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰሎሞን ፡ ለሞዐብ ፡ ርኵሰት ፡ ለካሞሽ ፥ ለዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ርኵሰት ፡ ለሞሎክ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ መስገጃ ፡ ሠራ ።

8 ፤ ለአማልክታቸው ፡ ዕጣን ፡ ለሚያጥኑ ፡ መሥዋዕትም ፡ ለሚሠዉ ፡ ለእንግዳዎች ፡ ሚስቶቹ ፡ ዅሉ ፡ እንዲሁ ፡
አደረገ ።

9 ፤ 10 ፤ ኹለት ፡ ጊዜም ፡ ከተገለጠለት ፥ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ እንዳይከተል ፡ ካዘዘው ፡ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ልቡን ፡ አርቋልና ፥ እግዚአብሔርም ፡ ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ አልጠበቀምና ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰሎሞንን ፡
ተቈጣ ።

11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰሎሞንን ፡ አለው ፦ ይህን ፡ ሠርተኻልና ፥ ያዘዝኹኽንም ፡ ቃል ፡ ኪዳኔንና ፡ ሥርዐቴን ፡
አልጠበቅኽምና ፡ መንግሥትኽን ፡ ከአንተ ፡ ቀዳድጄ ፡ ለባሪያኽ ፡ እሰጠዋለኹ ።

12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከልጅኽ ፡ እጅ ፡ እቀድዋለኹ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ አባትኽ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ይህን ፡ በዘመንኽ ፡ አላደርግም ።

13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ዳዊትና ፡ ስለመረጥኋት ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለልጅኽ ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡
እሰጣለኹ ፡ እንጂ ፡ መንግሥቱን ፡ ዅሉ ፡ አልቀድም ።

14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከኤዶምያስ ፡ ነገሥታት ፡ ዘር ፡ የኤዶምያስን ፡ ሰው ፡ ሃዳድን ፡ ጠላት ፡ አድርጎ ፡ በሰሎሞን ፡ ላይ ፡
አስነሣው ።

15 ፤ 16 ፤ ኢዮአብና ፡ እስራኤልም ፡ ዅሉ ፡ የኤዶምያስን ፡ ወንድ ፡ ዅሉ ፡ እስኪገድሉ ፡ ድረስ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በዚያ ፡
ተቀምጠው ፡ ነበርና ፥ ዳዊት ፡ በኤዶምያስ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፥ የሰራዊቱም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብ ፡ ተወግተው ፡ የሞቱትን ፡
ሊቀብር ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፥ የኤዶምያስንም ፡ ወንድ ፡ ዅሉ ፡ በገደለ ፡ ጊዜ ፥

17 ፤ ሃዳድ ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ሳለ ፡ ሃዳድና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ከኤዶምያስ ፡ ሰዎች ፡ የኾኑ ፡ የአባቱ ፡ ባሪያዎች ፡
ወደ ፡ ግብጽ ፡ ኰብልለው ፡ ነበር ።

18 ፤ ከምድያምም ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ፋራን ፡ መጡ ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ከፋራን ፡ ሰዎች ፡ ወሰዱ ፥ ወደ ፡ ግብጽም ፡
መጡ ፥ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ገቡ ፤ ርሱም ፡ ቤት ፡ ሰጥቶ ፡ ቀለብ ፡ ዳረገው ፥ ምድርም ፡
ሰጠው ።

19 ፤ የሚስቱንም ፡ የእቴጌዪቱን ፡ የቴቄምናስን ፡ እኅት ፡ እስኪያጋባው ፡ ድረስ ፡ ሃዳድ ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡
ባለሟል ፡ ኾነ ።

20 ፤ የቴቄምናስ ፡ እኅት ፡ ጌንባትን ፡ ወለደችለት ፥ ቴቄምናስም ፡ በፈርዖን ፡ ቤት ፡ አሳደገችው ፤ ጌንባትም ፡ በፈርዖን ፡
ቤት ፡ በፈርዖን ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ነበረ ።

21 ፤ ሃዳድም ፡ በግብጽ ፡ ሳለ ፡ ዳዊት ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ እንዳንቀላፋ ፥ የሰራዊቱም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡

በሰማ ፡ ጊዜ ፣ ሃዳድ ፡ ፈርዖንን ፦ ወደ ፡ አገሬ ፡ እኼድ ፡ ዘንድ ፡ አሰናብተኝ ፡ አለው ።

22 ፤ ፈርዖንም ፦ እንሆ ፣ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አገርኽ ፡ መኼድ ፡ የፈለግኽ ፡ ምን ፡ ዐጥተኽ ፡
ነው ፧ አለው ። ርሱም ፦ አንዳች ፡ አላጣኹም ፤ ነገር ፡ ግን ፣ ልኺድ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ሃዳድም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡
ተመለሰ ፣ ሃዳድም ፡ ያደረገው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እስራኤልን ፡ አስጨነቀ ፣ በኤዶምያስም ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ከጌታው ፡ ከሱባ ፡ ንጉሥ ፡ ከአድርዐዛር ፡ የኰበለለውን ፡ የኤልያዳን ፡ ልጅ ፡ ሬዞንን ፡
ጠላት ፡ አድርጎ ፡ አስነሣበት ።

24 ፤ ዳዊትም ፡ የሱባን ፡ ሰዎች ፡ በገደለ ፡ ጊዜ ፡ ሬዞን ፡ ሰዎችን ፡ ሰብስቦ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃ ፡ ኾነ ፤ ወደ ፡ ደማስቆም ፡
ኼዱ ፣ በዚያም ፡ ተቀመጡ ፤ በደማስቆም ፡ ላይ ፡ አነገሡት ።

25 ፤ ሃዳድም ፡ ካደረገው ፡ ክፋት ፡ ሌላ ፡ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ የእስራኤል ፡ ጠላት ፡ ነበረ ።

26 ፤ ከሳሪራ ፡ አገር ፡ የኾነ ፡ የሰሎሞን ፡ ባሪያ ፡ የኤፍሬማዊው ፡ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡
ዐመፀ ፤ እናቱም ፡ ጽሩዓ ፡ የተባለች ፡ ባልቴት ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

27 ፤ በንጉሡም ፡ ያመፀበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሰሎሞን ፡ ሚሎን ፡ ሠራ ፣ የአባቱንም ፡ የዳዊትን ፡ ከተማ ፡
ሰባራውን ፡ ጠገነ ።

28 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ጽኑዕ ፡ ኀያል ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ሰሎሞንም ፡ ጕልማሳው ፡ በሥራ ፡ የተመሰገነ ፡ መኾኑን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡
በዮሴፍ ፡ ነገድ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሾመው ።

29 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኢዮርብዓም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ሴሎናዊው ፡ ነቢዩ ፡ አኪያ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡
ተገናኘው ፤ አኪያም ፡ ዐዲስ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ነበር ፡ ኹለቱም ፡ በሜዳው ፡ ለብቻቸው ፡ ነበሩ ።

30 ፤ አኪያም ፡ የለበሰውን ፡ ዐዲስ ፡ ልብስ ፡ ይዞ ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ቈራረጠው ።

31 ፤ ኢዮርብዓምንም ፡ አለው ፦ ዐሥር ፡ ቍራጭ ፡ ውሰድ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላልና ፦ እንሆ ፣ ከሰሎሞን ፡ እጅ ፡ መንግሥቱን ፡ እቀዳለኹ ፣ ዐሥሩንም ፡ ነገዶች ፡ እሰጥኻለኹ ፤

32 ፤ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ስለመረጥኋት ፡ ከተማ ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ግን ፡ አንድ ፡
ነገድ ፡ ይቀርለታል ፤

33 ፤ ጥለውኛልና ፣ ለሲዶናውያንም ፡ አምላክ ፡ ለዐስታሮት ፣ ለሞዐብም ፡ አምላክ ፡ ለካሞሽ ፣ ለዐሞንም ፡ ልጆች ፡
አምላክ ፡ ለሚልኮም ፡ ሰግደዋልና ፣ አባቱም ፡ ዳዊት ፡ እንዳደረገ ፡ በፊቴ ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፣ ሥርዐቴንና ፡
ፍርዴንም ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ በመንገዴ ፡ አልኼዱምና ።

34 ፤ መንግሥቱንም ፡ ኹሉ ፡ ከእጁ ፡ አልወስድም ፤ ትእዛዜንና ፡ ሥርዐቴን ፡ ስለጠበቀው ፡ ስለመረጥኹት ፡ ስለ ፡
ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ግን ፡ በዕድሜው ፡ ኹሉ ፡ አለቃ ፡ አደርገዋለኹ ።

35 ፤ መንግሥቱንም ፡ ከልጁ ፡ እጅ ፡ እወስዳለኹ ፣ ለአንተም ፡ ዐሥሩን ፡ ነገድ ፡ እሰጥኻለኹ ።

36 ፤ ስሜንም ፡ ባኖርኹባት ፡ በዚያች ፡ በመረጥኋት ፡ ከተማ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለባሪያዬ ፡ ለዳዊት ፡ በፊቴ ፡ ኹልጊዜ ፡
መብራት ፡ ይኾንለት ፡ ዘንድ ፡ ለልጁ ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ እሰጠዋለኹ ።

37 ፤ አንተንም ፡ እወስድኻለኹ ፣ ነፍስኽም ፡ በወደደችው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ትነግሣለች ፣ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡
ትኾናለኽ ።

38 ፤ ባሪያዬም ፡ ዳዊት ፡ እንዳደረገ ፣ ያዘዝኹኽን ፡ ኹሉ ፡ ብትሰማ ፣ በመንገዴም ፡ ብትኼድ ፣ በፊቴም ፡ የቀናውን ፡
ብታደርግ ፣ ሥርዐቴንና ፡ ትእዛዜን ፡ ብትጠብቅ ፣ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፣ ለዳዊትም ፡ እንደ ፡ ሠራኹለት ፡ ጽኑ ፡
ቤት ፡ እሠራልኻለኹ ፣ እስራኤልንም ፡ ለአንተ ፡ እሰጥኻለኹ ።

39 ፤ ስለዚህም ፡ የዳዊትን ፡ ዘር ፡ አስጨንቃለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፣ በዘመን ፡ ኹሉ ፡ አይደለም ።

40 ፤ ሰሎሞንም ፡ ኢዮርብዓምን ፡ ሊገድለው ፡ ወደደ ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡
ኰበለለ ፣ ወደግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሺሻቅ ፡ መጣ ፣ ሰሎሞንም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በግብጽ ፡ ተቀመጠ ።

41 ፤ የቀረውም ፡ የሰሎሞን ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ ጥበቡም ፥ እንሆ ፥ በሰሎሞን ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

42 ፤ ሰሎሞንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ።

43 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ሮብዓም ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ምዕራፍ ፡ 12 ።

1 ፤ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፥ ሮብዓም ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ ኼደ ።

2 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ ርሱም ፡ ከንጉሡ ፡ ከሰሎሞን ፡ ፊት ፡ ኰብሎ ፡
በግብጽ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበርና ፥ በግብጽም ፡ ሳለ ፡ ልከው ፡ ጠርተውት ፡ ነበርና ፥

3 ፤ ኢዮርብዓምና ፡ የእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ መጥተው ፡ ለሮብዓም ።

4 ፤ አባትኽ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶብን ፡ ነበር ፤ አኹንም ፡ አንተ ፡ ጽኑውን ፡ የአባትኽን ፡ አገዛዝ ፥ በላያችንም ፡ የጫነውን ፡
የከበደውን ፡ ቀንበር ፡ አቃልልን ፤ እኛም ፡ እንገዛልኻለን ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

5 ፤ ርሱም ፦ ኺዱ ፥ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፡ አላቸው ። ሕዝቡም ፡ ኼዱ ።

6 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፦ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ እመልስለት ፡ ዘንድ ፡ የምትመክሩኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ አባቱ ፡
ሰሎሞን ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ከነበሩት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ።

7 ፤ እነርሱም ፦ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አኹን ፡ ባሪያ ፡ ብትኾን ፡ ብትገዛላቸውም ፥ መልሰኽም ፡ በገርነት ፡
ብትናገራቸው ፥ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ባሪያዎች ፡ ይኾኑልኻል ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

8 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ሽማግሌዎች ፡ የመከሩትን ፡ ምክር ፡ ትቶ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካደጉትና ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ከነበሩት ፡
ብላቴናዎች ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ።

9 ፤ ርሱም ፦ አባትኽ ፡ የጫኑብንን ፡ ቀንበር ፡ አቃልልን ፡ ለሚሉኝ ፡ ሕዝብ ፡ እመልስላቸው ፡ ዘንድ ፡ የምትመክሩኝ ፡
ምንድር ፡ ነው ፧ አላቸው ።

10 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያደጉት ፡ ብላቴናዎች ፦ አባትኽ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶብናል ፥ አንተ ፡ ግን ፡ አቃልልን ፡ ለሚሉኽ ፡
ሕዝብ ። ታናሺቱ ፡ ጣቴ ፡ ከአባቴ ፡ ወገብ ፡ ትወፍራለች ።

11 ፤ አኹንም ፡ አባቴ ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ጭኖባችኊል ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በቀንበራችኹ ፡ ላይ ፡ እጨምራለኹ ፤ አባቴ ፡
በዐለንጋ ፡ ገርፏችኊል ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በጊንጥ ፡ እገርፋችኊለኹ ፡ በላቸው ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

12 ፤ ንጉሡም ፦ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ኢዮርብዓምና ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡
በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ መጡ ።

13 ፤ ንጉሡም ፡ ሽማግሌዎች ፡ የመከሩትን ፡ ምክር ፡ ትቶ ፡ ለሕዝቡ ፡ ጽኑ ፡ ምላሽ ፡ መለሰላቸው ።

14 ፤ እንደ ፡ ብላቴናዎችም ፡ ምክር ። አባቴ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶባችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በቀንበራችኹ ፡ ላይ ፡
እጨምራለኹ ፤ አባቴ ፡ በዐለንጋ ፡ ገርፏችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በጊንጥ ፡ እገርፋችኊለኹ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሴሎናዊው ፡ በአኪያ ፡ አድርጎ ፡ ለናባጥ ፡ ልጅ ፡ ለኢዮርብዓም ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡
እንዲያጸና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተመድቦ ፡ ነበርና ፥ ንጉሡ ፡ ሕዝቡን ፡ አልሰማም ።

16 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ንጉሡ ፡ እንዳልሰማቸው ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ለንጉሡ ። በዳዊት ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ክፍል ፡
አለን ፧ በእሴይም ፡ ልጅ ፡ ዘንድ ፡ ርስት ፡ የለንም ። እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ድንኳኖቻችኹ ፡ ተመለሱ ፤ ዳዊት ፡
ሆይ ፥ አኹን ፡ ቤትኽን ፡ ተመልከት ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። እስራኤልም ፡ ወደ ፡ ድንኳኖቻቸው ፡ ኼዱ ።

17 ፤ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ በተቀመጡት ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ሮብዓም ፡ ነገሠባቸው ።

18 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ አስገባሪውን ፡ አዶኒራምን ፡ ሰደደ ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በድንጋይ ፡

ደበደቡት ፥ ሞተም ። ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ሠረገላው ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ሸሸ ።

19 ፤ እስራኤልም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከዳዊት ፡ ቤት ፡ ሸፈተ ።

20 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ኢዮርብዓም ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልከው ፡ ወደ ፡ ሸንጓቸው ፡
ጠሩት ፥ በእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አነገሡት ። ከብቻው ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ በቀረ ፡ የዳዊትን ፡ ቤት ፡ የተከተለ ፡ አንድ ፡
ሰው ፡ አልነበረም ።

21 ፤ ሮብዓምም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ፥ የእስራኤልንም ፡ ቤት ፡ ወግተው ፡ መንግሥቱን ፡ ወደሰሎሞን ፡ ልጅ ፡
ወደ ፡ ሮብዓም ፡ ይመልሱ ፡ ዘንድ ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ ኹሉና ፡ ከብንያም ፡ ነገድ ፡ የተመረጡትን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡
ሺሕ ፡ ሰልፈኛዎች ፡ ሰዎች ፡ ሰበሰበ ።

22 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ሳማያ ።

23 ፤ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ ለሮብዓምና ፡ ለይሁዳ ፡ ለብንያምም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ለቀረውም ፡ ሕዝብ ፡
ኹሉ ፦

24 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፥ አትውጡ ፥ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡
ወንድሞቻችኹን ፡ አትውጉ ፤ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለስ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፡ ሲል ፡
መጣ ። የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ሰሙ ፥ እንደእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ተመልሰው ፡ ኼዱ ።

25 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ሴኬምን ፡ ሠርቶ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ፤ ደግሞም ፡ ከዚያ ፡
ወጥቶ ፡ ጵኒኤልን ፡ ሠራ ።

26 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ በልቡ ፦ አኹን ፡ መንግሥቱ ፡ ወደዳዊት ፡ ቤት ፡ ይመለሳል ።

27 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መሥዋዕትን ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቢወጣ ፥ የዚህ ፡
ሕዝብ ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ ጌታቸው ፡ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ ይመለሳል ፥ እኔንም ፡ ይገድሉኛል ፡ አለ ።

28 ፤ ንጉሡም ፡ ተማከረ ፥ ኹለትም ፡ የወርቅ ፡ ጥጃዎች ፡ አድርጎ ፦ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትወጡ ፡
ዘንድ ፡ ይበዛባች኿ል ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጡኽን ፡ አማልክትኽን ፡ እይ ፡ አላቸው ።

29 ፤ አንዱን ፡ በቤቴል ፥ ኹለተኛውንም ፡ በዳን ፡ አኖረ ።

30 ፤ ለአንዱ ፡ ጥጃ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡ ፡ እስከ ፡ ዳን ፡ ድረስ ፡ ይኼድ ፡ ነበርና ፥ ይህ ፡ ኀጢአት ፡ ኾነ ።

31 ፤ በኰረብታዎቹም ፡ ላይ ፡ መስገጃዎች ፡ ሠራ ፥ ከሌዊ ፡ ልጆች ፡ካይደሉ ፡ ከሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ካህናትን ፡ አደረገ ።

32 ፤ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛውም ፡ ቀን ፡ በይሁዳ ፡ እንደሚደረግ ፡ በዓል ፡ ያለ ፡ በዓል ፡
አደረገ ፥ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ ሠዋ ፤ ለሠራቸውም ፡ ጥጃዎች ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ እንዲሁ ፡ በቤቴል ፡
አደረገ ፤ ለኰረብታ ፡ መስገጃዎችም ፡ የመረጣቸውን ፡ ካህናት ፡ በቤቴል ፡ አኖራቸው ።

33 ፤ በስምንተኛውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ በልቡ ፡ ባሰበው ፡ ቀን ፡ በቤቴል ፡ በሠራው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡
ሠዋ ፤ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በዓል ፡ አደረገላቸው ፤ በመሠዊያውም ፡ ሠዋ ፥ ዕጣንም ፡ ዐጠነ ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ምዕራፍ ፡ 13 ።

1 ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከይሁዳ ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ መጣ ፤ ኢዮርብዓምም ፡
ዕጣን ፡ እያጠነ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

2 ፤ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፦ መሠዊያ ፡ ሆይ ፥ መሠዊያ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ስሙ ፡
ኢዮስያስ ፡ የሚባል ፡ ልጅ ፡ ለዳዊት ፡ ቤት ፡ ይወለዳል ፤ ዕጣንም ፡ የሚያጥኑብኽን ፡ የኰረብታ ፡ መስገጃዎቹን ፡ ካህናት ፡
ይሠዋብኻል ፥ የሰዎቹንም ፡ ዐጥንት ፡ ያቃጥልብኻል ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ጮኸ ።

3 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፦ እግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እንሆ ፥ መሠዊያው ፡ ይሰነጠቃል ፥ በላዩም ፡
ያለው ፡ ዐመድ ፡ ይፈሳል ፡ ብሎ ፡ ምልክት ፡ ሰጠ ።

4 ፤ ንጉሡም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በቤቴል ፡ ባለው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ የጮኸውን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡
ጊዜ ፥ ኢዮርብዓም ፡ እጁን ፡ ከመሠዊያው ፡ አንሥቶ ፦ ያዙት ፡ አለ ። በርሱም ፡ ላይ ፡ የዘረጋት ፡ እጅ ፡ ደረቀች ፥ ወደ ፡
ርሱም ፡ ይመልሳት ፡ ዘንድ ፡ አልተቻለውም ።

5 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ምልክት ፡ መሠዊያው ፡ ተሰነጠቀ ፥ ዐመዱም ፡
ከመሠዊያው ፡ ፈሰሰ ።

6 ፤ ንጉሡም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፦ አኹን ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ ለምን ፥ እጄም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
ትመለስ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ጸልይ ፡ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመነ ፥ የንጉሡም ፡ እጅ ፡
ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመለሰች ፥ እንደ ፡ ቀድሞም ፡ ኾነች ።

7 ፤ ንጉሡም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ና ፡ እንጀራም ፡ ብላ ፥ በረከትም ፡ እሰጥኻለኹ ፡
አለው ።

8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ንጉሡን ፦ የቤትኽን ፡ እኩሌታ ፡ እንኳ ፡ ብትሰጠኝ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡
አልገባም ፥ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ እንጀራ ፡ አልበላም ፥ ውሃም ፡ አልጠጣም ፤

9 ፤ እንጀራ ፡ አትብላ ፥ ውሃም ፡ አትጠጣ ፥ በመጣኽበትም ፡ መንገድ ፡ አትመለስ ፡ በሚል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
ታዝዤያለኹና ፡ አለው ።

10 ፤ በሌላም ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፥ ወደ ፡ ቤቴልም ፡ በመጣበት ፡ መንገድ ፡ አልተመለሰም ።

11 ፤ በቤቴልም ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ነቢይ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፤ ልጆቹም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥተው ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በቤቴል ፡ ያደረገውን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ነገሩት ፡ ደግሞም ፡ ለንጉሡ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡
ለአባታቸው ፡ ነገሩት ።

12 ፤ አባታቸውም ፦ በማናቸው ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፧ አላቸው ። ልጆቹም ፡ ከይሁዳ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡
የኼደበትን ፡ መንገድ ፡ አመለከቱት ።

13 ፤ ልጆቹንም ፦ አህያውን ፡ ጫኑልኝ ፡ አላቸው ፤ አህያውንም ፡ በጫኑለት ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጠበት ።

14 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ በዃላ ፡ ኼደ ፤ በአድባርም ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ተቀምጦ ፡ አገኘውና ። ከይሁዳ ፡ የመጣኽ ፡
የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ አለው ። ርሱም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ።

15 ፤ ርሱም ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ና ፥ እንጀራም ፡ ብላ ፡ አለው ።

16 ፤ ርሱም ፦ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እመለስና ፡ እገባ ፡ ዘንድ ፡ አይቻለኝም ፤ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንጀራ ፡
አልበላም ፥ ውሃም ፡ አልጠጣም ፤

17 ፤ በዚያ ፡ እንጀራ ፡ አትብላ ፥ ውሃም ፡ አትጠጣ ፥ በመጣኽበትም ፡ መንገድ ፡ አትመለስ ፡ በሚል ፡ በእግዚአብሔር ፡
ቃል ፡ ተብሎልኛልና ፥ አለ ።

18 ፤ ርሱም ፦ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ነቢይ ፡ ነኝ ፤ መልአክም ፦ እንጀራ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ውሃም ፡ ይጠጣ ፡
ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ መልሰው ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተናገረኝ ፡ አለው ። ዋሽቶም ፡
ተናገረው ።

19 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ተመለሰ ፥ በቤቱም ፡ እንጀራ ፡ በላ ፥ ውሃም ፡ ጠጣ ።

20 ፤ በማእዱም ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደመለሰው ፡ ነቢይ ፡ መጣ ፤

21 ፤ ከይሁዳም ፡ ወደመጣው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡
ላይ ፡ ዐምፀኻልና ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘኽን ፡ ትእዛዝ ፡ አልጠበቅኽምና ፥

22 ፤ ተመልሰኽም ፦ እንጀራ ፡ አትብላ ፥ ውሃም ፡ አትጠጣ ፡ ባለኽ ፡ ስፍራ ፡ እንጀራ ፡ በልተኻልና ፥ ውሃም ፡
ጠጥተኻልና ፥ ሬሳኽ ፡ ወዳባቶችኽ ፡ መቃብር ፡ አይደርስም ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

23 ፤ እንጀራም ፡ ከበላ ፥ ውሃም ፡ ከጠጣ ፡ በዃላ ፡ አህያውን ፡ ጫነለት ።

24 ፤ ተመልሶም ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ አንበሳ ፡ አግኝቶ ፡ ገደለው ፤ ሬሳውም ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡
ነበር ፥ አህያውም ፡ በርሱ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ አንበሳውም ፡ ደግሞ ፡ በሬሳው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

25 ፤ እንሆም ፥ መንገድ ፡ ዐላፊ ፡ ሰዎች ፡ ሬሳው ፡ በመንገዱ ፡ ወድቆ ፡ አንበሳውም ፡ በሬሳው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ አዩ ፡
መጥተውም ፡ ሽማግሌው ፡ ነቢይ ፡ ተቀምጦባት ፡ በነበረው ፡ ከተማ ፡ አወሩ ።

26 ፤ ያም ፡ ከመንገድ ፡ የመለሰው ፡ ነቢይ ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ በእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ያመፀ ፡ ያ ፡
የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደተናገረው ፡ ቃል ፥ እግዚአብሔር ፡ ለአንበሳ ፡ አሳልፎ ፡
ሰጥቶታል ፤ ሰብሮም ፡ ገድሎታል ፡ አለ ።

27 ፤ ልጆቹንም ፦ አህያ ፡ ጫኑልኝ ፡ አላቸው ፤ እነርሱም ፡ ጫኑለት ።

28 ፤ ኼደም ፥ ሬሳውም ፡ በመንገድ ፡ ወድቆ ፥ በሬሳውም ፡ አጠገብ ፡ አህያውና ፡ አንበሳው ፡ ቆመው ፥ አንበሳው ፡
ሬሳውን ፡ ሳይበላው ፥ አህያውንም ፡ ሳይሰብረው ፡ አገኘ ።

29 ፤ ነቢዩም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ አንሣ ፥ በአህያውም ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፡ መለሰው ፤ ያለቅስለትና ፡ ይቀብረው ፡
ዘንድ ፡ ወደገዛ ፡ ከተማው ፡ ይዞት ፡ መጣ ።

30 ፤ ሬሳውንም ፡ በገዛ ፡ መቃብሩ ፡ አኖረው ፤ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እያሉ ፡ አለቀሱለት ።

31 ፤ ከቀበረውም ፡ በኋላ ፡ ልጆቹን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦ በሞትኹ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡
በተቀበረበት ፡ መቃብር ፡ ቅበሩኝ ፤ ዐጥንቶቼንም ፡ በዐጥንቶቹ ፡ አጠገብ ፡ አኑሩ ፤

32 ፤ በቤቴል ፡ ባለው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፥ በሰማርያም ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ባሉ ፡ በኰረብታዎቹ ፡ መስገጃዎች ፡ ላይ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የጮኸው ፡ ነገር ፡ በእውነት ፡ ይደርሳልና ።

33 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ከክፉ ፡ መንገድ ፡ አልተመለሰም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለኰረብታዎቹ ፡ መስገጃዎች ፡
አብልጦ ፡ ከሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ካህናትን ፡ አደረገ ፤ የሚወደውንም ፡ ኹሉ ፡ ይቀድስ ፡ ነበር ፥ ርሱም ፡ ለኰረብታዎቹ ፡
መስገጃዎች ፡ ካህን ፡ ይኾን ፡ ነበር ።

34 ፤ እስኪፈርስም ፡ ከምድርም ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ለኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ ኀጢአት ፡ ኾነ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ምዕራፍ ፡ 14 ።

1 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የኢዮርብዓም ፡ ልጅ ፡ አብያ ፡ ታመመ ።

2 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ሚስቱን ፦ ተነሺ ፥ የኢዮርብዓምም ፡ ሚስት ፡ እንደ ፡ ኾንሽ ፡ እንዳትታወቂ ፡ ልብስሽን ፡ ለውጪና ፡
ወደ ፡ ሴሎ ፡ ኺጂ ፤ እንሆ ፥ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እንድነግሥ ፡ የነገረኝ ፡ ነቢዩ ፡ አኪያ ፡ በዚያ ፡ አለ ።

3 ፤ በእጅሽም ፡ ዐሥር ፡ እንጀራና ፡ ዕንጐቻዎች ፡ አንድም ፡ ምንቸት ፡ ማር ፡ ይዘሽ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ኺጂ ፤ በልጁም ፡
የሚኾነውን ፡ ይነግርሻል ፡ አላት ።

4 ፤ የኢዮርብዓምም ፡ ሚስት ፡ እንዲሁ ፡ አደረገች ፥ ተነሥታም ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ኼደች ፤ ወደአኪያም ፡ ቤት ፡
መጣች ። አኪያም ፡ ስለ ፡ መሸምገሉ ፡ ዐይኖቹ ፡ ፈዝው ፡ ነበርና ፤ ማየት ፡ አልቻለም ።

5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አኪያን ፦ እንሆ ፥ ስለታመመው ፡ ልጇ ፡ ትጠይቅኽ ፡ ዘንድ ፡ የኢዮርብዓም ፡ ሚስት ፡
ትመጣለች ፤ ሌላ ፡ ሴትም ፡ መስላ ፡ ተሰውራለችና ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ በላት ፡ አለው ።

6 ፤ ርሷም ፡ በደጅ ፡ ስትገባ ፡ አኪያ ፡ የእግሯን ፡ ኰቴ ፡ ሰማ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ የኢዮርብዓም ፡ ሚስት ፡
ሆይ ፥ ግቢ ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ ሌላ ፡ ሴት ፡ መሰልሽ ፡ እኔም ፡ ብርቱ ፡ ወሬ ፡ ይገፔ ፡ ተልኬልሻለኹ ።

7 ፤ ኺጂ ፥ ለኢዮርብዓምም ፡ እንዲህ ፡ በዪው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከሕዝብ ፡
መካከል ፡ ለይቼ ፡ ከፍ ፡ አድርጌኽ ፡ ነበር ፥ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አድርጌኽ ፡ ነበር ፥

8 ፤ ከዳዊትም ፡ ቤት ፡ መንግሥቱን ፡ ቀድጄ ፡ ሰጥቼኽ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ እንደ ፡
ተከተለኝ ፥ በፊቴም ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እንዳደረገ ፥ ትእዛዜንም ፡ እንደ ፡ ጠበቀ ፡ እንደ ፡ ባሪያዬ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡

አልኾንኽም ።

9 ፤ ከአንተም ፡ አስቀድመው ፡ ከነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ ሠራኽ ፤ ታስቈጣኘም ፡ ዘንድ ፡ ኼደኽ ፡ ሌላዎችን ፡
አማልክትና ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎች ፡ አደረግኽ ፥ ወደ ፡ ኋላኽም ፡ ጣልኸኝ ።

10 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ በኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ አመጣለኹ ፥ ከኢዮርብአምም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡
የታሰረውንና ፡ የተለቀቀውን ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ እቈርጣለኹ ፤ ሰውም ፡ ፋንድያን ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ እንደሚጠርግ ፡
እኔ ፡ የኢዮርብዓምን ፡ ቤት ፡ ፈጽሜ ፡ እጠርጋለኹ ።

11 ፤ ከኢዮርብዓምም ፡ ወገን ፡ በከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ የሞተውን ፡ ውሻዎች ፡ ይበሉታል ፤ በሜዳውም ፡ የሞተውን ፡
የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ይበሉታል ፤ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ።

12 ፤ እንግዲህ ፡ ተነሥተሽ ፡ ወደ ፡ ቤትሽ ፡ ኺጂ ፤ እግርሽም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ይሞታል ።

13 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ያለቅሱለታል ፥ ይቀብሩትማል ፤ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
በኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ልጅ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ተገኝቶበታልና ፥ ከኢዮርብዓም ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ ይቀበራል ።

14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ያስነሣል ፤ ርሱም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የኢዮርብዓምን ፡ ቤት ፡
ያጠፋል ።

15 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሸምበቆ ፡ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚንቀሳቀስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሁ ፡ እስራኤልን ፡
ይመታል ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ያስቈጡ ፡ ዘንድ ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ተክለዋልና ፥ ለአባቶቻቸው ፡ ከሰጣቸው ፡
ከዚች ፡ ከመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ እስራኤልን ፡ ይነቅላል ፥ በወንዙም ፡ ማዶ ፡ ይበትናቸዋል ።

16 ፤ ስለበደለውና ፡ እስራኤልንም ፡ ስላሳተበት ፡ ስለ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ እስራኤልን ፡ ይጥላል ።

17 ፤ የኢዮርብዓምም ፡ ሚስት ፡ ተነሥታ ፡ ኼደች ፥ ወደ ፡ ቴርሳ ፡ መጣች ፤ ወደ ፡ ቤቱም ፡ መድረክ ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡
ልጁ ፡ ሞተ ።

18 ፤ በባሪያውም ፡ በነቢዩ ፡ በአኪያ ፡ እንደተነገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ቀበሩት ፡
አለቀሱለትም ።

19 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮርብዓም ፡ ነገር ፥ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፥ እንዴትም ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፥ እንሆ ፥ በእስራኤል ፡
ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

20 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ፤ ከአባቶቹም ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ ልጁም ፡
ናዳብ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

21 ፤ የሰሎሞንም ፡ ልጅ ፡ ሮብዓም ፡ በይሁዳ ፡ ነገሠ ፤ ሮብዓምም ፡ ንጉሥ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ የአርባ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡
ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ስሙን ፡ ያኖርባት ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ በመረጣት ፡ ከተማ ፡
በኢየሩሳሌም ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ የእናቱም ፡ ስም ፡ ናዕማ ፡ ነበረ ፤ ርሷም ፡ አሞናዊት ፡ ነበረች ።

22 ፤ ይሁዳም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ሠራ ፤ አባቶቻቸውም ፡ ከሠሩት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ አብዝተው ፡ በሠሩት ፡
ኀጢአት ፡ አስቈጡት ።

23 ፤ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ኰረብታ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ ቅጠሉ ፡ ከለመለመ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡
መስገጃዎችንና ፡ ሐውልቶችን ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶችንም ፡ ለራሳቸው ፡ ሠሩ ።

24 ፤ በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ሰዶማውያን ፡ ነበሩ ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳደዳቸውን ፡
የአሕዛብን ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

25 ፤ ሮብዓምም ፡ በነገሠ ፡ በዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ሺሻቅ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ መጣ ።

26 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ መዛግብትንና ፡ የንጉሥ ፡ ቤት ፡ መዛግብትን ፡ ወሰደ ፤ ኹሉንም ፡ ወሰደ ፤ ሰሎሞንም ፡
የሠራውን ፡ የወርቁን ፡ ጋሻ ፡ ኹሉ ፡ ወሰደ ።

27 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ በፋንታው ፡ የናስ ፡ ጋሻዎችን ፡ ሠራ ፥ የንጉሥንም ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ በሚጠብቁ ፡ በዘበኛዎች ፡

አለቃዎች ፡ እጅ ፡ አኖራቸው ።

28 ፤ ንጉሡም ፡ ዘወትር ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሲገባ ፡ ዘበኞዎች ፡ ይሸከሟቸው ፡ ነበር ፤ መልሰውም ፡ በዘበኞዎች ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያኖሯቸው ፡ ነበር ።

29 ፤ የቀረውም ፡ የሮብዓም ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

30 ፤ በዘመኑም ፡ ኹሉ ፡ በሮብዓምና ፡ በኢዮርብዓም ፡ መካከል ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ።

31 ፤ ሮብዓምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ። ልጁም ፡ አብያም ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ምዕራፍ ፡ 15 ።

1 ፤ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ በነገሠ ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ አብያም ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ኾነ ።

2 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ መዓካ ፡ የተባለች ፡ የአቤሴሎም ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

3 ፤ ከርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ባደረገው ፡ በአባቱ ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ ኼደ ፤ ልቡም ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ልብ ፡ ከአምላኩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ፍጹም ፡ አልነበረም ።

4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ልጁን ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ያስነሣ ፡ ዘንድ ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ አምላኩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መብራት ፡ ሰጠው ፤

5 ፤ ዳዊት ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፥ ካዘዘውም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ፈቀቅ ፡ አላለም ፡ ነበርና ።

6 ፤ በኢዮርብዓምና ፡ በሮብዓም ፡ ልጅ ፡ በአብያም ፡ መካከል ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ጠብ ፡ ነበረ ።

7 ፤ የቀረውም ፡ የአብያም ፡ ነገር ፥ ያደርገውም ፡ ኹሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧ በአብያምና ፡ በኢዮርብዓምም ፡ መካከል ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ።

8 ፤ አብያምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ቀበሩት ። ልጁም ፡ አሣ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

9 ፤ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮርብዓም ፡ በኻያኛውም ፡ ዓመት ፡ አሣ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

10 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ መዓካ ፡ የተባለች ፡ የአቤሴሎም ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

11 ፤ አሣ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

12 ፤ ከአገሩም ፡ ሰዶማውያንን ፡ አስወገደ ፥ አባቶቹም ፡ ያደረጉትን ፡ ጣዖታትን ፡ ኹሉ ፡ አራቀ ።

13 ፤ በማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ጣዖት ፡ ስለ ፡ ሠራች ፡ እናቱን ፡ መዓካን ፡ እቴጌ ፡ እንዳትኾን ፡ ሻራት ፤ ጣዖቷንም ፡ ሰበረው ፥ በቄድሮንም ፡ ፈፋ ፡ አጠገብ ፡ አቃጠለው ።

14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መስገጃዎች ፡ አላራቀም ፤ የአሣ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ፍጹም ፡ ነበረ ።

15 ፤ አባቱ ፡ የቀደሰውንና ፡ ርሱም ፡ የቀደሰውን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ዕቃውንም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አገባው ።

16 ፤ በአሣና ፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በባኦስ ፡ መካከል ፥ በዘመናቸው ፡ ኹሉ ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ።

17 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ባኦስ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤ ከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ከአሣ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ እንዳይወጣ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ማንም ፡ እንዳይገባ ፡ አድርጎ ፡ ራማን ፡ ሠራ ።

18 ፤ አሣም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በንጉሥ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ የቀረውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ኹሉ ፡ ወስዶ ፡ በባሪያዎቹ ፡ እጅ ፡ ሰጣቸው ፤ ንጉሡም ፡ አሣ ፡ በደማስቆ ፡ ለተቀመጠው ፡ ለዐዚን ፡ ልጅ ፡ ለጠብሪሞን ፡ ልጅ ፡ ለሶርያ ፡

ንጉሥ ፡ ለወልደ ፡ አዴር ፦

19 ፤ በእኔና ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ በአባቴና ፡ በአባትኽም ፡ መካከል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ጸንቷል ፤ እንሆ ፥ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ገጸ ፡
በረከት ፡ ሰድጄልኻለኹ ፤ ርሱ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንዲርቅ ፡ ኼደኽ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከባኦስ ፡ ጋራ ፡ ያለኽን ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ አፍርስ ፡ ብሎ ፡ ሰደደ ።

20 ፤ ወልደ ፡ አዴርም ፡ ለንጉሡ ፡ ለአሣ ፡ ዕሺ ፡ አለው ፤ የሰራዊቱንም ፡ አለቃዎች ፡ በእስራኤል ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡
ሰዶ ፡ ዒዮንንና ፡ ዳንን ፥ አቤልቤት ፡ መዓካንና ፡ ኪኔሬትን ፡ ኹሉ ፡ የንፍታሌምንም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ መታ ።

21 ፤ ባኦስም ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ራማን ፡ መሥራት ፡ ትቶ ፡ በቴርሳ ፡ ተቀመጠ ።

22 ፤ ንጉሡም ፡ አሣ ፡ በይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገረ ፤ ማንም ፡ ነጻ ፡ አልነበረም ፤ ባኦስም ፡ የሠራበትን ፡ የራማን ፡
ድንጋይና ፡ ዕንጨት ፡ ወሰዱ ፥ ንጉሡም ፡ አሣ ፡ የብንያምን ፡ ጌባንና ፡ ምጽጳን ፡ ሠራበት ።

23 ፤ የቀረውም ፡ የአሣ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ ጭከናውም ፡ ኹሉ ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ የሠራቸውም ፡ ከተማዎች ፥ በይሁዳ ፡
ነገሥት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧ ነገር ፡ ግን ፡ በሸመገለ ፡ ጊዜ ፡ እግሮቹ ፡ ታመሙ ።

24 ፤ አሣም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ። ልጁም ፡ ኢዮሳፍጥ ፡
በፋንታው ፡ ነገሠ ።

25 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ የኢዮርብዓም ፡ ልጅ ፡ ናዳብ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡
ነገሠ ፤ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

26 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፥ በአባቱም ፡ መንገድ ፡ እስራኤልንም ፡ ባሳተበት ፡ ኀጢአት ፡ ኼደ ።

27 ፤ ከይሳኮርም ፡ ቤት ፡ የኾነ ፡ የአኪያ ፡ ልጅ ፡ ባኦስ ፡ ተማማለበት ፤ ናዳብና ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ገባቶንን ፡ ከበው ፡
ነበርና ፥ ባኦስ ፡ በፍልስጥኤም ፡ አገር ፡ ባለው ፡ በገባቶን ፡ ገደለው ።

28 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ባኦስ ፡ ናዳብን ፡ ገደለው ፥ በፋንታውም ፡ ነገሠ ።

29 ፤ 30 ፤ ንጉሥም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ የኢዮርብዓምን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ መታ ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ስለሠራው ፡
ኀጢአት ፥ እስራኤልንም ፡ ስላሳተበት ፥ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስላስቈጣበት ፡ ማስቈጫ ፥ በባሪያው ፡
በሴሎናዊው ፡ በአኪያ ፡ እጅ ፡ እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፥ እስኪያጠፋው ፡ ድረስ ፡ ከኢዮርብዓም ፡
አንድ ፡ ትንፋሽ ፡ ያለው ፡ አላስቀረም ።

31 ፤ የቀረውም ፡ የናዳብ ፡ ነገርና ፡ ያደረገው ፡ ኹሉ ፥

(32 ፤ ) ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

33 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የአኪያ ፡ ልጅ ፡ ባኦስ ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በቴርሳ ፡
ንጉሥ ፡ ኾኖ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

34 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፥ በኢዮርብዓምም ፡ መንገድ ፡ እስራኤልንም ፡ ባሳተበት ፡ ኀጢአት ፡ ኼደ ።

__________________መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 16 ።

1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በባኦስ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ወደዐናኒ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዩ[162] ፡ መጣ ።

2 ፤ እኔ ፡ ከመሬት ፡ አስነሥቼ ፡ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አድርጌኻለኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ በኢዮርብዓም ፡
መንገድ ፡ ኼደኻል ፥ በኀጢአታቸውም ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ አስተኻቸዋል ።

3 ፤ ስለዚህም ፥ እንሆ ፥ ባኦስንና ፡ ቤቱን ፡ ፈጽሜ ፡ እጠርጋለኹ ፤ ቤትኽንም ፡ እንደ ፡ ናባጥ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡
ኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ አደርጋለኹ ።

4 ፤ ከባኦስም ፡ ወገን ፡ በከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚሞተውን ፡ ውሻዎች ፡ ይበሉታል ፤ በሜዳውም ፡ የሚሞተውን ፡ የሰማይ ፡

162 ዕብ. ፥ የሁ ፡ (ያምላክ) ።

ወሮች ፡ ይበሉታል ።

5 ፤ የቀረውም ፡ የባኦስ ፡ ነገር ፥ ሥራውና ፡ ጭከናውም ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡
አይደለምን ፧

6 ፤ ባኦስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በቴርሳም ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ኤላ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

7 ፤ በእጁም ፡ ሥራ ፡ ያስቈጣው ፡ ዘንድ ፥ እንደ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ስላደረገው ፡ ክፋት ፡
ኹሉ ፡ ርሱንም ፡ ስለ ፡ ገደለው ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በባኦስና ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ ወደዐናኒ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡
ኢዩ ፡ መጣ ።

8 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በኻያ ፡ ስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ የባኦስ ፡ ልጅ ፡ ኤላ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በቴርሳ ፡ ኹለት ፡
ዓመት ፡ ነገሠ ።

9 ፤ የእኩሌቶቹም ፡ ሠረገላዎች ፡ አለቃ ፡ ዘምሪ ፡ ተማማለበት ፤ ዔላም ፡ በቴርሳ ፡ ነበረ ፥ በቴርሳም ፡ በነበረው ፡ በቤት ፡
አሽከሮች ፡ አለቃ ፡ በአሳ ፡ ቤት ፡ ይሰክር ፡ ነበር ።

10 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በኻያ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ዘምሪ ፡ ገብቶ ፡ መታው ፡ ገደለውም ፥ በፋንታውም ፡
ነገሠ ።

11 ፤ ንጉሥም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ በዙፋኑም ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፥ የባኦስን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ መታ ፤ ከዘመዶችና ፡ ከወዳጆች ፡
ኹሉ ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ እንኳ ፡ አልቀረም ።

12 ፤ 13 ፤ ባኦስና ፡ ልጁ ፡ ኤላ ፡ ስለሠሩት ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፥ በምናምንቴም ፡ ሥራቸው ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ያስቈጡት ፡ ዘንድ ፡ እስራኤልን ፡ ስላሳቱበት ፡ ኀጢአት ፥ በነቢዩ ፡ በኢዩ ፡ እጅ ፡ በባኦስ ፡ ላይ ፡
እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘምሪ ፡ የባኦስን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ አጠፋ ።

14 ፤ የቀረውም ፡ የኤላ ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

15 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በኻያ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ዘምሪ ፡ በቴርሳ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ነገሠ ። ሕዝቡም ፡
በፍልስጥኤም ፡ አገር ፡ የነበረው ፡ ገባቶንን ፡ ከብው ፡ ነበር ።

16 ፤ ከተማዪቱንም ፡ ከብው ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ዘምሪ ፡ እንደ ፡ ዐመፀ ፥ ንጉሡንም ፡ እንደ ፡ ገደለ ፡ ሰሙ ፤ እስራኤልም ፡
ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ የሰራዊቱን ፡ አለቃ ፡ ዘንበሪን ፡ አነገሡ ።

17 ፤ ዘንበሪም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ከገባቶን ፡ ወጥተው ፡ ቴርሳን ፡ ከበቡ ።

18 ፤ ዘምሪም ፡ ከተማዪቱ ፡ እንደ ፡ ተያዘች ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፥ የንጉሡንም ፡ ቤት ፡
በራሱ ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ አቃጠለ ፤

19 ፤ ስላደረገውም ፡ ኀጢአት ፥ እስራኤልንም ፡ ስላሳተበት ፡ ኀጢአት ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡
አድርጓልና ፥ በኢዮርብዓምም ፡ መንገድ ፡ ኼዷልና ፥ ሞተ ።

20 ፤ የቀረውም ፡ የዘምሪ ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ዐመፅ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡
አይደለምን ፧

21 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ በኹለት ፡ ተከፈለ ፤ የሕዝቡም ፡ እኩሌታ ፡ የጎናትን ፡ ልጅ ፡ ታምኒን ፡
ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ ተከተለው ፤ እኩሌታውም ፡ ዘንበሪን ፡ ተከተለ ።

22 ፤ ዘንበሪንም ፡ የተከተለ ፡ ሕዝብ ፡ የጎናትን ፡ ልጅ ፡ ታምኒን ፡ በተከተለ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በረታ ፤ ታምኒም ፡
ሞተ ፥ ዘንበሪም ፡ ነገሠ ።

23 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በሠላሳ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ዘንበሪ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡
ነገሠ ። በቴርሳም ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

24 ፤ ከሳምርም ፡ በኹለት ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ የሰማርያን ፡ ተራራ ፡ ገዛ ፤ በተራራውም ፡ ላይ ፡ ሠራ ፥ የሠራውንም ፡
ከተማ ፡ በተራራው ፡ ባለቤት ፡ በሳምር ፡ ስም ፡ ሰማርያ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

25 ፤ ዘንበሪም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፥ ከርሱም ፡ አስቀድሞ ፡ ከነበሩት ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ከፋ ።

26 ፤ በናባጥም ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ መንገድ ፡ ኼሎ ፡ በምናምንቴም ፡ ነገራቸው ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ያስቈጡት ፡ ዘንድ ፡ እስራኤልን ፡ ባሳተበት ፡ ኀጢአት ፡ ኼደ ።

27 ፤ የቀረውም ፡ ዘንበሪ ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ጭከና ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡
አይደለምን ፧

28 ፤ ዘንበሪም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በሰማርያም ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ አክአብ[163] ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

29 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በሠላሳ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ የዘንበሪ ፡ ልጅ ፡ አክአብ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡
ነገሠ ፤ የዘንበሪም ፡ ልጅ ፡ አክአብ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

30 ፤ የዘንበሪም ፡ ልጅ ፡ አክአብ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

31 ፤ በናባጥም ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ መኼድ ፡ ታናሽ ፡ ነገር ፡ መሰለው ፥ የሲዶናውያንንም ፡ ንጉሥ ፡
የኤትበዓልን ፡ ልጅ ፡ ኤልዛቤልን ፡ አገባ ፥ ኼዶም ፡ በዓልን ፡ አመለከ ፡ ሰገደለትም ።

32 ፤ በሰማርያም ፡ በሠራው ፡ በበዓል ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ለበዓል ፡ መሠዊያ ፡ አቆመ ።

33 ፤ አክአብም ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ተከለ ፤ አክአብም ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የእስራኤልን ፡
አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያስቈጣውን ፡ ነገር ፡ አበዛ ።

34 ፤ በርሱም ፡ ዘመን ፡ የቤቴል ፡ ሰው ፡ አኪኤል[164] ፡ ኢያሪኮን ፡ ሠራ ፤ በነዌም ፡ ልጅ ፡ በኢያሱ ፡ እጅ ፡ እንደተነገረው ፡
እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፥ በበኵር ፡ ልጅ ፡ በአቢሮን ፡ መሠረቷን ፡ አደረገ ፥ በታናሹ ፡ ልጁም ፡ በሰጉብ ፡ በሮቿን ፡
አቆመ ።

__________________መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 17 ።

1 ፤ በገለዓድ ፡ ቴስቢ ፡ የነበረው ፡ ቴስብያዊው ፡ ኤልያስ ፡ አክአብን ፦ በፊቱ ፡ የቆምኹት ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡
ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ከአፌ ፡ ቃል ፡ በቀር ፡ በእነዚህ ፡ ዓመታት ፡ ጠልና ፡ ዝናብ ፡ አይኾንም ፡ አለው ።

2 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ለርሱ ፡ መጣለት ።

3 ፤ ከዚህ ፡ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ኺድ ፥ በዮርዳኖስም ፡ ትይዩ ፡ ባለው ፡ በኮራት ፡ ፈፋ ፡ ውስጥ ፡ ተሸሸግ ።

4 ፤ ከወንዙም ፡ ትጠጣለኽ ፥ ቍራዎችም ፡ በዚያ ፡ ይመግቡኽ ፡ ዘንድ ፡ አዝዣለኹ ።

5 ፤ ኼደም ፥ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ አደረገ ። ኼዶም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ትይዩ ፡ ባለው ፡ በኮራት ፡ ፈፋ ፡ ውስጥ ፡
ተቀመጠ ።

6 ፤ ቍራዎቹም ፡ በየጧትና ፡ በየማታው ፡ እንጀራና ፡ ሥጋ ፡ ያመጡለት ፡ ነበር ፤ ከወንዙም ፡ ይጠጣ ፡ ነበር ።

7 ፤ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዝናብ ፡ አልነበረምና ፡ ወንዙ ፡ ደረቀ ።

8 ፤ ተነሥተኽም ፡ በሲዶና ፡ አጠገብ ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሰራጽታ ፡ ኺድ ፥ በዚያም ፡ ተቀመጥ ፤

9 ፤ እንሆም ፥ ትመግብኽ ፡ ዘንድ ፡ አንዲት ፡ ባልቴት ፡ አዝዣለኹ ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መጣለት ።

10 ፤ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ሰራጽታ ፡ ኼደ ፤ ወደከተማዪቱም ፡ በር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ አንዲት ፡ ባልቴት ፡ በዚያ ፡ ዕንጨት ፡
ትለቅም ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ጠርቶ ፦ የምጠጣው ፡ ጥቂት ፡ ውሃ ፡ በጽዋ ፡ ታመጭልኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንሻለኹ ፡ አላት ።

11 ፤ ውሃም ፡ ልታመጣለት ፡ በኼደች ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ጠርቶ ፥ ቍራሽ ፡ እንጀራ ፡ በእጅሽ ፡ ይዘሽ ፡ ትመጪ ፡
ዘንድ ፡ እለምንሻለኹ ፡ አላት ።

12 ፤ ርሷም ፦ አምላክኽ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! በማድጋ ፡ ካለው ፡ ከዕፍኝ ፡ ዱቄት ፥ በማሰሮም ፡ ካለው ፡ ከጥቂት ፡

163 ዕብ. ፥ አኀአብ ፡ (እኀወ ፡ አብ ፥ ያባት ፡ ወንድም) ።

164 ዕብ. ፥ ሐይኤል ፡ (ሕያው ፡ እግዚአብሔር) ።

ዘይት ፡ በቀር ፡ እንጀራ ፡ የለኝም ፤ እንሆም ፥ ገብቼ ፡ ለኔና ፡ ለልጄ ፡ አጋግረው ፡ ዘንድ ፡ በልተነውም ፡ እንሞት ፡ ዘንድ ፡ ጥቂት ፡ ዕንጨት ፡ እሰበስባለኹ ፡ አለች ።

13 ፤ ኤልያስም ፡ አላት ፡— አትፍሪ ፤ ይልቅስ ፡ ኼደሽ ፡ እንዳልሺው ፡ አድርጊ ፤ አስቀድመሽ ፡ ግን ፡ ከዱቄቱ ፡ ለእኔ ፡ ታናሽ ፡ ዕንጐቻ ፡ አድርገሽ ፡ አምጪልኝ ፥ ከዚያም ፡ በዃላ ፡ ለአንቺና ፡ ለልጅሽ ፡ አድርጊ ፤

14 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡— በምድር ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዝናብ ፡ እስከሚሰጥበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፥ ዱቄቱ ፡ ከማድጋ ፡ አይጨረስም ፥ ዘይቱም ፡ ከማሰሮው ፡ አይጐድልም ።

15 ፤ ርሷም ፡ ኼዳ ፡ እንደ ፡ ኤልያሳ ፡ ቃል ፡ አደረገች ፤ ርሷና ፡ ርሱ ፡ ቤቷም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ በሉ ።

16 ፤ በኤልያስም ፡ እጅ ፡ እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዱቄቱ ፡ ከማድጋው ፡ አልተጨረሰም ፥ ዘይቱም ፡ ከማሰሮው ፡ አልጐደለም ።

17 ፤ ከዚያም ፡ በዃላ ፡ የባለቤቲቱ ፡ ልጅ ፡ ታመመ ፤ ትንፋሹም ፡ እስኪ.ታጣ ፡ ድረስ ፡ ደዌው ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ነበረ ።

18 ፤ ርሷም ፡ ኤልያስን ፡— የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኝ ፨ ኀጢአቴንስ ፡ ታሳስብ ፡ ዘንድ ፥ ልጄንስ ፡ ትገድል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥተኻልን ፨ አለችው ።

19 ፤ ኤልያስም ፡— ልጅሽን ፡ ስጪኝ ፡ አላት ። ከብብቷም ፡ ወስዶ ፡ ተቀምጦበት ፡ ወደነበረው ፡ ሰገነት ፡ አወጣው ፡ በዐልጋውም ፡ ላይ ፡ አጋደመው ።

20 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡— አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ልጇን ፡ በመግደልኽ ፡ ይህችን ፡ ትቀልበኝ ፡ የነበረቺቱን ፡ ባልቴት ፡ እንዲህ ፡ ደግሞ ፡ አስጨነቅኻትን ፨ ብሎ ፡ ጮኸ ።

21 ፤ በብላቴናውም ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ተዘረጋበት ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡— አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ የዚህ ፡ ብላቴና ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ትመለስ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የኤልያስን ፡ ቃል ፡ ሰማ ፤ የብላቴናው ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመለሰች ፥ ርሱም ፡ ዳነ ።

23 ፤ ኤልያስም ፡ ብላቴናውን ፡ ይዞ ፡ ከሰገነቱ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አወረደው ፥ ኤልያስም ፡— እንሆ ፥ ልጅሽ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፡ ብሎ ፡ ለእናቱ ፡ ሰጣት ።

24 ፤ ሴቲቱም ፡ ኤልያስን ፡— የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በአፍኽ ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አኹን ፡ ዐወቅኹ ፡ አለችው ።

## ___________________መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 18 ።

1 ፤ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በዃላ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ። ኺድ ፥ ለአክአብ ፡ ተገለጥ ፥ በምድር ፡ ላይም ፡ ዝናብ ፡ እሰጣለኹ ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ መጣ ።

2 ፤ ኤልያስም ፡ ለአክአብ ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ኼደ ፤ በሰማርያም ፡ ራብ ፡ ጸንቶ ፡ ነበር ።

3 ፤ አክአብም ፡ የቤቱን ፡ አዛዥ ፡ ዐብድዩ[165]ን ፡ ጠራ ፤ ዐብድዩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጅግ ፡ ይፈራ ፡ ነበር ።

4 ፤ ኤልዛቤልም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነቢያት ፡ ባስገደለች ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ መቶውን ፡ ነቢያት ፡ ወስዶ ፡ ዐምሳ ፡ ዐምሳውን ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ሸሽጎ ፡ እንጀራና ፡ ውሃ ፡ ይመግባቸው ፡ ነበር ።

5 ፤ አክአብም ፡ ዐብድዩን ፡— በአገሩ ፡ መካከል ፡ ወደውሃው ፡ ምንጭ ፡ ኹሉና ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ኹሉ ፡
ኺድ ፤ እንስሳዎችም ፡ ኹሉ ፡ እንዳይጠፉ ፡ ፈረሶችንና ፡ በቅሎዎችን ፡ የምናድንበት ፡ ሣር ፡ ምናልባት ፡ እናገኛለን ፡ አለው ።

6 ፤ ኹለቱም ፡ የሚመለሱበትን ፡ አገር ፡ ተካፈሉ ፤ አክአብም ፡ ለብቻው ፡ ባንድ ፡ መንገድ ፡ ዐብድዩም ፡ ለብቻው ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ኼዱ ።

165 ዕብ. ፥ ዖባድያህ ፡ (ዐብደ ፡ እግዚእ ፥ የጌታ ፡ አገልጋይ) ።

7 ፤ ዐብድዩም ፡ በመንገድ ፡ ሲኼድ ፥ እንሆ ፥ ኤልያስ ፡ ተገናኘው ፤ ዐብድዩም ፡ ዐወቀው ፥ በግንባሩም ፡
ተደፍቶ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ኤልያስ ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ አለ ።

8 ፤ ኤልያስም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ ኼደኽ ፡ ለጌታኽ ፦ ኤልያስ ፡ ተገኝቷል ፡ በል ፡ አለው ።

9 ፤ ዐብድዩም ፡ አለ ፦ እኔን ፡ ባሪያኽን ፡ እንዲገድል ፡ በአክአብ ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ኀጢአት ፡
አድርጌያለኹ ፧

10 ፤ አምላክኽ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ጌታዬ ፡ ይፈልግኽ ፡ ዘንድ ፡ ያልላከበት ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡
የለም ፤ ኹሉም ፦ በዚህ ፡ የለም ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ አንተን ፡ እንዳላገኙ ፡ መንግሥቱንና ፡ ሕዝቡን ፡ አምሏቸው ፡ ነበር ።

11 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፦ ኺድ ፥ ኤልያስ ፡ ተገኘ ፡ ብለኽ ፡ ለጌታኽ ፡ ንገር ፡ ትለኛለኽ ።

12 ፤ እኔም ፡ ከአንተ ፡ ጥቂት ፡ ራቅ ፡ ስል ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አንሥቶ ፡ ወደማላውቀው ፡ ስፍራ ፡
ይወስድኻል ፤ እኔም ፡ ገብቼ ፡ ለአክአብ ፡ ስናገር ፥ ባያገኝኽ ፡ ይገድለኛል ፤ እኔም ፡ ባሪያኽ ፡ ከትንሽነቴ ፡ ዠምሬ ፡
እግዚአብሔርን ፡ እፈራ ፡ ነበር ።

13 ፤ ኤልዛቤል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነቢያት ፡ ባስገደለች ፡ ጊዜ ፥ መቶውን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢያት ፡ ወስጄ ፥ ዐምሳ ፡
ዐምሳውንም ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ሸሽጌ ፥ እንጀራና ፡ ውሃ ፡ የመገብኳቸው ፥ ይህ ፡ ያደርግኹት ፡ ነገር ፡ በእውኑ ፡
ለጌታዬ ፡ አልታወቀኽምን ፧

14 ፤ አኹንም ፥ ኼደኽ ፦ ኤልያስ ፡ ተገኘ ፡ ብለኽ ፡ ለጌታኽ ፡ ንገር ፡ ትላለኽ ፤ ርሱም ፡ ይገድለኛል ።

15 ፤ ኤልያስም ፦ በፊቱ ፡ የቆምኹት ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! እኔ ፡ ዛሬ ፡ ለርሱ ፡ እገለጣለኹ ፡
አለ ።

16 ፤ ዐብድዩም ፡ አክአብን ፡ ሊገናኘው ፡ ኼደ ፥ ነገረውም ፤ አክአብም ፡ ኤልያስን ፡ ሊገናኘው ፡ መጣ ።

17 ፤ አክአብም ፡ ኤልያስን ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፦ እስራኤልን ፡ የምትገለባብጥ ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ አለው ።

18 ፤ ኤልያስም ፦ እስራኤልን ፡ የምትገለባብጡ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ትታችኹ ፡ በዓሊምን ፡
የተከተላችኹ ፥ አንተና ፡ የአባትኽ ፡ ቤት ፡ ናችኹ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ።

19 ፤ አኹንም ፡ ልከኽ ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፥ በኤልዛቤልም ፡ ማእድ ፡ የሚበሉትን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ የበዓልን ፡
ነቢያት ፥ አራት ፡ መቶም ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድን ፡ ነቢያት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ተራራ ፡ ሰብስብ ፡ አለ ።

20 ፤ አክአብም ፡ ወደእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ልኮ ፡ ነቢያቱን ፡ ኹሉ ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ተራራ ፡ ሰበሰበ ።

21 ፤ ኤልያስም ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ቀርቦ ፦ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ በኹለት ፡ ዐሳብ ፡ ታነክሳላችኹ ፧ እግዚአብሔር ፡
አምላክ ፡ ቢኾን ፡ ርሱን ፡ ተከተሉ ፤ በዓል ፡ ግን ፡ አምላክ ፡ ቢኾን ፡ ርሱን ፡ ተከተሉ ፡ አለ ። ሕዝቡም ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡
አልመለሱለትም ።

22 ፤ ኤልያስም ፡ ሕዝቡን ፡ አለ ፦ ከእግዚአብሔር ፡ ነቢያት ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ቀርቻለኹ ፤ የበዓል ፡ ነቢያት ፡ ግን ፡ አራት ፡
መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

23 ፤ ኹለት ፡ ወይፈኖች ፡ ይሰጡን ፤ እነርሱም ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፡ ይምረጡ ፥ እየብልቱም ፡ ይቍረጡት ፥ በዕንጨትም ፡
ላይ ፡ ያኑሩት ፥ በበታቹም ፡ እሳት ፡ አይጨምሩ ፤ እኔም ፡ ኹለተኛውን ፡ ወይፈን ፡ አዘጋጃለኹ ፥ በዕንጨቱም ፡ ላይ ፡
አኖረዋለኹ ፥ በበታቹም ፡ እሳት ፡ አልጨምርም ።

24 ፤ እናንተም ፡ የአምላካችኹን ፡ ስም ፡ ጥሩ ፥ እኔም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እጠራለኹ ፤ ስምቶም ፡ በእሳት ፡
የሚመልስ ፡ አምላክ ፥ ርሱ ፡ አምላክ ፡ ይኹን ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

25 ፤ ኤልያስም ፡ የበዓልን ፡ ነቢያት ፦ እናንተ ፡ ብዙዎች ፡ ናችኹና ፥ አስቀድማችኹ ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፡ ምረጡና ፡
አዘጋጁ ፤ የአምላካችኹንም ፡ ስም ፡ ጥሩ ፥ በበታቹም ፡ እሳት ፡ አትጨምሩ ፡ አላቸው ።

26 ፤ ወይፈኑንም ፡ ወስደው ፡ አዘጋጁ ፥ ከጧትም ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡ ድረስ ፦ በዓል ፡ ሆይ ፥ ስማን ፡ እያሉ ፡ የበዓልን ፡
ስም ፡ ጠሩ ። ድምፅም ፡ አልነበረም ፥ የሚመልስም ፡ አልነበረም ፤ በሠሩትም ፡ መሠዊያ ፡ ዙሪያ ፡ እያነከሱ ፡ ያሸበሽቡ ፡

ነበር ።

27 ፤ በቀትርም ፡ ጊዜ ፡ ኤልያስ ። አምላክ ፡ ነውና ፥ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ጩኹ ፤ ምናልባት ፡ ዐሳብ ፡ ይዞታል ፥ ወይም ፡ ፈቀቅ ፡ ብሏል ፥ ወይም ፡ ወደ ፡ መንገድ ፡ ኼዷል ፥ ወይም ፡ ተኝቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መቀስቀስ ፡ ያስፈልገዋል ፡ እያለ ፡ አላገጠባቸው ።

28 ፤ በታላቅም ፡ ቃል ፡ ይጮኹ ፥ እንደ ፡ ልማዳቸውም ፡ ደማቸው ፡ እስኪፈስ ፡ ድረስ ፡ ገላቸውን ፡ በካራና ፡ በቀጭኔ ፡ ይቧጭሩ ፡ ነበር ።

29 ፤ ቀትርም ፡ ካለፈ ፡ በዃላ ፡ መሥዋዕተ ፡ ሠርክ ፡ እስኪደርስ ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፤ ድምፅም ፡ አልነበረም ፥ የሚመልስና ፡ የሚያደምጥም ፡ አልነበረም ።

30 ፤ ኤልያስም ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ቅረቡ ፡ አላቸው ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረቡ ። ፈርሶ ፡ የነበረውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መሠዊያ ፡ አበጀ ።

31 ፤ ኤልያስም ፦ ስምኽ ፡ እስራኤል ፡ ይኾናል ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ደረሰለት ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ቊጥር ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ ድንጋዮች ፡ ወሰደ ።

32 ፤ ከድንጋዮችም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፤ በመሠዊያውም ፡ ዙሪያ ፡ ኹለት ፡ መስፈሪያ ፡ እኽል ፡ የሚያዝ ፡ ጕድጓድ ፡ ቈፈረ ።

33 ፤ ዕንጨቱንም ፡ በተርታ ፡ አደረገ ፥ ወይፈኑንም ፡ በብልት ፡ በብልቱ ፡ ቈረጠ ፥ በዕንጨቱም ፡ ላይ ፡ አኖረና ።

34 ፤ አራት ፡ ጋን ፡ ውሃ ፡ ሙሉ ፡ በሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ በዕንጨቱ ፡ ላይ ፡ አፍሱ ፡ አሉ ። ደግሞም ፦ ድገሙ ፡ አለ ፤ እነርሱም ፡ ደገሙ ። ርሱም ፦ ሦስተኛ ፡ አድርጉ ፡ አለ ፤ ሦስተኛም ፡ አደረጉ ።

35 ፤ ውሃውም ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ፈሰሰ ፤ ደግሞም ፡ ጕድጓዱን ፡ በውሃ ፡ ሞላው ።

36 ፤ መሥዋዕተ ፡ ሠርክ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ነቢዩ ፡ ኤልያስ ፡ ቀርቦ ፦ አቤቱ ፥ የአብርሃምና ፡ የይሥሐቅ ፡ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፥ እኔም ፡ ባሪያኽ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፥ ይህንም ፡ ኹሉ ፡ በቃልኽ ፡ እንዳደረግኹ ፡ ዛሬ ፡ ይገለጥ ።

37 ፤ አንተ ፥ አቤቱ ፥ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፥ ልባቸውንም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ መለስኽ ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ስማኝ ፥ አቤቱ ፥ ስማኝ ፡ አለ ።

38 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እሳት ፡ ወደቀች ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕቱንም ፡ ዕንጨቱንም ፡ ድንጋዮቹንም ፡ ዐፈሩንም ፡ በላች ፥ በጕድጓዱም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ውሃ ፡ ላሰች ።

39 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ያንን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፍተው ። እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ አሉ ።

40 ፤ ኤልያስም ፦ ከበዓል ፡ ነቢያት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳያመልጥ ፡ ያዙ ፡ አላቸው ። ያዟቸውም ፤ ኤልያስም ፡ ወደቂሶን ፡ ወንዝ ፡ ወስዶ ፡ በዚያ ፡ አሳረዳቸው ።

41 ፤ ኤልያስም ፡ አክአብን ፦ የዝናቡ ፡ ውሽንፍር ፡ እጅግ ፡ ነውና ፥ ተነሥተኽ ፡ ውጣ ፥ ብላም ፡ ጠጣም ፡ አለው ።

42 ፤ አክአብም ፡ ሊበላና ፡ ሊጠጣ ፡ ወጣ ፤ ኤልያስም ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ዐናት ፡ ወጣ ፤ ፊቱንም ፡ በጕልበቱ ፡ መካከል ፡ አድርጎ ፡ በግንባሩ ፡ ተደፋ ።

43 ፤ ብላቴናውንም ፦ ወጥተኽ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ተመልከት ፡ አለው ። ወጥቶም ፡ ተመልክቶም ፦ ምንም ፡ የለም ፡ አለ ። ርሱም ፦ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ተመላለስ ፡ አለው ። ብላቴናውም ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ተመላለሰ ።

44 ፤ በሰባተኛውም ፡ ጊዜ ፦ እንሆ ፥ የሰው ፡ እጅ ፡ የምታኽል ፡ ታናሽ ፡ ደመና ፡ ከባሕር ፡ ወጣች ፡ አለ ። ርሱም ፦ ወጥተኽ ፡ አክአብን ፦ ዝናብ ፡ እንዳይከለክልኽ ፡ ሠረገላን ፡ ጭነኽ ፡ ውረድ ፡ በለው ፡ አለ ።

45 ፤ ከጥቂትም ፡ ጊዜ ፡ በዃላ ፡ ሰማዩ ፡ ከደመናውና ፡ ከነፋሱ ፡ የተነሣ ፡ ጨለመ ፥ ብዙም ፡ ዝናብ ፡ ኾነ ፤ አክአብም ፡ በሠረገላው ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ኼደ ።

46 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በኤልያስ ፡ ላይ ፡ ነበረች ፤ ወገቡንም ፡ አሸንፍጦ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ እስኪገባ ፡

ድረስ ፡ በአክአብ ፡ ፊት ፡ ይሮጥ ፡ ነበር ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ምዕራፍ ፡ 19 ።

1 ፤ አክአብም ፡ ኤልያስ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ እንዳደረገ ፥ ነቢያትንም ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ እንደ ፡ ገደለ ፡ ለኤልዛቤል ፡ ነገራት ።

2 ፤ ኤልዛቤልም ፦ ነገ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነፍስኽን ፡ ከነዚህ ፡ እንደ ፡ አንዷቱ ፡ ነፍስ ፡ ባላደርጋት ፥ አማልክት ፡ ይህን ፡
ያድርጉብኝ ፡ ይህንም ፡ ይጨምሩብኝ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ መልእክተኛ ፡ ላከች ።

3 ፤ ኤልያስም ፡ ፈርቶ ፡ ተነሣ ፥ ነፍሱንም ፡ ሊያድን ፡ ኼደ ፥ በይሁዳም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ መጥቶ ፡
ብላቴናውን ፡ በዚያ ፡ ተወ ።

4 ፤ ርሱም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የሚያኽል ፡ መንገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ኼደ ፤ መጥቶም ፡ ከክትክታ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡
ተቀመጠና ፦ ይበቃኛል ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፥ እኔ ፡ ከአባቶቼ ፡ አልበልጥምና ፡ ነፍሴን ፡ ውሰድ ፡ ብሎ ፡ እንዲሞት ፡
ለመነ ።

5 ፤ በክትክታውም ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ተጋደመ ፡ እንቅልፍም ፡ አንቀላፋ ፤ እንሆም ፥ መልአክ ፡ ዳሰሰውና ። ተነሥተኽ ፡
ብላ ፡ አለው ።

6 ፤ ሲመለከትም ፥ እንሆ ፥ በራሱ ፡ አጠገብ ፡ የተጋገረ ፡ ዕንጐቻና ፡ በማሰሮ ፡ ውሃ ፡ አገኘ ። በላም ፡
ጠጣም ፥ ተመልሶም ፡ ተኛ ።

7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ደግሞ ፡ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ መጥቶ ፡ ዳሰሰውና ። የምትኼድበት ፡ መንገድ ፡ ሩቅ ፡
ነውና ፥ ተነሥተኽ ፡ ብላ ፡ አለው ።

8 ፤ ተነሥቶም ፡ በላ ፡ ጠጣም ፤ በዚያም ፡ ምግብ ፡ ኀይል ፡ እስከእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ እስከ ፡ ኰሬብ ፡ ድረስ ፡ አርባ ፡
ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ ኼደ ።

9 ፤ እዚያም ፡ ወዳለ ፡ ዋሻ ፡ መጣ ፥ በዚያም ፡ ዐደረ ፤ እንሆም ፦ ኤልያስ ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ የሚል ፡
የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጣ ።

10 ፤ ርሱም ፦ ለሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ ቀንቻለኹ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቃል ፡ ኪዳንኽን ፡
ትተዋልና ፥ መሠዊያዎችኽንም ፡ አፍርሰዋልና ፥ ነቢያትኽንም ፡ በሰይፍ ፡ ገድለዋልና ፤ እኔም ፡ ብቻዬን ፡
ቀርቻለኹ ፤ ነፍሴንም ፡ ሊወስዷት ፡ ይሻሉ ፡ አለ ።

11 ፤ ርሱም ፦ ውጣ ፥ በተራራውም ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቁም ፡ አለ ። እንሆም ፥ እግዚአብሔር ፡
ዐለፈ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ትልቅና ፡ ብርቱ ፡ ነፋስ ፡ ተራራዎቹን ፡ ሰነጠቀ ፡ አለቶቹንም ፡ ሰባበረ ፥ እግዚአብሔር ፡
ግን ፡ በነፋሱ ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም ። ከነፋሱም ፡ በኋላ ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ኾነ ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በምድር ፡
መናወጥ ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም ።

12 ፤ ከምድር ፡ መናወጥ ፡ በኋላ ፡ እሳት ፡ ኾነ ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በእሳቱ ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም ። ከእሳቱም ፡ በኋላ ፡
ትንሽ ፡ የዝምታ ፡ ድምፅ ፡ ኾነ ።

13 ፤ ኤልያስም ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱን ፡ በመጐናጸፊያው ፡ ሸፈነ ፥ ወጥቶም ፡ በዋሻው ፡ ደጃፍ ፡
ቆመ ። እንሆ ፦ ኤልያስ ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጣ ።

14 ፤ ርሱም ፦ ለሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ ቀንቻለኹ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቃል ፡ ኪዳንኽን ፡
ትተዋልና ፥ መሠዊያዎችኽንም ፡ አፍርሰዋልና ፥ ነቢያትኽንም ፡ በሰይፍ ፡ ገድለዋልና ፤ እኔም ፡ ብቻዬን ፡
ቀርቻለኹ ፤ ነፍሴንም ፡ ሊወስዷት ፡ ይሻሉ ፡ አለ ።

15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፦ ኺድ ፥ በመጣኽበትም ፡ መንገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡
ተመለስ ፤ ከዚያም ፡ በደረስኽ ፡ ጊዜ ፡ በሶርያ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አዛሄልን ፡ ቅባው ፤

16 ፤ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ የናሜሲን ፡ ልጅ ፡ ኢዩን ፡ ቅባው ፤ በፋንታኽም ፡ ነቢይ ፡ ይኾን ፡

ዘንድ ፡ የአቤልምሖላን ፡ ሰው ፡ የሣፋጥን ፡ ልጅ ፡ ኤልሳዕን ፡ ቅባው ፤ ከአዛሄልም ፡ ሰይፍ ፡ ያመለጠውን ፡ ኹሉ ።

17 ፤ ኢዩ ፡ ይገድለዋል ፤ ከኢዩም ፡ ሰይፍ ፡ ያመለጠውን ፡ ኹሉ ፡ ኤልሳዕ ፡ ይገድለዋል ።

18 ፤ እኔም ፡ ከእስራኤል ፡ ጒልበታቸውን ፡ ለበዓል ፡ ያላንበረከኩትን ፡ ኹሉ ፤ በአፋቸውም ፡ ያልሳሙትን ፡ ኹሉ ፤ ሰባት ፡
ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ለእኔ ፡ አስቀራለኹ ።

19 ፤ ከዚያም ፡ ኼደ ፤ የሣፋጥንም ፡ ልጅ ፡ ኤልሳዕን ፡ በዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ጥማድ ፡ በሬዎች ፡ ሲያርስ ፤ ርሱም ፡ ከዐሥራ ፡
ኹለተኛው ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ አገኘው ። ኤልያስም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ዐልፎ ፡ መጐናጸፊያውን ፡ ጣለበት ።

20 ፤ በሬዎቹንም ፡ ተወ ፤ ከኤልያስም ፡ በኋላ ፡ ሮጦ ፦ አባቴንና ፡ እናቴን ፡ እስማቸው ፡
ዘንድ ፤ እባክኽ ፤ ተወኝ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እከተልኻለኹ ፡ አለው ። ርሱም ፦ ኺድና ፡ ተመለስ ፤ ምን ፡
አድርጌልኻለኹ ፡ አለው ።

21 ፤ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶ ፡ ኹለቱን ፡ በሬዎች ፡ ወስዶ ፡ አረዳቸው ፤ ሥጋቸውንም ፡ በበሬዎቹ ፡ ዕቃ ፡
ቀቀለው ፤ ለሕዝቡም ፡ ሰጣቸው ፤ በሉም ፤ ርሱም ፡ ተነሥቶ ፡ ኤልያስን ፡ ተከትሎ ፡ ኼደ ፤ ያገለግለውም ፡ ነበር ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፤ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ምዕራፍ ፡ 20 ።

1 ፤ ለኢይዝራኤላዊውም ፡ ለናቡቴ ፡ በሰማርያ ፡ ንጉሥ ፡ በአክአብ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ነበረው ።

2 ፤ አክአብም ፡ ናቡቴን ፦ በቤቴ ፡ አቅራቢያ ፡ ነውና ፤ የአትክልት ፡ ቦታ ፡ አደርገው ፡ ዘንድ ፡ የወይን ፡ ቦታኽን ፡
ስጠኝ ፤ ስለ ፡ ርሱም ፡ ከርሱ ፡ የተሻለ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ እሰጥኻለኹ ፤ ወይም ፡ ብትወድ ፡ ግምቱን ፡ ገንዘብ ፡
እሰጥኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።

3 ፤ ናቡቴም ፡ አክአብን ፦ የአባቶቼን ፡ ርስት ፡ እሰጥኽ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያርቅልኝ ፡ አለው ።

4 ፤ ኢይዝራኤላዊውም ፡ ናቡቴ ፦ የአባቶቼን ፡ ርስት ፡ አልሰጥኽም ፡ ብሎ ፡ ስለተናገረው ፡ አክአብ ፡ ተቈጥቶና ፡ ተናዶ ፡
ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ። በዐልጋውም ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ፊቱን ፡ ተሸፋፈነ ፤ እንጀራም ፡ አልበላም ።

5 ፤ ሚስቱም ፡ ኤልዛቤል ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥታ ፦ ልብኽ ፡ የሚያዝን ፡ እንጀራስ ፡ የማትበላ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡
ነው ፡ አለችው ።

6 ፤ ርሱም ፦ ኢይዝራኤላዊውን ፡ ናቡቴን ፦ የወይንኽን ፡ ቦታ ፡ በገንዘብ ፡ ስጠኝ ፤ ወይም ፡ ብትወድ ፡ በፋንታው ፡
ሌላ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ እሰጥኻለኹ ፡ ብዬ ፡ ተናገርኹት ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ የወይን ፡ ቦታዬን ፡ አልሰጥኽም ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡
መለሰልኝ ፡ ነው ፡ አላት ።

7 ፤ ሚስቱም ፡ ኤልዛቤል ። አንተ ፡ አኹን ፡ የእስራኤልን ፡ መንግሥት ፡ ትገዛለኽን ፡ ተነሣ ፡ እንጀራም ፡ ብላ ፤ ልብኽም ፡
ደስ ፡ ይበላት ፤ የኢይዝራኤላዊውን ፡ የናቡቴን ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ እሰጥኻለኹ ፡ አለችው ።

8 ፤ በአክአብም ፡ ስም ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈች ፤ በማኅተሙም ፡ አተመችው ፤ በከተማው ፡ ወደ ፡ ነበሩትና ፡ ከናቡቴም ፡ ጋራ ፡
ወደተቀመጡት ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ከበርቴዎች ፡ ደብዳቤውን ፡ ላከች ።

9 ፤ በደብዳቤውም ፦ ስለ ፡ ጾም ፡ ዐዋጅ ፡ ንገሩ ፤ ናቡቴንም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ አስቀምጡት ፤

10 ፤ ኹለትም ፡ ምናምንቴ ፡ ሰዎች ፡ በፊቱ ፡ አስቀምጡና ፦ እግዚአብሔርንና ፡ ንጉሡን ፡ ሰድቧል ፡ ብለው ፡
ይመስክሩበት ፤ አውጥታችኹም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ውገሩት ፡ ብላ ፡ ጻፈች ።

11 ፤ በከተማውም ፡ የተቀመጡት ፡ የከተማው ፡ ሰዎችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከበርቴዎችም ፡ ኤልዛቤል ፡ እንዳዘዘቻቸውና ፡
ወደ ፡ እነርሱ ፡ በተላከው ፡ ደብዳቤ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

12 ፤ የጾም ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ፤ ናቡቴንም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ አስቀመጡት ።

13 ፤ ኹለቱም ፡ ምናምንቴ ፡ ሰዎች ፡ ገብተው ፡ በፊቱ ፡ ተቀመጡ ፤ ምናምንቴዎቹ ፡ ሰዎችም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ። ናቡቴ ፡
እግዚአብሔርንና ፡ ንጉሡን ፡ ሰድቧል ፡ ብለው ፡ በናቡቴ ፡ ላይ ፡ መሰከሩ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከከተማ ፡ አውጥተው ፡
እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ወገሩት ።

14 ፤ ወደ ፡ ኤልዛቤልም ፦ ናቡቴ ፡ ተወግሮ ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ላኩ ።

15 ፤ ኤልዛቤልም ፡ ናቡቴ ፡ ተወግሮ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ኤልዛቤል ፡ አክአብን ፦ ናቡቴ ፡ ሞቷል ፡ እንጂ ፡
በሕይወት ፡ አይደለምና ፡ በገንዘብ ፡ ይሰጥኽ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ያለውን ፡ የኢይዝራኤላዊውን ፡ የናቡቴን ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡
ተነሥተኽ ፡ ውረስ ፡ አለችው ።

16 ፤ አክአብም ፡ ናቡቴ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ይወርሰው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤላዊው ፡ ወደናቡቴ ፡ ወይን ፡
ቦታ ፡ ሊወርድ ፡ ተነሣ ።

17 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ቴስብያዊው ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

18 ፤ ተነሥተኽ ፡ በሰማርያ ፡ የሚኖረውን ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ አክአብን ፡ ትገናኝ ፡ ዘንድ ፡
ውረድ ፤ እንሆ ፣ ይወርሰው ፡ ዘንድ ፡ በወረደበት ፡ በናቡቴ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ አለ ።

19 ፤ አንተም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ገድለኽ ፡ ወረስኸውን ፧ ብለኽ ፡
ንገረው ። ደግሞም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ውሻዎች ፡ የናቡቴን ፡ ደም ፡ በላሱበት ፡ ስፍራ ፡ የአንተን ፡
ደም ፡ ደግሞ ፡ ውሻዎች ፡ ይልሱታል ፡ ብለኽ ፡ ንገረው ።

20 ፤ አክአብም ፡ ኤልያስን ፦ ጠላቴ ፡ ሆይ ፣ አገኘኸኝን ፧ አለው ። ርሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
መለሰለት ፦ አግኝቼኻለኹ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ለማድረግ ፡ ራስኽን ፡ ሸጠኻልና ።

21 ፤ እንሆ ፣ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣብኻለኹ ፣ ፈጽሞም ፡ እጠርግኻለኹ ፣ ከአክአብም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ የታሰረውንና ፡
የተለቀቀውን ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ አጠፋለኹ ፤

22 ፤ በሥራኽም ፡ አስቈጥተኸኛልና ፣ እስራኤልንም ፡ አስተኻልና ፣ ቤትኽን ፡ እንደ ፡ ናባጥ ፡ ልጅ ፣ እንደ ፡ ኢዮርብዓም ፡
ቤት ፣ እንደ ፡ አኪያም ፡ ልጅ ፣ እንደ ፡ ባኦስ ፡ ቤት ፡ አደርገዋለኹ ።

23 ፤ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኤልዛቤል ፦ በኢይዝራኤል ፡ ቅጥር ፡ አጠገብ ፡ ኤልዛቤልን ፡ ውሻዎች ፡ ይበሏታል ፡
ብሎ ፡ ተናገረ ።

24 ፤ ከአክአብም ፡ ወገን ፡ በከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ የሞተውን ፡ ውሻዎች ፡ ይበሉታል ፤ በሜዳውም ፡ የሞተውን ፡ የሰማይ ፡
ወፎች ፡ ይበሉታል ።

25 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉት ፡ ለመሥራት ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ ሸጠ ፣ ሚስቱም ፡ ኤልዛቤል ፡ እንደ ፡
ነዳችው ፣ እንደ ፡ አክአብ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

26 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ያጠፋቸው ፡ አሞራውያን ፡ እንደ ፡ ሠሩት ፡ ኹሉ ፣ ጣዖታትን ፡
በመከተል ፡ እጅግ ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ ሠራ ።

27 ፤ አክአብም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፡ ገላውን ፡ ማቅ ፡ አለበሰ ፣ ጾመም ፣ በማቅ ፡ ላይም ፡
ተኛ ፣ ቅስስ ፡ ብሎም ፡ ኼደ ።

28 ፤ 29 ፤ ደግሞም ፦ አክአብ ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ ተዋረደ ፡ አየኽን ፧ በፊቴ ፡ የተዋረደ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በልጁ ፡ ዘመን ፡
በቤቱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣለኹ ፡ እንጂ ፡ በርሱ ፡ ዘመን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላመጣም ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቃል ፡ ወደ ፡ ቴስብያዊው ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ መጣ ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፣ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ምዕራፍ ፡ 21 ።

1 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ጭፍራውን ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ነገሥት ፡
ነበሩ ፣ ፈረሶችና ፡ ሠረገላዎችም ፡ ነበሩ ፤ ወጥቶም ፡ ሰማርያን ፡ ከበበ ፣ ወጋትም ።

2 ፤ ወደእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አክአብ ።

3 ፤ ወልደ ፡ አዴር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ብርኽና ፡ ወርቅኽ ፡ ለእኔ ፡ ነው ፤ ሴቶችኽና ፡ መልካካሞቹም ፡ ልጆችኽ ፡ ለእኔ ፡
ናቸው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ መልእክተኛዎችን ፡ ላከ ።

4 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ መልሶ ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ እንዳልኽ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ለኔም ፡ የኾነው ፡ ኹሉ ፡
የአንተ ፡ ነው ፡ አለ ።

5 ፤ ደግሞም ፡ መልእክተኛዎች ፡ ተመልሰው ፦ ወልደ ፡ አዴር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ቀድሞ ፡ ብርኽንና ፡ ወርቅኽን ፡
ሴቶችኽንና ፡ ልጆችኽንም ፡ ትሰጠኛለኽ ፡ ብዬ ፡ ልኬብኽ ፡ ነበር ፤

6 ፤ ነገም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባሪያዎቼን ፡ እልክብኻለኹ ፥ ቤትኽንም ፡ የባሪያዎችኽንም ፡ ቤቶች ፡ ይበረብራሉ ፤ ደስ ፡
የሚያሠኛቸውንም ፡ ኹሉ ፡ በእጃቸው ፡ አድርገው ፡ ይወስዳሉ ፡ አሉ ።

7 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ የአገሩን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ ጠርቶ ፦ ተመልከቱ ፥ ይህም ፡ ሰው ፡ ክፉ ፡ እንዲሻ ፡
እዩ ፤ ስለ ፡ ሴቶቼ ፡ ስለ ፡ ልጆቼ ፡ ስለ ፡ ብሬና ፡ ወርቄም ፡ ላከብኝ ፥ እንቢም ፡ አላልኹም ፡ አለ ።

8 ፤ ሽማግሌዎችም ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፦ አትስማው ፥ ዕሺም ፡ አትበለው ፡ አሉት ።

9 ፤ ለወልደ ፡ አዴርም ፡ መልእክተኛዎች ፦ ለጌታዬ ፡ ለንጉሥ ፦ ለእኔ ፡ ለባሪያኽ ፡ በመዠመሪያ ፡ የላክኽብኝን ፡
ኹሉ ፡ አደርጋለኹ ፤ ይህን ፡ ግን ፡ አደርገው ፡ ዘንድ ፡ አይቻለኝም ፡ በሉት ፡ አላቸው ። መልእክተኛዎችም ፡ ተመልሰው ፡
ይህን ፡ አወሩለት ።

10 ፤ ወልደ ፡ አዴርም ፦ ለሚከተለኝ ፡ ሕዝብ ፡ የሰማርያ ፡ ትቢያ ፡ ጭብጥ ፡ ጭብጥ ፡ ይበቃው ፡ እንደ ፡
ኾነ ፥ አማልክት ፡ ይህን ፡ ያድርጉብኝ ፡ ይህን ፡ ይጨምሩብኝ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ።

11 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ መልሶ ፦ በቃ ፤ ለሰልፍ ፡ የሚታጠቅ ፡ ጋሻ ፡ ጦሩን ፡ እንደሚያወልቅ ፡ አይመካ ፡ አለው ።

12 ፤ ወልደ ፡ አዴርም ፡ ያን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከነገሥታቱ ፡ ጋራ ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ይጠጣ ፡
ነበር ፤ ባሪያዎቹንም ፦ ተሰለፉ ፡ አላቸው ፤ እነርሱም ፡ በከተማዪቱ ፡ ትይዩ ፡ ተሰለፉ ።

13 ፤ እንሆም ፥ ነቢይ ፡ ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አክአብ ፡ ቀርቦ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህን ፡ ብዙ ፡
ጭፍራ ፡ ኹሉ ፡ ታያለኽን ፡ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለኹ ፥ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡
ታውቃለኽ ፡ አለ ።

14 ፤ አክአብም ፦ በማን ፡ አለ ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በአውራጃዎቹ ፡ አለቃዎች ፡
ጕልማሳዎች ፥ አለ ፤ ርሱም ፦ ሰልፉን ፡ ማን ፡ ይዠምራል ፡ አለ ፤ ርሱም ፦ አንተ ፡ አለው ።

15 ፤ የአውራጃዎቹንም ፡ አለቃዎች ፡ ጕልማሳዎች ፡ ቈጠረ ፥ ኹለት ፡ መቶም ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ፤ ከነርሱም ፡
በኋላ ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፥ ቈጠረ ፥ ሰባትም ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

16 ፤ ቀትርም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ወጡ ፤ ወልደ ፡ አዴር ፡ ረዳቶቹም ፡ ሠላሳ ፡ ኹለቱ ፡ ነገሥታት ፡ እየጠጡ ፡ በድንኳን ፡
ውስጥ ፡ ይሰክሩ ፡ ነበር ።

17 ፤ የአውራጃዎቹም ፡ አለቃዎች ፡ ጕልማሳዎች ፡ አስቀድመው ፡ ወጡ ፤ ወልደ ፡ አዴርም ፡ መልእክተኛዎችን ፡
ላከ ፥ እነርሱም ፦ ሰዎች ፡ ከሰማርያ ፡ ወጥተዋል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

18 ፤ ርሱም ፦ ለዕርቅ ፡ ወይም ፡ ለሰልፍ ፡ መጥተው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በሕይወታቸው ፡ ያዟቸው ፥ አለ ።

19 ፤ እነዚህም ፡ የአውራጃዎች ፡ አለቃዎች ፡ ጕልማሳዎች ፡ ከከተማዪቱ ፡ ወጡ ፥ ሰራዊትም ፡ ተከተላቸው ።

20 ፤ ኹሉም ፡ በያንዳንዱ ፡ በፊቱ ፡ የነበረውን ፡ ሰው ፡ ገደለ ፥ ሶርያውያንም ፡ ሸሹ ፤ እስራኤልም ፡
አሳደዷቸው ፥ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ በፈረሱ ፡ አመለጠ ።

21 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥም ፡ ወጥቶ ፡ ፈረሶቹንና ፡ ሠረገላዎቹን ፡ ያዘ ፥ ሶርያውያንንም ፡ በታላቅ ፡ ውጊት ፡ ገደላቸው ።

22 ፤ ነቢዩም ፡ ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ቀርቦ ፦ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡
ይመጣብኻልና ፥ ኺድ ፥ በርታ ፥ የምታደርገውንም ፡ ተመልከትና ፡ ዕወቅ ፡ አለው ።

23 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ባሪያዎች ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፦ አምላካቸው ፡ የተራራዎች ፡ አምላክ ፡
ነው ፤ ስለዚህ ፥ በርትተውብን ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሜዳ ፡ ላይ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ብንዋጋ ፡ በርግጥ ፡ እንበረታባቸዋለን ።

24 ፤ ይህንም ፡ አድርግ ፤ ከጭፍራዎችኽ ፡ ነገሥታቱን ፡ አርቅ ፥ በፋንታቸውም ፡ አለቃዎችን ፡ ሹም ።

25 ፤ አንተም ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ጠፋብኽ ፡ ሰራዊት ፥ ፈረሱን ፡ በፈረስ ፡ ፋንታ ፥ ሠረገላውንም ፡ በሠረገላ ፡
ፋንታ ፥ ሰራዊትን ፡ ቍጠር ፤ በሜዳም ፡ ላይ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዋጋለን ፥ በርግጥም ፡
እንበረታባቸዋለን ። ምክራቸውንም ፡ ሰማ ፥ እንዲሁም ፡ አደረገ ። ፐ ፡

26 ፤ በሚመጣውም ፡ ዓመት ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ሶርያውያንን ፡ አሰለፈ ፥ ከእስራኤልም ፡ ጋራ ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
አፌቅ ፡ ወጣ ።

27 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተሰለፉ ፥ ሊገጥሟቸውም ፡ ወጡ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ኹለት ፡ ትናንሽች ፡
የፍየል ፡ መንጋዎች ፡ ኾነው ፡ በፊታቸው ፡ ሰፈሩ ፤ ሶርያውያን ፡ ግን ፡ ምድሩን ፡ ሞልተው ፡ ነበር ።

28 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ቀርቦ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፦ ሶርያውያን ፦ እግዚአብሔር ፡ የተራራዎች ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሸለቆ ፡ አምላክ ፡ አይደለም ፡
ብለዋልና ፥ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ጭፍራ ፡ ኹሉ ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለኹ ፥ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡
ታውቃላችኹ ፡ አለው ።

29 ፤ እነዚህም ፡ በእነዚያ ፡ ትይዩ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ሰፈሩ ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ተጋጠሙ ፥ የእስራኤልም ፡
ልጆች ፡ ከሶርያውያን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ እግረኛ ፡ ገደሉ ።

30 ፤ የቀሩትም ፡ ወደ ፡ አፌቅ ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ ሸሹ ፤ ቅጥሩም ፡ በቀሩት ፡ በኻያ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡
ላይ ፡ ወደቀ ። ወልደ ፡ አዴርም ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ወደ ፡ ዕልፍኙ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።

31 ፤ ባሪያዎቹም ፦ እንሆ ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ነገሥታት ፡ መሓሪዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ሰምተናል ፤ በወገባችን ፡ ማቅ ፡
እንታጠቅ ፥ በራሳችንም ፡ ገመድ ፡ እንጠምጥም ፥ ወደእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ እንውጣ ፤ ምናልባት ፡ ነፍስኽን ፡
ይምራታል ፡ አሉት ።

32 ፤ ወገባቸውንም ፡ በማቅ ፡ ታጠቁ ፥ በራሳቸውም ፡ ገመድ ፡ ጠመጠሙ ፥ ወደእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡
መጥተው ፦ ባሪያኽ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፦ ነፍሴን ፡ ትምራት ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ ብሏል ፡ አሉት ። ርሱም ፦ ገና ፡
በሕይወቱ ፡ አለን ፧ ወንድሜ ፡ ነው ፥ አለ ።

33 ፤ ሰዎቹም ፡ የደግ ፡ ምልክት ፡ አደረጉትና ፡ ቃሉን ፡ ከአፉ ፡ ተቀብለው ። ወንድምኽ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ አለ ፡
አሉት ። ርሱም ፦ ኺዱ ፥ አምጡት ፡ አለ ። ወልደ ፡ አዴርም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወጣ ፥ በሠረገላውም ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው ።

34 ፤ ወልደ ፡ አዴርም ፦ አባቴ ፡ ከአባትኽ ፡ የወሰዳቸውን ፡ ከተማዎች ፡ እመልስልኻለኹ ፤ አባቴ ፡ በሰማርያ ፡
እንዳደረገ ፡ አንተ ፡ በደማስቆ ፡ ገበያ ፡ ታደርጋለኽ ፡ አለው ። አክአብም ፦ እኔም ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እሰድኻለኹ ፡
አለ ። ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጎ ፡ ሰደደው ።

35 ፤ ከነቢያትም ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ባልንጀራውን ፦ ምታኝ ፡ አለው ። ሰውዮውም ፡
ይመታው ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለ ።

36 ፤ ርሱም ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማኽምና ፥ እንሆ ፥ ከእኔ ፡ በራቅኽ ፡ ጊዜ ፡ አንበሳ ፡ ይገድልኻል ፡
አለው ። ከርሱም ፡ በራቀ ፡ ጊዜ ፡ አንበሳ ፡ አግኝቶ ፡ ገደለው ።

37 ፤ ደግሞም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አግኝቶ ፦ ምታኝ ፡ አለው ። ሰውዮውም ፡ መታው ፥ በመምታቱም ፡ አቈሰለው ።

38 ፤ ነቢዩም ፡ ኼዶ ፡ በመንገድ ፡ አጠገብ ፡ ንጉሡን ፡ ቈየው ፤ ዐይኖቹንም ፡ በቀጸላው ፡ ሸፍኖ ፡ ተሸሸገ ።

39 ፤ ንጉሡም ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጮኸ ፦ ባሪያኽ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ መካከል ፡ ወጣ ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ ሰው ፡
ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አመጣና ፦ ይህን ፡ ሰው ፡ ጠብቅ ፥ ቢኰበልልም ፡ ነፍስኽ ፡ በነፍሱ ፡ ፋንታ ፡
ትኾናለች ፥ ወይም ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ ትከፍላለኽ ፡ አለኝ ።

40 ፤ ባሪያኽም ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ሲመለከት ፡ ጠፋ ፡ አለው ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፦ ፍርድኽ ፡ እንዲሁ ፡
ይኾናል ፤ አንተ ፡ ፈርደኸዋል ፡ አለው ።

41 ፤ ፈጥኖም ፡ ቀጸላውን ፡ ከዐይኑ ፡ አነሣ ፡ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ከነቢያት ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቀው ።

42 ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ ዕርም ፡ ያልኹትን ፡ ሰው ፡ ከእጅኽ ፡ አውጥተኻልና ፥ ነፍስኽ ፡

በነፍሱ ፡ ፋንታ ፡ ሕዝብኽም ፡ በሕዝቡ ፡ ፋንታ ፡ ይኾናሉ ፡ አለው ።

43 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ እየተቈጣና ፡ እየተናደደ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ፥ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ መጣ ።

## መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ምዕራፍ ፡ 22 ።

1 ፤ ሶርያና ፡ እስራኤልም ፡ ሳይዋጉ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ተቀመጡ ።

2 ፤ በሦስተኛውም ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ወረደ ።

3 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ባሪያዎቹን ፦ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ የእኛ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፥ እኛም ፡ ከሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ሳንወስዳት ፡ ዝም ፡ እንዳልን ፡ ታውቃላችኹን ፧ አላቸው ።

4 ፤ ኢዮሳፍጥንም ፦ በሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ እንዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ትመጣለኽን ፧ አለው ። ኢዮሳፍጥም ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፦ እኔ ፡ እንደ ፡ አንተ ፥ ሕዝቤም ፡ እንደ ፡ ሕዝብኽ ፥ ፈረሶቼም ፡ እንደ ፡ ፈረሶችኽ ፡ ናቸው ፡ አለው ።

5 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አስቀድመኽ ፡ ትጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

6 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ነቢያቱን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ የሚያኽሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሰብስቦ ፦ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ለሰልፍ ፡ ልኺድን ፧ ወይስ ፡ ልቅር ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ በንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታልና ፥ ውጣ ፡ አሉት ።

7 ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ ግን ፦ እንጠይቀው ፡ ዘንድ ፡ ሌላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ በዚህ ፡ አይገኝምን ፧ አለ ።

8 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ እግዚአብሔርን ፡ የምንጠይቅበት ፡ የይምላ ፡ ልጅ ፡ ሚክያስ[166] ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክፉ ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ ትንቢት ፡ አይናገርልኝምና ፡ እጠላዋለኹ ፡ አለው ። ኢዮሳፍጥም ፦ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ አይበል ፡ አለ ።

9 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ አንዱን ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ ጠርቶ ፦ የይምላን ፡ ልጅ ፡ ሚክያስን ፡ ፈጥነኽ ፡ አምጣ ፡ አለው ።

10 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ ለብሰው ፡ በሰማርያ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ አጠገብ ፡ በአደባባይ ፡ በዙፋኖቻቸው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ ነቢያቱም ፡ ኹሉ ፡ በፊታቸው ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ።

11 ፤ የክንዓና ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስም ፡ የብረት ፡ ቀንዶች ፡ ሠርቶ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በእነዚህ ፡ ሶርያውያንን ፡ ትወጋለኽ ፡ አለ ።

12 ፤ ነቢያትም ፡ ኹሉ ፦ እግዚአብሔር ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታልና ፥ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ኺድና ፡ ተከናወን ፡ እያሉ ፡ እንዲህ ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ።

13 ፤ ሚክያስንም ፡ ሊጠራ ፡ የኼደ ፡ መልእክተኛ ፦ እንሆ ፥ ነቢያት ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ አፍ ፡ ኾነው ፡ ለንጉሡ ፡ መልካምን ፡ ይናገራሉ ፤ ቃልኽም ፡ እንደ ፡ ቃላቸው ፡ እንዲኾን ፡ መልካም ፡ እንድትናገር ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

14 ፤ ሚክያስም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! እግዚአብሔር ፡ የሚነግረኝን ፡ ርሱን ፡ እናገራለኹ ፡ አለ ።

15 ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፦ ሚክያስ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ለሰልፍ ፡ እንኺድን ፧ ወይስ ፡ እንቅር ፧ አለው ፤ ርሱም ፦ ውጣና ፡ ተከናወን ፤ እግዚአብሔርም ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

16 ፤ ንጉሡም ፦ ከእውነት ፡ በቀር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እንዳትነግረኝ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ አምልኻለኹ ፧ አለው ።

17 ፤ ርሱም ፦ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ጠባቂ ፡ እንደሌላቸው ፡ በጎች ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ ተበትነው ፡

166 ዕብ. ፥ ሚከያሁ ፡ (ማን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፧ ) ።

አየኹ ፤ እግዚአብሔርም ፦ ለእነዚህ ፡ ጌታ ፡ የላቸውም ፡ እያንዳንዱም ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለስ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡
ተናገረ ።

18 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ክፉ ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ እንደማይናገርልኝ ፡ አላልኹኽምን ፧ አለው ።

19 ፤ ሚክያስም ፡ አለ ፦ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስማ ፤ እግዚአብሔር ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፥ የሰማይም ፡
ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ በቀኙና ፡ በግራው ፡ ቆመው ፡ አየኹ ።

20 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ወጥቶ ፡ በሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ይወድቅ ፡ ዘንድ ፡ አክአብን ፡ የሚያሳስት ፡ ማን ፡
ነው ፧ አለ ። አንዱም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፥ ሌላውም ፡ እንዲያ ፡ የለ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ።

21 ፤ መንፈስም ፡ ወጣ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፦ እኔ ፡ አሳስተዋለኹ ፡ አለ ።

22 ፤ እግዚአብሔርም ፦ በምን ፧ አለው ፤ ርሱም ፦ ወጥቼ ፡ በነቢያቱ ፡ ኹሉ ፡ አፍ ፡ ሐሰተኛ ፡ መንፈስ ፡ እኾናለኹ ፡
አለ ። እግዚአብሔርም ፦ ማሳሳትስ ፡ ታሳስተዋለኽ ፥ ይኾንልኻልም ፤ ውጣ ፥ እንዲሁም ፡ አድርግ ፡ አለ ።

23 ፤ አኹንም ፦ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእነዚህ ፡ በነቢያትኽ ፡ ኹሉ ፡ አፍ ፡ ሐሰተኛ ፡ መንፈስ ፡
አድርጓል ፤ እግዚአብሔርም ፡ በላይኽ ፡ ክፉ ፡ ተናግሮብኻል ።

24 ፤ የክንዓናም ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ቀረበ ፥ ሚክያስንም ፡ ጕንጩን ፡ በጥፊ ፡ መታውና ። አንተን ፡ ሊናገር ፡
የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በምን ፡ መንገድ ፡ ከእኔ ፡ ዐለፈ ፧ አለ ።

25 ፤ ሚክያስም ፦ እንሆ ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ ልትሸሸግ ፡ ወደ ፡ ዕልፍኝኽ ፡ በኼድኽ ፡ ጊዜ ፡ ታያለኽ ፡ አለ ።

26 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፦ ሚክያስን ፡ ውሰዱ ፥ ወደከተማዪቱም ፡ ሹም ፡ ወደ ፡ ዐሞን ፡ ወደንጉሡም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡
ኢዮአስ ፡ መልሳችኹ ፦ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

27 ፤ በደኅና ፡ እስክመለስ ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ በግዞት ፡ አኑሩት ፥ የመከራም ፡ እንጀራ ፡ መግቡት ፥ የመከራም ፡
ውሃ ፡ አጠጡት ፡ በሉ ፡ አለ ።

28 ፤ ሚክያስም ፦ በደኅና ፡ ብትመለስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኔ ፡ የተናገረ ፡ አይደለም ፡ አለ ። ደግሞም ፦ አሕዛብ ፡
ኹሉ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፡ አለ ።

29 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ወጡ ።

30 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ልብሴን ፡ ለውጬ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ እገባለኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ልብስኽን ፡
ልበስ ፡ አለው ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ልብሱን ፡ ለውጦ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ገባ ።

31 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ሠላሳ ፡ ኹለቱን ፡ የሠረገላዎች ፡ አለቃዎች ፦ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በቀር ፥ ታናሽ ፡ ቢኾን ፡
ወይም ፡ ታላቅ ፡ ከማናቸውም ፡ ጋራ ፡ አትግጠሙ ፡ ብሎ ፡ አዞ ፡ ነበር ።

32 ፤ የሠረገላዎች ፡ አለቃዎችም ፡ ኢዮሳፍጥን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፦ በእውነት ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡
አሉ ፤ ይገጥሙትም ፡ ዘንድ ፡ ከበቡት ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ጮኸ ።

33 ፤ የሠረገላዎች ፡ አለቃዎችም ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እንዳልኾነ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ርሱን ፡ ከማሳደድ ፡ ተመለሱ ።

34 ፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ ቀስቱን ፡ ድንገት ፡ ገትሮ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ በጥሩሩ ፡ ልብስ ፡ መጋጠሚያ ፡ በኩል ፡
ወጋው ፤ ሠረገለኛውንም ፦ መልሰኽ ፡ ንዳ ፥ ተወግቻለኹና ፡ ከሰልፍ ፡ ውስጥ ፡ አውጣኝ ፡ አለው ።

35 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰልፍ ፡ በረታ ፤ ንጉሡም ፡ በሶርያውያን ፡ ፊት ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ተደግፎ ፡ ነበር ፥ ማታም ፡
ሞተ ፤ የቊስሉም ፡ ደም ፡ በሠረገላው ፡ ውስጥ ፡ ፈሰሰ ።

36 ፤ በሰራዊቱም ፡ መካከል ፡ ፀሓይ ፡ ስትገባ ፦ ንጉሡ ፡ ሞቷልና ፥ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፥ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡
አገሩ ፡ ይኺድ ፡ የሚል ፡ ጩኸት ፡ ኾነ ።

37 ፤ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ መጡ ፥ ንጉሡንም ፡ በሰማርያ ፡ ቀበሩት ።

38 ፤ አመንዝራዎች ፡ በታጠቡባት ፡ በሰማርያ ፡ ኵሬ ፡ ሠረገላውን ፡ ዐጠቡት ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንደተናገረው ፡ ቃል ፡

ውሻዎች ፡ ደሙን ፡ ላሱት ።

39 ፤ የቀረውም ፡ የአክአብ ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ዅሉ ፥ ከዝኆን ፡ ጥርስም ፡ የሠራው ፡ ቤት ፥ የሠራቸውም ፡ ከተማዎች ፡ ዅሉ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

40 ፤ አክአብም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ልጁ ፡ አካዝያስ[167] ፡ ነገሠ ።

41 ፤ አክአብም ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ የአሣ ፡ ልጅ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

42 ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጐበዝ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ ዓዘባ ፡ የተባለች ፡ የሺልሒ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

43 ፤ በአባቱም ፡ በአሣ ፡ መንገድ ፡ ዅሉ ፡ ኼደ ፥ ከርሱም ፡ ፈቀቅ ፡ አላለም ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ አደረገ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መስገጃዎች ፡ አላራቀም ፤ ሕዝቡ ፡ ገና ፡ በኰረብታዎቹ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

44 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ታረቀ ።

45 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ጭከና ፥ እንዴትም ፡ እንደ ፡ ተወጋ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

46 ፤ ከአባቱ ፡ ከአሣ ፡ ዘመን ፡ የተረፉትን ፡ ሰዶማውያን ፡ ከምድር ፡ አጠፋ ።

47 ፤ በኤዶምያስም ፡ ንጉሥ ፡ አልነበረም ፤ ሹሙም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ነበረ ።

48 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ወደ ፡ ኦፊር ፡ ኼደው ፡ ወርቅ ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ የተርሴስን ፡ መርከቦች ፡ ሠራ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መርከቦቹ ፡ በዔጽዮንጋብር ፡ ተሰበሩ ፡ እንጂ ፡ አልኼዱም ።

49 ፤ የአክአብም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ባሪያዎቼ ፡ ከባሪያዎችኽ ፡ ጋራ ፡ በመርከብ ፡ ይኺዱ ፡ አለው ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ ግን ፡ አልወደደም ።

50 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ፤ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ልጁ ፡ ኢዮራም[168] ፡ ነገሠ ።

51 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮሳፍጥ ፡ በዐሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የአክአብ ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ መንገሥ ፡ ዠመረ ፤ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

52 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፥ በአባቱና ፡ በእናቱም ፡ መንገድ ፥ እስራኤልንም ፡ ባሳተው ፡ በናባጥ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ መንገድ ፡ ኼደ ።

53 ፤ በዓልንም ፡ አመለከ ፡ ሰገደለትም ፤ አባቱም ፡ እንዳደረገ ፡ ዅሉ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቈጣ ፨

167 ዕብ. ፥ አኀዝያሁ ።

168 ዕብ. ፥ የውራም ።